# ይግባኝ ለክርስቶስ

## የአቡነ ጴጥሮስ የመጨረሻ እስትንፋስ

*ጸሐፊው ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ*
*አዘጋጅቶ ሊያቀርብ ይግባኙን ለክርስቶስ*
*ቁርጥ ቃሉን ጻፈ በመትረየስ እርሳስ*

አዘጋጅ:- አባ ቀውስጦስ
የሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ
1999 ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

© ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ
1999 ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

አድራሻ፡- ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት
ስልክ 0111 35 07 13
መ.ሣ.ቁ 29
**ፍቼ**
ስልክ 0111 57 97 14
**አዲስ አበባ**


# ምስጋና

ይህችን እነስተኛ መጽሐፍ ሳዘጋጅ፣ በኮምፒውተር ረቂቁን በመጻፍ፣ እርማት በማድረግ፣ ጽሑፉን በአጠቃላይ ለኅትመት ዝግጁ እስኪሆን ድረስ በማንኛውም መንገድ አስተዋጽኦ ላደረጋችሁ ልጆቼ ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ በበረከት ይጎብኛችሁ፣ በረድኤት ይጠብቃችሁ፣ በረከተ ቅዱሳንን ያድላችሁ:: ከዚህም ሁሉ ጋር ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ::

አባ ቀውስጦስ ሊቀ ጳጳስ

www.ethiopianorthodox.org

# መታሰቢያነቱ



ሐምሌ 1928 ዓ.ም. በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ፍቅር ተይዘው በአረመኔውና በጨካኙ የኢጣልያ ጦር በጥይት ተደብድበው ደግባኛቸውን ለክርስቶስ ሳቀረቡት ለሰማዕቱ ሊቀ ጳጳስ ለብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ይሁንልኝ።

አባ ቀውስጦስ ሊቀ ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ
የሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ምክንያተ ስያሜ ---------- 7
መቅድም ---------- 8
መግቢያ ---------- 12
ምዕራፍ አንድ የዱር ሡልጣን ጉዳይ ---------- 16
ምዕራፍ ሁለት ግብፃውያን በአባቶቻችን ላይ ---------- 25
ምዕራፍ ሦስት ግብፃውያን ኢትዮጵያውያንን አጠቁ ሲባል ---------- 33
ምዕራፍ አራት የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ---------- 41
ምዕራፍ አምስት ምስራባውያን በክህደት መርዝ ያደነዘዟቸው ---------- 52
አንቀጽ አንድ ከብርሃን ወደ ጨለማ አሳዛኝ ጉዞ ---------- 53
አንቀጽ ሁለት የማይገባ ትምክህት ---------- 55
ምዕራፍ ስድስት ስደተኞቹ አነማን ናቸው ---------- 56
አስረጅ አንድ ኤልያስ ስለ ናቡቴ ---------- 59
አስረጅ ሁለት ዮሐንስ አፈወርቅ ስለደህይቱ መበለት ---------- 61
አንቀጽ ሦስት በአሁኑ ጊዜ የአክአብን ያህል እንኳ
የሚጸጸት አልተገኘም:: ---------- 65
ምዕራፍ ሰባት ክህደትን በዲሞክራሲ ያወጀ ትውልድ ---------- 68
ምዕራፍ ስምንት እናቶች በሕፃናት ላይ ---------- 75
አንቀጽ አራት ይህ ወቅት እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ ወቅት ነው ---------- 85
አንቀጽ አምስት ብሔራዊ ፊደልን መናቅ ቅኝ ተገዥነትን መናፈቅ ነው 87
አንቀጽ ስድስት ዘመናችን ያፈራው ትውልድ አታላይ ብቻ
ሳይሆን ሾተላይም ነው:: ---------- 90
የፕሮፌሰር ስቬን ሩቢንሰን ምስክርነት ---------- 94




# ምክንያተ ስያሜ

የዚህን መጽሐፍ ርእስ «ይግባኝ ለክርስቶስ» ስማለት የሰየምኩበት እና ምክንያተ ስያሜውንም የጻፍኩበት ምክንያት ከዚህ የሚከተለው ነው::

ይህን ለመጻፍ ያነሳሱኝ ሁኔታዎች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስመለከታቸውና እያየሁ ሳዝንባቸው የነበሩት በዚሁ መጽሐፍ የተካተቱት ነገሮች ናቸው:: እነዚህን ነገሮች ተመልክቼም በመጽሐፌ እንደገለጽኩት ለክርስቶስ ይግባኝ ያሰኘል በምልበት ጊዜ ስማዕቱ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ በምዕራባውያኑ ዘንድ ያሳለፍነው ምዕተ ዓመት ሰማዕት ተብለው ተመረጡ:: የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት እና ዩኔስኮ በጋራ ባቋቋሙት ኮሚቴ ከተመረጡ በኋላ ሐምሌ 22 ቀን 1993 ዓ.ም (29 July, 2001) በስዊድን ሀገር በስዊድናውያን ዘንድ በስማቸው የጸሎት ቤት ተሠርቶ ተመረቀ:: ከዚህም በኋላ ጥቅምት 12 ቀን 1998 ዓ.ም. በተካሔደው ቅዱስ ሲኖዶስ «አቡነ ጴጥሮስ ሰማዕተ ጽድቅ ዘኢትዮጵያ» ተብለው የሰማዕትነት ስማቸው ጸድቆ ቅድስና ተሰጣቸው:: ይህንንም ተከትሉ በተወለዱባት ከተማ በፍቼ የመታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን እየታነጸላቸው ይገኛል:: ከዚህም በመነሣት 70ኛ ዓመት በዓለ ዕረፍታቸውን ሐምሌ 22 ቀን 1998 ዓ.ም በፍቼ ከተማ ለማክበር የምዘጋጅበት ጊዜ ይህን መጽሐፍ ለማሳተም ከተነሣሁበት ጊዜ ጋር ተገጣጠመ:: ይህም ብቻ ሳይሆን በመጽሐፌ ቀደም ብዬ አቡነ ጴጥሮስን ከማዘከሬም በላይ ይግባኛቸውን «ይግባኝ ለክርስቶስን» እንደ አዝማች በየ አናቅጹ ተጠቅሜበት ነበር:: የሁኔታዎቹን መገጣጠም ከተመለከትኩኝ በኋላ የመጽሐፌን ርእስ ለመቀየር አሰብኩ:: አቡነ ጴጥሮስ ያለፈው ምዕተ ዓመት እውነተኛ ሰማዕት ተብለው ከኢትዮጵያውያኑ አልፎ በምዕራባውያኑ እንኳ ሳይቀር ከተመረጡ እኔም መጽሐፌን በእርሳቸው የመጨረሻ እስትንፋስ «ይግባኝ ለክርስቶስ» ብዬ ለመሰየም ወሰንኩ:: በዚህ ምክንያት ርእሱ ይሰየም እንጂ ጽሑፉ ግን ቀደም ብሎም በዚህ ርእስ የተዘጋጀ እስከሚመስል ድረስ ከርእሱ ጋር ተዋሕዶ አገኘሁት:: እኔም ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ተመልክቼ በዚሁ አጸናሁት:: ስለዚህ የተወደዳችሁ አንባብያን የርእሱ ምክንያት ከላይ የተገለጸው መሆኑን ተረድታችሁ የመጽሐፉን መልእክት ደግሞ በርጋታ በማንበብ እንድትገነዘቡልኝ እጋብዛለሁ:: ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የምዕተ ዓመቱ ሰማዕት ሆነው እንዲመረጡ ያስቻለው የፕሮፌሰር ስቬን ሩቨንስንን የእንጊሊዝኛ ጽሑፍም አስተርጉሜ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ አያይዤ አቅርቤላችኋለሁ::

*አባ ቀውስጦስ ሊቀ ጳጳስ*

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

በማንኛውም ጊዜና ቦታ ለሚሠራም ሆነ ለሚነገር ቁም ነገር ርእስ ወይም መግቢያ መቅድም ያስፈልገዋል። ምክንያቱም አንድ ቁም ነገር መነሻ ከሌለው መድረሻው ስለማይታወቅ ነው።

በመሆኑም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ላለው ቁም ነገር መነሻው ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን የተቀበለችበት ታሪክ ነው። የታሪኩም ጥንታዊ ስፍራ በኢየሩሳሌም ያለው የኢትዮጵያ ገዳም ዴር ሡልጣን ነው። ማንም እንደሚያውቀው ኢየሩሳሌምና ኢትዮጵያ እንዲሁም ኢትዮጵያና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የታሪካቸው ጽምረት ወይም ተዋሕዶ ጸንቶ እንዲኖር የተመሠረተው በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ነው።

በስም አጠራርም ህገረ አግዚአብሔር በመባል ኢትዮጵያና ኢየሩሳሊም አንድ ናቸው።

ይሁን እንጂ ኢየሩሳሌም ከአቤል ጀምሮ እስከ ዘካርያስ ከዘካርያስም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ንጹሕ ደም የሚፈስባት መከራ የማይለያት ሁና በመገኘቷ ሊታዘንላት የሚገባ ነው። እንዲያውም የአማኞች ሁሉ የሕይወት ምንጭ መፍለቂያ በመሆኗ ህልውናዋ ተጠብቆ እንዲኖር የማይመኝ የለም።

ምኞትም ብቻ ሳይሆን እንደነ አቤሜሌክ አድገቷን እንጂ ጥፋቷን እንዳያሳየን የምንጸልይላት ብዙዎች ነን። በሌላ መልኩ ደግሞ እግዚአብሔር በማይወሰን ቸርነቱ ላዘጋጀው ሰላምና ሕይወት ጸጋና በረከት ባለቤት እንድትሆን መርጧታል። ሆኖም የተነገረላትን ተስፋና ትንቢት አልቀበልም ማለቷ የተስፋዋ ባለቤት የሆነ እግዚአብሔርን አስቆጥቶታል። ከቁጣውም የተነሣ በዓለም ዙሪያ የምትታወቅበትን መመኪያዋ የነበረች ታቦተ ሕጉን ጽላተ ኪዳኑን ከጂ ነሥቶ /ወስዶ/ በአምነት እጆቿን ዘርግታ ለምትለምነው የተሰፋዋ ወራሽ ለሆነችው ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ አሳልፎ ሰጥቶባታል።

www.ethiopianorthodox.org



በጊዜውም ጊዜ የተነገረው ተስፋና ትንቢት የተቆጠረው ሱባዔ ቢፈጸም ኢሳይያስ በትንቢቱ «ስሙ ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።» ብሎ ኢሳይያስ 9÷6፣ ሉቃስ1÷47። ላይ የመሠከረለት ዘለዓለማዊ አምላክ፤ የሰውን ባሕርይ ተዋሕዶ ሰው ከሆነ በኋላ ሕገ መንግሥቱ ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ በሉቃ 19÷42 ላይ እንደተጻፈው «ሶበሰ ተአምሪ ዮም ሰላምኪ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ አሳወቅሽም እንጂ ብታውቂስ ሰላምሽ ዛሬ ነው ፤የይቅርታሽም ዘመን አሁን ነው፤» በማለት የሚደርስባትን ችግር ሳይሸሽግ ገልጦ እያለቀሰ በእንባ ጭምር አስጠንቅቋት ነበር።

እርሷ ግን አሁንም አለመታደል ሆነና ምክሩን ለመስማት ዠሮዋን አልሰጠችም። በእርሱም ለማመን ልቧን አላስገዛችም። እንዲያውም ይባስ ብላ «አእትቶ ወስቅሎ ከፌቴ አስወግደው፤ ከፍ፡ አድርገህም በእንጨት ላይ ስቀለው እያለች፤» በጲላጦስ ፊት ከጧት እስከ ማታ ይሙት በቃ ለማስፈረድ ስትጮህ ውላለች። ኢትዮጵያ ግን እንዲህ አይደለችም። ኢሳይያስ «እንደ በግ ሊታረድ መጣ፤» ብሎ የተናገረውን ትንቢት እንዲተረጉምላት ሐዋርያው ፊልጶስን ተማፅናለች። ከተረጐመላት በኋላ በሐዋርያት ሥራ ፰÷26 እስከ መጨረሻው ባለው መሥመር ውስጥ እንደተጻፈው «እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን አምናለሁ፤ እነሆ ውኃ ከዚህ አለ፤ በስሙ እምኜ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማነው?» በማለት ልዋል ልደር፣ ልጠራጠር ሳትል ከመቶ ሃያው ቤተሰብ ቀጥላ ከዓለም በፊት በመጀመሪያው መቶ ዓመት በ34 ዓ.ም አምና ተቀብላዋለች። እርሱም ለአመኑበት ቅርብ ነውና «ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ እኀድር እስመ ኀረይክዋ፤ መርጫታለሁና ለዘለዓለሙ ማደሪያዬ ናት፤» ብሎ አማናዊት ጽዮን ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያምን ለእናትነት በመረጠበት መለኮታዊ ጥበቡ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያንም ለአምልኮቱ መገለጫ እንድትሆን አድርጎ ከሌሎች ዓለማት ለይቶ መርጧታል።

በዚህም መሠረት ለሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰድሣ ዓመታት ሥርዓተ አምልኮትን ከምትፈጽምበት ቤተ እግዚአብሔር ሳትለይ ኖራለች። ይሁን እንጂ ከላይ በተጠቀሱት ሰፊ ዘመናት ውስጥ አቀራረቡና ስልቱ በየዓይነቱ የሆነ ፈተና በየጊዜው ሳይገጥማት አልኖረችም ። ሆኖም በእምነቷም ሆነ በህልውናዋ ላይ በተለያዩ ጊዜያት የቀረበባትን ፈተናና የተቃጣባትን ጥቃት በድል አድራጊነት እየተወጣች ክብር ምስጋና ለኃያሉ እግዚአብሔር በማለት የድኅ ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን ስትመሰክር ኖራለች። በዚህም የዓለም ሕዝብ እያደነቃት ከዚህ ደርሳለች፤ አሁን ግን ለዘመናት ጸንቶ በነበረው ሥርዓቷ ለመኖር አልቻለችም። በተለይ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የተነሣው ኢ.አማኒ. ትውልድ፦

1ኛ/ በዕድሜ ልኳ ከኖረችበት ቤተ እግዚአብሔር እንድትለይ፤ ተለይታም እንድትወጣ እያስገደዳት በመሆኑ፤

2ኛ/ ልጆቿ ሃይማኖታቸው የማይፈቅድላቸውን ዓላማ ከመከተላቸው የተነሣ በተለያየ ሃይማኖት መስል ክህደት ተከፋፍለው ለረሀብ፣ ለስደት፣ ለመከራ በመዳረጋቸው፤

3ኛ/ በኢትዮጵያነቷ ውስጥ እስከ አሁን የነበረ ዛሬም ወደፊትም ሊኖር የሚገባውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ሥርዓቷን ሊለውጡ ጨርሰም ሊያጠፉ በሚታገሉ ኃይሎች ላይ የሚፈርድባቸው ዳኛ ባለመገኘቱ የዚህ ጽሑፍ ርእስ እንደ አቡነ ጴጥሮስ የመጨረሻ አሰትንፋስ «ይግባኝ ለክርስቶስ» ሊያሰኝ ችሏል።

ይህም ለጽሑፉ መግቢያ በር ሲሆን በውስጡ ላለው ኃይለ ቃል አልፎ አልፎ እንደ አዝማች ሁኖ ተቀርጿል። ይህንንም ለመረዳት እስከ ጽሑፉ መጨረሻ መመልከት ያስፈልጋል።

ይህም በሰምንት ምዕራፍ፣ በሁለት አሰረጅና በስድሳ አንቀጽ ባጭር ባጭሩ ስለተገለጸ ፍሬ ነገሩን ማንም ሰው በቀና መንፈስ እንዲመለከተው በትሕትና አሳስባለሁ።



ከዚህም ጋራ ችግርን ለመግለጽ ቃላትን አሳክቶ የመጻፍ ችሎታ የሌለኝ መሆኔን ሳልሸሽግ አገልጻለሁ። ነገር ግን አቀናብሮ የመጻፍ ችሎታ ባይኖረኝም በመንፈሳዊ ቁጭትና በሜት ተነሣሥቼ ይህን ጽሑፍ ለማቅረብ ተገድጃለሁ። የተገደድኩበትም ምክንያት ፦

1ኛ. ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር በመባል እውቅና ያገኘችበት አምልኮተ እግዚአብሔር እንዳይጣስና በአምልኮተ ባዕድ የምእመናን ሕይወት እንዳይበላሽ

2ኛ. ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓተ ሃይማኖት እንዳይፈርስ ለመከላከል ያህል ነው።

ይህም ጥረቴ ከቤተ ክርስቲያን ጠላቶች በቀር ማንንም የሚያስከፋ እንደማይሆን አምናለሁ። ስለማምንም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ህልውና ተጠብቆ እንዲኖር የሚመኙ ሁሉ ያዝኑብኛል ብዬ አልሰጋም።

እንዲያውም የጸሎት ተባባሪ ሁነው ባሁኑ ሰዓት መላልሰው ሊጸልዩት የሚገባቸው ጸሎት «አቤቱ አምላካችን ካሉተኛና ከዐመፀኛ ትውልድ አድነን፤ ነፍሳችንንና ሥጋችንን በቸርነትህ ጠብቅ፤ ቤተክርስቲያናችንን በምስጋናና በጸሎት በቀናች ሃይማኖትም ጠብቅ፤ አምላካችን ሆይ ይቅር በለን። አባታችን ሆይ፣ በሰማይ የምትኖር፣ ወደፈተና አታግባን፣ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ፣ ለሰይጣን ከመሸነፍ ከመዋረድና ከመውደቅ አድነን፣ በየጊዜው በየሰዓቱ ሁሉ ያለድካምና የለሃኬት እናገለግልህ ዘንድ እርዳን፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን።» የሚል መሆን እንዳለበት አስገነዝባለሁ። «ሊጦን ዘሐሙስ»

www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ይግባኝ ለክርስቶስ የሚለው ቃል ተበዳይነቱ እየታወቀ በባለሥልጣኖች ዘንድ ትክክለኛ ፍትሕ አጥቶ በግፍ የተፈረደበት ሰው የነበረው ተሰፋ ሲሚጠጥ የሚያሰማው የመጨረሻ ቃል ነው:: በመሠረቱ ኃይለኛው ደካማውን እንዳያጠቃው፥ ባለ ጸጋውም ድሀውን እንዳ ይበድለው የሚከላከልለት ወይም የሚጠብቀው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ አለ:: ከእግዚአብሔር የተሰጠውም ሕግ ሰውን ሲጠብቀው የሚችለው ሰመጀመሪያ ለው ሕጉን ሲጠብቀው ነው:: ነገር ግን ሕጉን በመጠበቅ ፋንታ ሕግ አፍራሽ በመሆን አንዱ ሌላውን ሲበድለው ሕግን ለማስከበር የሚፈርድ ባለስልጣን እንዲኖር እግዚአብሔር ፈቅዷል:: ችግሩ በእግዚአብሐ.ር ፈቃድ ሥልጣን አግኝተው ሕዝብን እንዲመሩ እንዲያስተዳድሩ የተመረጡ ሰዎች ለተመረጡበት ዓላማ ብቁ ሆነው አለመገኘታቸው ነው:: ብቁ ሆነው ካለመገኘታቸውም የተነሣ ክተገፋው ይልቅ እንደ በርባን ላለው የግፍ ግፍ ለፈጸመው በማድላት እውነትን በሐሰት ሸፍነው በተገፋው ላይ ይፈርዱበታል:: ይግባኝ ብሎ ሲሔድ የበላዩ ባለሥልጣን ይግባኙን ተቀብሎ እውነቱንና ሐሰቱን ለመለየት እንዳይችል የግፍ አድራጊው ማደንዘገር /ጉቦ/ አእምሮውን እየሰተነበት ዓይኑን እያጨለመበት ግራ ተጋብቶ ልቡ እያወቀ ያንኑ በሐሰት የተፈረደበትን ከሚያጸድቅበት በቀር እውነተኛ ፍርድ አይፈርድለትም::

ከዚህም በኋላ በሰው ዳኝነት በኩል የነበረው ተስፋ ሲሚጠጥ ይግባኝ ለክርስቶስ ይላል:: በርግጥም በፍጹም እምነት ይግባኝ ለክርስቶስ የሚል ተበዳይ አይኖርም እንጂ ካለ ሳይውል ሳያድር ይግባኙን ተቀብሎ ክርስቶስ ትክክለኛውን ፍትሕ እንደሚሰጠው አይጠረጠርም::



ለምሳሌ ፋሽስት ኢጣሊያ ድንግሊቱን ኢትዮጵያን በወራሪነት በደፈራት ጊዜ ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር በማስረከብ ይግባኛቸውን ማሰማት የፈለጉት ኢትዮጵያዊው ሰማዕት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ፋሽስቱ ገና ሲያዛቸው «በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ፤ ተከታዮቼን ግን አትንኩ፤» ነበር ያሉት:: ብፁዕነታቸውን በዚህም በዕለተ ሐሙስ በአይሁድ ሲያዝ ለሮማውያን ጭፍሮች «ማንን ትፈልጋላችሁ? እኔ እንደሆንኩ አለሁላችሁ፤ እነርሱን ግን ተውዋቸው ይሒዱ» ያለውን ጌታችንን መስለውታል:: ዮሐ.18፥8::

ብፁዕነታቸው በፋሺስት እጅ ተይዘው ወደ ግራዚያኒ የቀረቡት ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. ነበር:: በወቅቱ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ፥ አቡነ ጴጥሮስን በዲፕሎማሲ ለማስፈታትና ዓለምአቀፉን ኅብረተሰብ ለማሰማት ፈልገው ግራዚያኒን «ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታሰማ በአቡነ ጴጥሮስ ላይ አንዳች ነገር ማድረግ አይገባሀም» አሉት:: እርሱ ግን ደም እንደተጠማ ውሻ ተቻኰለ:: በእነርሱ አገዛዝ እምነውና ሃይማኖታቸውን ንቀው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ክደው እነርሱን መስለው ለመኖር ቢስማሙ ብቻ ለሕይወት ተስፋ፤ የመኖር ዕድል እንዳላቸው ገለጸላቸው:: እርሳቸው ግን እውነትን ይዘው ቀጠሉ:: በዐመፅ ተመልተው በደም ተጨማልቀው በግፍ ለመግደል አሁንም አሁንም ከሚላሉቱ ባልደረቦቹ ሦስቱን በዳኝነት ሰየመ:: እርሳቸውም «ሕዝብ ቀስቅሰዋል፣ራስዎም ዐምፀዋል፣ሌሎችንም እንዲያምፁ አድርገዋል» በሚል ተከሰሰው ቀረቡ:: ከዳኞቹ አንዱም «ካህናቱም ሆኑ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች፣ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስም የኢጣሊያንን መንግሥት ገዥነት እምነው፤ እሜን ብለው ሲቀበሉ እርስዎ ለምን ሀመፁ? ለምን ብቻዎን እፈንጋጭ ሆኑ?» ሲል ራሱ በከሳሽ አንበደት ተናገራቸው:: እርሳቸውም ፍትሕ እንደሌለች ግፍም ጽድቅ መስላ እንደታየች አስተውለዋልና «አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ

www.ethiopianorthodox.org

ናቸው፤ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገዳቸው ነገር የለም። እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ። ሐላፊነት ያለብኝ ክርስቲያን አባት ነኝ። ስለዚህ ስለ አገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያኔ እቆረቆራለሁ። ከዚሁ በቀር ለአናንተ ችሎት የማቀርበው ነገር የለኝም። ለፈጣሪዬ ብቻ የምናገረውን እናገራለሁ። እኔን በመግደል እንደወሰናችሁ ሀውቃለሁ። ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጎ ተከታዮቼን ግን አትንኩ» በማለት አቤቱታቸውን ለእግዚ አብሔር አቀረቡ፤ ይግባኝ ለክርስቶስ አሉ። ግራዚያንም በስምንት ጥይት አስደብድቧቸው አልሞት ባሉ ጊዜ ከአዛዦቹ አንዱ በሦስት የሽጉጥ ጥይት ራሳቸውን በመምታት ገደላቸው። ሕዝቡ በአንድነት አለቀሰ፤ ዋይታውን አሰማ። እርሳቸው ነፍሳቸውን ሰውተው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ፍትሕ እንዲሰጥላቸው ይግባኝ ለክርስቶስ አሉ። እግዚአብሔርም የእርሳቸውንና የመሰሎቻቸውን ቁራጥ በማዕታት አባቶች ይግባኝ ተቀበለ። የሕዝቡንም ዋይታና ለቅሶ ሰማ። ስለዚህም ገጸ መዓቱንም ወደ እነርሱ /ግራዚያኒ/ አዞረ። «ገጹ ለእግዚአብሐር ኀበ እለ ይገብሩ እኩየ:- የእግዚአብሔር ፊቱ ክፉ ወደሚያደርጉት ነውና» መዝ.33÷16 ሠራዊቱ እንደ ተበተነ፤ መሪው እንደተዋረደ እንዲቀር አደረገ። በሀገራቸውም ላይ ሂትለርን አስነሥቶ ፊታቸውን ወደዚያ እንዲያዞሩ ሀገራችንም ለቅቀው እንዲወጡ አስገደዳቸው። በዚሁ ጊዜ በጄኔቫ ጉባኤ ላይ ተሰብስበው ለነበሩት ግፈኞች ዓለምን በወራሪነት ለመቀራመት ለተነሡ ነገሥታት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዘው አቤቱታ በሚያቀርቡበት ሰዓት ከማፏጨትና ከማሽሟጠጥ በቀር አቤቱታቸውን የሰማቸው አልነበረም።

እርሳቸው ግን ይህንን ግፍ ታሪክና እግዚአብሔር ይፍረደው በማለት በክረረ ኃዘን ይግባኛቸውን ለክርስቶስ አቅርበዋል። ክርስቶስም ይግባኙን ተቀብሎ ትክክለኛ ፍርድ በመፍረድ ፋሽስት ኢጣሊያን እንደ ሡናክሬም ሰራዊት በዋለበት አስቀርቶታል።



የኢትዮጵያ ባንዲራ በኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ እንድትውለበለብና ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴም ዙፋናቸውን እንዲረከቡ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ጀግና ሕዝብም የአምስቱን ዓመት የመከራ ጉዞና ተጋድሎ አያስታወስ ይግባኝ በሚ እውነተኛ ፈራጅ የሆነ ክርስቶስን ለማመስገን በቅቷል።

ይግባኝ ለክርስቶስ የሚባለው እንዲህ ስለሚጠቅም ነው። ምንም እንኳን ቃሉ ከባድ ቢሆንም በዚህ አጭር ጽሑፌ ውስጥ ላሰባሰብኩት ከባድ ነው ብዬም ላመንኩበት ነገር ርእስ አድርጌ መርጩዋለሁ። ርአስ አድርጌም በመረጥኩት ቃል ለማሰባሰብ የሞከርኩት:-

1ኛ. በደርግ ሥልጣን ይዞታችን ላይ ሲፈጸም የነበረውና አሁንም እየተፈጸመ ያለው ችግር፤

2ኛ. በዛሬይቱ ኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊት እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ላይ በተሃራሪዎች እየተፈ ጸመ ያለው ነገር ነው።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕ ዶ ቤተክርስቲያን ላይ እየተፈጸመ ያለው ነገር ከቀድሞ ጀምሮ አንድ መንግሥት አልፎ ሌላው መንግሥት በተተካ ቁጥር ሲነድ ሲበርድ የኖረ ነው። ጊዜ ሲያልፍ የሚያልፍ በመሆኑ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይሆንም።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አንድ

# የዴር ሡልጣን ጉዳይ

የዴር ሡልጣን ጉዳይ ከማንኛውም የተለየ ክብደት ያለው ነው። እንደሚታወቀው እስካሁን በተደረገው የመከራ ጉዞ እንደተረዳነው የዴር ሡልጣን ጉዳይ ፈራጅ ዳኛ ያጣ፣ ሥጋዊ ደማዊ የሆነ ምድራዊ ባለ ሥልጣን በይግባኝ ስሚነት ሊፈታው ያልቻለ ነው። ወደፊትም እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርስቶስ ከማለት በቀር በሰው በኩል ዳኝነት ይገኛል የሚል እምነት ስለሌለኝ በጽሑፌ ውስጥ ለተመልካች የነገሩን ክብደት ለመግለ ጽ ሞክሬያለሁ። ወደ ፍሬ ነገሩም ለመግባት በቅድሚያ የኢ ትዮጵያውያን ይዞታ በጎልጎታ እንዴት እንደነበረ በመጠኑ እገልጻለሁ። ዝርዝር ሁኔታውም የሚከተለው ነው።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያውያን ይዞታ በጎልጎታ መነሻው ከክርስቶስ ልደት በፊት በአራት ሺህ አምስት መቶ ዓመተ ዓለም ነው። ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን ስለክርስቶስ ፍቅር መስቀሉን ተሸክመው ከኢትዮጵያ እስከ ቀራንዮ በፍኖተ መስቀል ሲ ጓዙ በሱዳንና በግብፅ በረሐ የደረሰባቸው ጸዋትወ መከራ በእጅጉ የሚዘገንን እንደነበረ ተመሳልሶ ተነግሯል።

አሸዋ ሳይውጣቸው አውሬ ሳይበላቸው ከጎልጎታ የደረሱትም በዐፅመ ርስታቸው በዴር ሡልጣን ምክንያት በግብፃውያን ኮፕቶችና በአርመኖች በሌሎችም ቃዲዎች ሲፈጸምባቸው የነበረው ግፍ በክርስቶስ ላይ በዕለተ ዓርብ ተፈጽሞ የነበረውን መከራ መስቀል ሲ ያስታውስ የሚኖር ነው።

ዛሬም ችግሩ ሳይገታ በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ላይ የነበረውን መከራ ለዘር ተላልፎ በኛ በልጆቻቸው ላይ እየተፈጸመ ነው። ለዚህም ምክንያት የሆነው ከላይ የተጠቀሰው ዐፅመ ርስታችን ዴር ሡልጣን ነው።



ይህ ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያውያን ነው አይደለም ተብሎ አሻሚ ወይም አጠራጣሪ ነገር የሚገባበት አይደለም። የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ያረጋገጡት በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበ በትክክል የኢ ትዮጵያውያን ዐፅመ ርስት ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን እናቶቻችን እና አባቶቻችን በቅድስት እሌኒ አማካኝነት የተረከቡት ይህን ጥንታዊ ይዞታቸውን እያጠናከሩ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ላይ በየጊዜው የሚደርሰውን መከራ ሳይሰቀቁ ገዳማቸውን ሲ ያስፋፉ ኖረዋል። በአካባቢው ካሉት ታላላቅ ገዳማት አንጻርም በዴር ሡልጣን ገዳማችን የተሾሙትን ኢትዮጵያውያን አበምኔቶች እናስታውስ ከ1320 ዓ.ም. እስከ 1943 ዓ.ም. ድረስ ለዚሁ ገዳም በአስተዳዳሪነት 18 ኢትዮጵያውያን መምህራን ተሹመዋል። መዓርጉን ከፍ በማድረግ ደግሞ ከ1944 ዓ.ም እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ ዐሥራ ሁለት ሊቃነ ጳጳሳት ተሾመውበታል። እነዚህም መምህራኑ

1ኛ/ አባ ገብረክርስቶስ ፣
2ኛ/ አባ ቶማስ
3ኛ/ አባ ኒቆዲሞስ
4ኛ/ አባ ተጠምቀመድኅን
5ኛ/ አባ ፍሬክርስቶስ
6ኛ/ አባ ጊዮርጊስ
7ኛ/ አባ ብርሃነመስቀል
8ኛ/ አባ እንኪቶስ
9ኛ/ አባ ተስጋ
10ኛ/ አባ ወልደ ሰማዕት
11ኛ/ መመህር ፈቃደእግዚእ
12ኛ/ መምህር ማኅፀንተሥላሴ
13ኛ/ መምህር ይርዳው /አባ ተስፋመስቀል/
14ኛ/ መምህር ወልደ ሚካኤል
15ኛ/ መምህር ገብረ ጊዮርጊስ
16ኛ/ መምህር ክፍለ ገሪማ
17ኛ/ መምህር ገብረ ኢየሱስ
18ኛ/ መምህር ሐረገወይን ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ከሊቃነ ጳጳሳቱ፡-

1ኛ/ ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ የመጀመሪያው
2ኛ/ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ
3ኛ/ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ
4ኛ/ ብፁዕ አቡነ ማትያስ
5ኛ/ ብፁዕ አቡነ በርናባስ
6ኛ/ ብፁዕ አቡነ ሰላማ
7ኛ/ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ
8ኛ/ በድጋሚ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ
9ኛ/ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል
10ኛ/ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ
11ኛ ብፁዕ አቡነ ገሪማ
12ኛ ለሁለተኛ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ማቲያስ ናቸው::

ይህም እስከ ስምንተኛው ተራ ቁጥራ ድረስ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ሊቀ ጳጳስ ታሪክህን አስታውስ አትርሳ ብለው በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ ከገጽ 88 እስከ ገጽ 118 የሠፈረ ነው:: ወደፊትም እስከአሁን ከነበረው በተሻለ ሁኔታ የገዳሙ መንፈሳዊ አስተዳደር ሳይቋረጥ እንደሚቀጥልና ጸንቶም እንደሚኖር እምነታችን ፍፁም ነው:: ወደ ጥንተ ነገሩም ስንመለስ ኢትዮጵያውያን እናቶቻችንና አባቶቻችን ለእሥራኤል የተነገረውን ተስፋና ትንቢት ተካፋዮች ሆነው በአራት ሺህ አምስት መቶ ዓመተ ዓለም ብሉይ ኪዳንን የተቀበሉበት ታሪክ ነው::

የዚህም ምክንያት ንግሥተ ሳባ ናት:: ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት ከብዙ ገጸ በረከት ጋራ ብዙ ሠራዊት አስከትላ ወደ ኢየሩሳሌም መጥታለች::

በመጣችም ጊዜ ንጉሥ ሰሎሞን፡-

1ኛ. ተከትለዋት ለመጡት ሠራዊቶቿ፣

2ኛ. ገጸ በረከት ጭናባቸው ላመጣቻቸው ግመሎቿና ፈረሶቿ እንዲሁም በቅሎዎቿ ባጠቃላይ የጓዟ ማሳረፊያ የሚሆን



የጋዛን አካባቢ ሰጣት:: ለእርሷም ሉዓላዊ ክብሯን የሚጠብቅ ክቡር ሥፍራ መርጦ ከኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ አቅራቢያ የሚሆን ዴር ሡልጣንን ሰጧታል:: ንጉሡ በፈቃዱ ከሰጣት ሌላ እርሷ የወደደችውንና የለመነችውን ሁሉ እንደሰጣት ነገሥት ቀዳማዊ ም.10 ከቁጥር 1- 14 የሰፈረው ቃል ያስረዳል::

እርሷም የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠራ ቤተመንግሥት ሠርታበት ማረፊያ አድርጋዋለች፣ ልጇ ቀዳማዊ ምኒልክም ተረክቦታል:: ምኒልክ በ22 ዓመት ዕድሜው ወደ አባቱ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ሔዷል:: በአባቱም ቤተ መንግሥት ለሦስት ዓመታት ያህል በዕብራይስጥ ቋንቋ ሕገ መንግሥቱንና ሕገ ኦሪቱን ቢማር ከቆየ በኋላ አባቱ ሰሎሞን ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል 12ሺህ የሚሆኑ እዋቂዎች መርጦ ከተማሩትም ካህናትና ከመሳፍንት ልጆች 22 ታላላቅ ሹማምንት ሰጥቶ በአራት ሺህ አምስት መቶ አሥራ ስምንት ዓመተ ዓለም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ አድርጎ በክብር እንደሸኘው አክሊለ ብርሃን ወ/ቂርቆስ የተባሉት የቤተክርስቲያናችን ምሁር በጻፉት መጽሐፍ ገልጸውታል:: /መጽሔተ አሚን ገጽ 74/

ትውልድ አልፎ ትውልድ ቢተካ አንዳንድ ጊዜ ነገሥታቱ አንዳንድ ጊዜም ወኪሎቻቸው በኦሪቱ ሥርዓት መሠረት በዓመት በዓመት የእግዚአብሔርን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም በሚመጡበት ጊዜ የሚያርፉበት ቤተ መንግሥታቸው ዴር ሡልጣን ነው:: ነገሥታቱም ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ልደተ ክርስቶስ ስድሣ ሰባት ናቸው:: ዘመኑም ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሁለት ዘመን ነው:: ይህም ቃል ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ላይ የሰፈረ ነው::

www.ethiopianorthodox.org

# ከልደተ ክርስቶስ በኋላ

ከልደተ ክርስቶስም በኋላ ዐራት ነገሥታት በአረቱ ሥርዓት መሠረት በኢየሩሳሌም በዓል ለማክበር እየመጡ በዚሁ ቦታ ሲ ያርፉበት ኖረዋል:: ዐራተኛይቱም ንግሥት ሕንደኬ ናት:: የንግሥት ሕንደኬ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያውያን ሐዲስ ልደትን የተቀበሉበት ብሉይ ኪዳንን በሐዲስ ኪዳን የተረጐሙበት ዘመን ነው::

አባቶቻችን ከመቶ ሃያው ቤተሰብ ቀጥሎ ከዓለም ክርስቲያኖች በፊት ክርስትናውን ተቀብለዋል ስንል አብነት አድርገን ለምስክርነት የምንጠቅሰው የንግሥት ሕንደኬን ጃንደረባ ነው:: የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ እንደተለመደው የአረቱን በዓል ለማክበር ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣ በኋላ በጋዛ የነበረውን የኢትዮጵያውያንን ይዞታ ጎብኝቶ በሰረገላ ሆኖ ሲመለስ የኢ ሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር:: መንፈስ ቅዱስም ፊልጶስን «ሒድ፤ ይህን ሰረገላ ተከተለው፤ » አለው:: ፊልጶስም ፈጥኖ ደርሶ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማው:: ፊልጶስም «በውኑ የምታነበውን ታውቃለህን?» አለው:: ጃንደረባውም «ያስተማረኝ ሳይኖር በምን አውቃለሁ» አለው:: ወደ ሰረገላውም ወጥቶ አብሮት ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመነው፤ ጃንደረባውም ወደፊልጶስ ተመልሶ «ነቢዩ ስለማን እንዲህ ይላል? ስለራሱ ነውን? ወይስ ስለሌላ እባክህ ንገረኝ፤» አለው:: ፊልጶስም አንደበቱን ከፈተ:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም በዚያው ባለው መጽሐፍ ያስተምረው ጀመረ:: ሲሔዱም ከውኃ ደረሱ፤ ጃንደረባውም «ውኃ ይኸው መጠመቅን ማን ይከለክለኛል?» አለው:: ፊልጶስም «በፍጹም ልብህ ልታምን ይገባሃል» አለው:: ጃንደረባውም መልሶ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚ አብሔር ልጅ እንደሆነ አኔ አምናለሁ፤» አለው:: ሰረገላውንም እንዲያቆሙ አዘዘ፤ ሰረገላውንም አቆሙ:: ፊልጶስና ጃንደረባው



ባንድነት ወደ ውኃው ወረዱ፤ አጠመቀውም:: ከውኃውም ከወጡ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ፊልጶስን ነጥቆ ወሰደው፤ ዣንደ ረባውም ከዚያ ወዲያ አላየውም:: ደስ እያለው ወደ ሀገሩ ገባ በማለት ወንጌላዊ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 26 እስከ 40 በሰፊው ዘርዝሮ ጽፏል:: እንግዲህ ከዚህ በላይ ባጭሩ የተጠቀሰው ታሪክ የሚያስገነዝበን ለአባቶቻችን ዴር ሡልጣን ዐፅ መ ርስታቸው ጋዛም በይዞታቸው የቆየና በሐዋርያትም ዘመን ክርስትናን የተቀበሉበት ቦታቸው መሆኑን ነው::

ይሁን እንጂ ምንም እንኳ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበ በመሆኑ ማንም ሊፍቀው ባይችልም አባቶቻችን በተጠ መቁበት ፈሳሽ ውኃ አጠገብ ታሪካቸውን የሚያስታውስ አንድ ቤተክርስቲያን አለመሠራቱ፤ ያም ባይቻል አንድ የታሪክ ማስታወሻ መንፈሳዊ ሐውልት አለመኖሩ በጅጉ የሚያሳዝን ነው:: እንደሚታወቀው ጥጦስና እስባስያኖስ ኢየሩሳሌምን እስኪያጠፏት ድረስ በጋዛም ሆነ በጎልጎታና በዴር ሡልጣን የነበረን ይዞታ ሳይሸራረፍ ወይም የኔነው ይገባኛል የሚል ተከራካሪና ተፎካካሪ ሳይኖርብን ሙሉ በሙሉ በአባቶቻችንና በእናቶቻችን እጅ እንደነበረ ታሪክ የሚመሰክረው ነው:: ወረራው በንጥጦስ ከተጀመረ በኋላ ግን የተለያዩ ዐላውያን ነገሥታት እየተፈራረቁ ኢየሩሳሌምን አፈራርሰዋታል:: ያ ዘመን ቅዱሳን ሐዋርያት በየሐ ዱበት እንደበግ የሚታረዱበት፤ ኢየሩሳሌም በደም የተጥለቀለቀችበት ክፉ ዘመን በመሆኑ፤ በክርስቶስ ደም የከበረ ድውይ ፈዋሽ÷ ሙት አስነሽ የሆነ የክርስቲያኖች መመኪያቸውና የሕይወት አርማቸው ቅዱስ መስቀልም በጠላቶች በአይሁድ እጅ የተቀበረበት የጨለማ ዘመን ነበር::

በተከታታይም የነገሡት ነገሥታት እግዚአብሔርን የማይፈሩ ለሰው የማያዝኑና የማይራሩ፣ ጨካኞች ስለነበሩ:: የክርስቲያኖች ነጻነታቸው ተገፎ እንደ ሽንኩርት የሚላጡበት፣ እንደ ሻማ የሚቀልጡበት፣ ከአንበሳ ጋር የሚታገሉበት የመከራ

www.ethiopianorthodox.org

ዘመን ነበር። ዘመኑም ዘመነ ስማዕታት ተብሏል። ልሁል እግዚ አብሔር በጻድቁ ንጉሥ በቆስጠንጢኖስ አማካይነት መከራውን እስኪገታው ድረስ በዚያ ክፉ ዘመን በኢየሩሳሌም ርስት አለኝ፣ ይህ የኔ ይዞታ ነው ብሎ ሊጠይቅ የቻለ አንድም ክርስቲያን አልነበረም። ነገር ግን ጨለማን በብርሃን፣ ሐዘንን በደስታ የመለወጥ ሥልጣን ያለው ልዑል እግዚአብሔር ያን መከራ አሳልፎ ራትዕ ንጉሥ መፍቀሬ ሃይማኖት /ቅን ሃይማኖትን የሚወድ/ ቆስጠንጢኖስን አነገሠ። ጻድቁ ቆስጠንጢኖስ በእግዚ አብሔር ቅዱስ ፈቃድ ከነገሠ በኋላ መከራው ሲገታ እናቱ ቅድስት እሌኒ የተቀበረ የክርስቶስን መስቀል ለማውጣት ከእግዚ አብሔር ስለተፈቀደላት በ327 ዓመተ ምሕረት ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛለች። ጎልጎታም በደረሰች ጊዜ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ አጥታው ብዙ ብትቸገርም አመጣጧ በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለነበረ ተስውሯት አልቀረም። በተለያየ ምልክት የተቀበረበትን ቦታ አግኝታ፣ ለመንፈቅ ያህል ተራራውን አስቆፍራ ከተቀበረበት መስቀሉን አውጥታ በኢየሩሳሌም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርታለች። አሠርታም ስትፈጽም ለክርስቲያኖች በጎልጎታ ርስት ማካፈል ጀምራለች።

ርስት በምታካፍልበት ጊዜ በኢትዮጵያ የነገሡት ነገሥታት አብርሃ አጽብሐ ነበሩ። እነዚህም ቅዱሳን ነገሥታት መምህራቸው ቅዱስ ፍሬምናጦስን ወደ እስክንድርያ ልከው በእግዚአብሔር ፈቃድ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ አንብሮተ ለድ ጳጳስ ሆኖ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተብሎ ተሹሞላቸዋል። በቅዱስ ፍሬምናጦስም የወንጌል ትምህርት በመላ ኢትዮጵያ ተሰብኮላቸው የሃይማኖታቸውን ምስጢር ጠንቅቀው ከተረዱ በኋላ በአራተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት አጋማሽ ላይ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው የኢትዮጵያ ብሔ ራዊ ሃይማኖት ሆኖ ታውጇል።

በዚህም ጽኑ ሃይማኖታቸው እግዚአብሔርን እያገለገሉ ሲ



ኖሩ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የምእመናን ነጻነት ተረጋገጠ። የቅድስት እሌኒም በጎ ሥራ ጎልቶ ሲነገር በመስማታቸው «እስከዛሬ ድረስ ዝም ያልነው የመከራ ዘመን በመሆኑ ነው። አሁን ልዑል እግዚአብሔር በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አማካይነት በክርስቲያኖች ላይ የነበረው መከራ እንዲገታ ካደረገ ክርስቲያኖችም በጎልጎታ ርስት የሚካፈሉ ከሆነ፥ እኛም ክርስቲያኖች በመሆናችን በጎልጎታ ይዞታ ሊኖረን ይገባል። በተለይም ከንግሥተ ሳባ ተያይዞ የመጣ ዴርሡልጣን የተባለው ዐፅጽመ ርስታችን ነው። ይህም በታሪክ የተረጋገጠ እውነተኛ ርስታችን ነው። በመሆኑም ሊሰጠን ይገባል» ሲሉ ለንጉሥ ቆስጠንጢኖስና ለንግሥት እሌኒ የይግባናል ጥያቄ አቀረቡ። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስና ንግሥት እሌኒም ጥያቄያቸውን ተቀብለው በጎልጎታ ይዞታ እንዲኖራቸው አድርገዋል። ዴር ሡልጣንንም በዐፅመ ርስትነት አረጋግጠው ሰጥተዋቸዋል። ከሰጧቸውም በኋላ ለ300 ዘመናት ያህል እስላሞች እስከ ነገሡበት ዘመን ድረስ ኢትዮጵያውያን በሰላም ይኖሩበት ነበር በማለት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ «ታሪክህን አስታውስ አትርሳ» በሚል ርእስ ስለ ዴር ሡልጣን በጻፉት መጽሐፍ በምዕራፍ 1 በገ ጽ 7 ላይ ገልጸውታል። ከዚያም በኋላ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት በተለያየ ጊዜ መከራ ባይለያቸውም ከነ ዓጼ ካሌብ ጀምሮ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ደጋግ ስለነበሩ ዘውዳቸውን ሳይቀር ለዴር ሡልጣን ገዳማቸው እየላኩ መነኮሳቱን ይደግፏቸው ስለነበር መብት የሚያሳጣ የከፋ ችግር አልገጠማቸውም። ከጎልጎታ ሳይወጡ የዴር ሡልጣን ይዞታቸውን እያጠናከሩ በየዓመቱ የትንሣኤን መብራት መጀመሪያ የሚያበራው የኢ ትዮጵያ ገዳማት አበምኔት ነበር። ይህም ኢትዮጵያውያን በጎልጎታ የነበራቸው መብት ከፍተኛ እንደነበረ የሚያስረዳ ነው።

ገዳማቸውን በዙሪያው አስፋፍተው እስከ 16ኛውና እስከ 17ኛው መቶ ክፍለ መዘን ድረስ በጎልጎታ ይኖሩ ነበረ። በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከሕዝበ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኑም ለእድሳት ገንዘብ ተልከላቸው በቅዱሳት መካናት በጎልጎታ የነበሯቸውን መቅደሶችና ገዳሞቻቸውን እንዲታደሱ አድርገዋል። ይህንንም የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ የሰነድ ማስረጃዎች ብለው በጻፉት መጽሐፋቸው ገልጸውታል። አንደኛ ማስረጃ ገጽ 15፣ ሁለተኛ ማስረጃ ገጽ 17 ብለው በጻፉት ላይ «በኢትዮጵያዊው አባ ሒኒስ ትጋት በ150ሀ ዓ.ም መታደስ ጀመረ። የማደሻውም ገንዘብ ከግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እና ከኢትዮጵያውያን ምእመናን ዘንድ የተላከ ነው፤» ይላል።

ኢትዮጵያውያን ከግራኝ ጦርነት ወዲህ የቱርክ መንግሥት እንደጠላት አይቶ ቸል አላቸው። ከኢትዮጵያም ርዳታ ተቋረጠባቸው። በዚህ ምክንያት እጅግ በመቸገራቸው በጎልጎታ ውስጥ የነበራቸውን የርስት መብት ለአርመኖች ለቀው ዴር ሡልጣን ከሚባለው ከጎልጎታ ቤተክርስቲያን ጋር በምሥራቃዊ ክፍል በኩል ገጥሞ በሚገኘው ገዳማቸው ብቻ ተወስነው ሰፈሩ። ከዚህ በኋላ በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው የኢትዮጵያ ንብረት ሁሉ ለአርመኖች ተለቀ ነበር። የግሪክ ፓትርያርክ የኢትዮጵያ ንብረት በአርመን እጅ መውደቅ አይጠገባውም ሲል ተቃውሞ በሁለቱ ማኅበሮች በግሪክና በአርመን መካከል በኢትዮጵያ ንብረት ምክንያት በየጊዜው ይፈጠር የነበረው ትግል ልክ እንዳልነበረው ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ አስረድተዋል።

እንግዲህ ታሪኩን ስንመረምር ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ባለነው ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ላይ ተከታታይ ጥቃት ሲፈጸም የኖረ ለመሆኑ ማንም ሰው ሊረዳው ይገባል።

ግብፃውያን በአባቶቻችን ላይ በየጊዜው ያደረሱትን ጥቃት እናስታውስ ካልን ከ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የፈጸሙባቸው ለውር ደባ ለሰሚው የሚያስደንቅ ነው። እንኳን ከክርስቲያን ምንም ከማያውቅ አረመኔ የማይጠበቅ አሳዛኝ ድርጊት ሆኖ እናገኘዋለን። በመሠረቱ እግዚአብሔር አድልዎ የሌለበት አምላክ ነው።



# ምዕራፍ ሁለት

## ግብፃውያን በአባቶቻችን ላይ

ሰው ሆኖ በሞቱ ሞትን አሸንፎ በትንሣኤው መቃብርን ድል ነሥቶ ከተነሣ በኋላ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ለሐዋርያትና ለሰብአ አርድዕት አስተምሮ፣ ከቁልፍ ያዥ በረኛነት እስከ ፓትርያርክነት ያለውን መዓርገ ክህነት ሰጥቷቸዋል። ካረገ በኋላም ሐዋርያትና ሰብአ አርድዕት እስከ ጽንፈ ምድር ዞረው ወንጌልን በማስተማር ጳጳሳትን ሊቃነ ጳጳሳትን ሾመዋል። ሊቃነ ጳጳሳትም፣ ጳጳሳትን፣ ኤጲስ ቆጶሳትን እየሾሙ ወንጌል እየሰፋች ምእመናን እየበዙ እስከ ዓለም ዳርቻ አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል። ግብፃውያን ግን መዓርገ ጵጵስና ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይተላለፍ እግዚአብሔር የከለከለ አስመስለው «ወሰብአ ኢትዮጵያስ ኢይሲሙ ሊቀ እማአምራኒሆሙ፣ የኢትዮጵያ ሰዎች ከሊቃውንቶቻቸው ጵጵስና እንዳይሾሙ የተከለከለ ነው» በማለት ሥርዋጽ አስገብተው፤ ክልክለው ኑረዋል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ማንኛውም ሐዋርያ ባስተማረበት ሀገር ውስጥ ካስተማራቸው የሀገር ተወላጆች ምሁራን መካከል በአግሩ የሚተካ ኤጲስ ቆጶስ መርጦ ላስተማራቸው ምእመናን ሾሞላቸው ይሔዳል እንጂ የራሴ ተወላጅ ካልሆነ አልሾምላችሁም ብሎ ምእመናንን ያሳዘነ አንድም ሐዋርያ የለም።

ለዚህም ሌላ ምስክር አያሻም። ምክንያቱም ቅዱስ ማርቆስ እስክንድርያ ገብቶ ግብፃውያንን አስተምሯል። በስኤል ገመድ አስረውም፣ በክብት እያስጎተቱ ግፈኞች ግብፃውያን እስኪ ገድሉት ድረስ ላስተማራቸው ክርስቲያኖች የራሳቸው ተወላጅ የሆነ አንያኑን መርጦ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾመላቸው እንጂ በኢ

www.ethiopianorthodox.org

የሩሳሌም ካሉ ዘመዶቼ ካልሾምኳችሁ ለናንተ ወገን ጵጵስና አይገባም አላለም::

አባቶቻችንም ይህንን ተረድተው ከተወላጆቻቸው ከኢ ትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙላቸው ሳይጠይቁ ያለፉበት ጊዜ የለም:: ግብፃውያን ግን ገጸ በረከት ከመቀበል በቀር ሌላ ጎሊና አልነበራቸውም:: ያላስተማሩትን÷ ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን በመቀበል የሚቀድማቸውን÷ ከነሱ በፊት ክርስቲያን የሆነውን ምሁር ሕዝብ እንዳላዋቂ አድርገው «ኢትዮጵያውያን አንኳን ጵጵስና ተሾመው እንሾም ብለው በመመኘታቸው እንኳን እግዚ አብሔር መዓት አመጣባቸው::» በማለት የድፍረት ድፍረት በእግዚአብሔር ስም አሳበው ለጕሮ የከበደ የውሸት ታሪክ ጽፈዋል::

ይህንንም የውሸት ታሪክ እውነተኛ ታሪክ አስመስለን በመጽሐፋችን ውስጥ ጠርዘን እያነበብነው እንገኛለን:: ለማስገንዘብም ያህል ይህንኑ አሳፋሪ ታሪክ እንደሚከተለው ጽፌዋለሁ:: ዘመኑ እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር 1123 ዓ.ም እንደ አውሮፖ አቆጣጠር ደግሞ በ1131 ዓ.ም ነው:: በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ የነገሠው ጻድቁ ንጉሥ ሐርቤ ነበር:: በእስክንድርያ የተሾመው ፓትርያርክ አባ ገብርኤል የሚባል ሲ ሆን በኢትዮጵያ የተሾመው ጳጳስ ደግሞ አባ ሚካኤል ይባል ነበር:: የኢትዮጵያው ንጉሥ ሐርቤ ለኢትዮጵያ አገሮች ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾም ዘንድ አባ ሚካኤልን አዘዘው:: አባ ሚካኤልም ያለ ሊቀ ጳጳሳቱ ትእዛዝ ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳትን መሾም አልችልም ብሎ ለንጉሡ መለሰለት::

ስለዚህ የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ አባ ገብርኤልና ወደ ግብፅ ንጉሥ እየለመነ እና እየማለደ ንጉሡ አባ ገብርኤልን



እንዲያዝለት አባ ገብርኤልም ለአባ ሚካኤል እንዲፈቅድለትና በተጨማሪ ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳትን አስቀድሞ በሾሟቸው ላይ እንዲሾም መልእክት ላከ:: የግብፅ ንጉሥም የኢትዮጵያን ንጉሥ ፈቃዱን ሁሉ ይፈጽምለት ዘንድ አባ ሚካኤልን እንዲፈቅድለት አባ ገብርኤልን አዘዘው:: ከዚህ በኋላ መኳንንቱ ወደ ንጉሥ ዘንድ ገብተው እንዲህ አሉት:: በኢትዮጵያ ሀገር ኤጲስ ቆጶሳት ቢበዙ ደፍረው ጳጳሳትን ይሾማሉ:: ከዚህ በኋላ ከቶ ወደኛ አይመጡም:: ንጉሡም ይህንን በሰማ ጊዜ ይህን አባት አባ ገብርኤልን እንዲህ ብሎ አዘዘው:: ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ሀገር ኤጲስ ቆጶሳትን እንዳይሾም ለኢትዮጵያ ንጉሥ የውግዘት ደብዳቤ ላክ አለው::

ሊቀ ጳጳሳቱም የግብፅ ንጉሥ እንዳዘዘው ላከ፤ የውግዘት ደብዳቤውም ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ደርሳ በተነበበች ጊዜ የንጉሥ እዳራሽ ተቃጠለ:: በኢትዮጵያ አገርም ረሀብና ቸነፈር ሆነ፣ ዝናብም ተከለከለ፤ ችግርም ሆነ፤ የኢትዮጵያ ንጉሥ የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ ተላልፏልና:: ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ተመልሶ ተጸጸተ:: ወደ ግብፅ ንጉሥም ይህንን አባት አባ ገብርኤልን እንዲያዝለትና ከውግዘቱ ይፈታው ዘንድ እየለመነ መልእክት ላከ:: የግብፅ ንጉሥም አዘዘለት፤ አባ ገብርኤልም የመፍቻና የቡራኬ ደብዳቤ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እየባረከ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ላከ:: ይቺ የበረከት ደብዳቤ ወደ ኢትዮጵያ አገር ደርሳ በተነበበች ጊዜ እግዚአብሔር መዓቱን ከላያቸው አርቆ ይቅርታውን ሰጣቸው:: ዝናብም ወረደላቸው፤ ቸነፈሩም ተወግዶ ታላቅ ደስታ ሆነ ይላል::

ይህም ሚያዝያ 10 ቀን በሚነበበው ስንክሳር ውስጥ ይገኛል:: በጣፋጭ ምግብ ላይ አጸያፊ ነገር ሲወድቅበት ጣፋጩን ምግብ እንደሚያስጠላው ሁሉ ይህም የፈጠራ ታሪክ በቅዱሳን ታሪክ ውስጥ ተለጥፎ ሲነበብ የቅዱሳንን እውነተኛ ታሪክ የሚያጠራጥር እንዳይሆን ያሰጋል:: እንግዲህ ከዚህ በላይ የተገለ ጸውን ታሪክ አስተዋይ ልቡና ያለው ሰው ሊመዝነው ይገባል::

www.ethiopianorthodox.org

ንጉሥ ሐርቤ ለኢትዮጵያውያን ጵጵስና በመመኘቱ እግዚአብሔር ተቆጥቶ አዳራሹን አቃጠለበት፤ ዝናብም እንዳይዘንብ ከለከለበት፤ ሕዝቡንም በርሀብ በቸነፈር ቀጣበት፤ አባ ገብርኤል በእስላሙ ንጉሥ አማላጅነት ንጉሥ ሐርቤን ከውግዘቱ ቢፈታው የቡራኬ ደብዳቤውንም ልኮ በኢትዮጵያ ቢነበብ ዝናም ዘነበለት፣ ቸነፈሩም ተወገደለት፣ ሕዝቡንም ደስ አለው፤ በማለት በእግዚአብሔር ስም አስታኮ የተቀደሰውን ሕዝብ እግዚአብሔር እንደጠላው አስመስሎ የሐሰት ታሪክ በተቀደሰው ሕዝብ ላይ በድፍረት መጻፍ ሥርየት የሌለው ኃጢአት ነው። እንግዲህ ይህ ታሪክ ግብፃውያንም ይጻፉት፣ ደብተሮችም ይለጥፉት፣ በታሪኩ መግቢያ ላይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማን እንደጻፈው ያልታወቀ ጽሑፍ እናገኛለን የሚል ስላለ በተንኮል የተጻፈ ታሪክ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

ይህንንም ታሪክ እውነተኛ ነው የሚል ካለ፤ ንጉሥ ሐርቤ ለኢትዮጵያውያን ጵጵስና በመመኘቱ ብቻ በመቅሰፍት የተቀጣ ከሆነ፤ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ከብዙ ጥረት በኋላ የንጉሥ ሐርቤን ሐሳብ ወደ ተግባር ለውጠው።

1ኛ/ ግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም አራት ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን ጵጵስና አሹመዋል።

2ኛ/ የግብፅን ፓትርያርክ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ አስመጥተው እጨጌ ገብረመንፈስ ቅዱስን ሳዊሮስ አሰኝተው ጥር 1 ቀን 1922 ዓ.ም አሹመዋል።

3ኛ/ ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም አምስት ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን ጵጵስና አሹመዋል።

4ኛ/ ጵጵስናውን ወደ ሊቀ ጵጵስና ክፍ አድርገው ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ አሰኝተው አሹመዋቸዋል።

5ኛ/ የመጨረሻውን መዓርገ ክህነት በማስገኘት ሰኔ 21

www.ethiopianorthodox.org



ቀን 1951 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስን ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አሰኝተው አሹመዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ቤተ መንግሥት አልተቃጠለም፤ ዝናመ ምሕረትም ከኢትዮጵያ አልተቋረጠም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም በርሀብ በቸነፈር አልተቀጣም። ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና ከደስታ በስተቀር በዚህ ሰበብ ክፉ ነገር አላየንም። እንዲህም ከሆነ በንጉሥ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት በጵጵስና ጥያቄ ምክንያት መቅሰፍት ታዞ ነበር የተባለውን ታሪክ ማንም ሊቀበለው የማይገባ የመጨረሻ ውሸት ነው። የአባቶቻችንን ውጤታማ ድካም ከንቱ አድርጎ ለማስቀረት የተጠነሰሰ የጠላት ሴራ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተፈጸመ ሥውር ደባ ነው። ይህም ታሪክ እስከ ቅርብ ጊዜ በግእዝ ተጽፎ በብራና ተሸፍኖ ስለሚኖር ተመልካች አልነበረውም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ምሁሩ ሊቀ መዘምራን ሳሙኤል ማርያም ወልደ ኢየሱስ ግእዙን ወደ አማርኛ ተርጉመው አቅርበውታል። በዚህ መጽሐፍ ማን እንደ ጻፈው ያልታወቀ ጽሑፍ እናገኛለን በማለት ይህን ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚጎዳ ጠላት የጻፈውን ታሪክ መታረም እንደሚገባው አመልክተው ሳለ ለምን ሳይታረም ታተሞ ለምእመናን እንደተሰራጨ አልገባኝም። ወይም የሊቃውንቱ ጉባዔ አይቶ መርምሮና አርሞ ያሳለፈው የታመነ ታሪክ ነው ከተባለም ዛሬም እንደቀድሞው በኢትዮጵያ ላይ መቅሰፍት ያስጋል። በአባቶቻችን ጸሎት፥ በእግዚአብሔር ቸርነት፥ በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ያላሰለሰ ጥረት ተገኝቶ የነበረውን የጵጵስና መዓርግና ፓትርክናም ያለውድ በግድ ለግብፃውያን ማስረከብ ሊኖርብን ነው። እንደኔ አመለካከት ግን ይህ ጠላት በመጽሐፋችን ውስጥ የቀበረው የቤተክርስቲያናችንን ሕይወት የሚጎዳ ፈንጅ ነው። ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ሊመረምረውና ልጆቻችንንም ከማጠራጠሩ በፊት ሊያመክነው የሚገባ ነው። እንደሚታወቀው ግብፃውያን ኮፕቶች ቀድሞም ሆነ ዛሬ ምኞታቸው ኢትዮጵያዊት እናት ቤተክርስቲያናችንን አካለ ጎደሎ አድርገው እስክንድርያ እናታችን እያለች በመማጸን የእስክንደርያ ለማኝ ጥገኛ ሆና

እንድትኖር ነው። ይህም ከንቱ ሐሳባቸው ወይም ሕልማቸው በእግዚአብሔር ቸርነት በአባቶቻችን ጸሎት በግርማዊ ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለሥላሴ ጥረት ቅዠት ሆኖ ቀርቷል። ይሁን እንጂ የጦር ሜዳቸው ዴር ሡልጣን ገዳማችን እስከ አልተከለከለባቸው ድረስ እኛን ለማጥቃት ዕረፍት እንደማይኖራቸው በሚገባ እናውቃለን። እስላሞች በመንግሥት ከተጠናከሩበት ጊዜ ጀምሮ በዴር ሡልጣን ገዳማችን ላይ ከግብፃውያን ሲቃጣ የኖረው ጥቃት በየጊዜው በኢትዮጵያ የነገሡትን ነገሥታትና ሕዝቡን ያስለቸ እስካሁን ምድራዊ ዳኛ ያልተገኘለት ወደፊትም እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርስቶስ ከሚያሰኝ በቀር የፍርዱ ፍጻሜ በዚህ ጊዜ ይሆናል የማይባል ነው። ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ታሪክ በንመለከት ዴር ሡልጣን ከእጃቸው እንዳይወጣ በየጊዜው በኢትዮጵያ የነገሡት ነገሥታትና ሕዝቡ ቦታ ጠባቂ የሆኑትን የዴር ሡልጣንን መነኮሳት ጩኸት በስሙ ቁጥር በየዘመናቸው ለነበሩት ባለሥልጣኖች ያልጻፉት ጽሑፍ ያላደረጉት ትግል የለም። በተለይ መነኮሳቱ እንደ እሥረኛ በር እየተዘጋባቸው ለዘመናት ሲሰቃዩ ከኖሩ በኋላ ዳግማዊ ሀዬ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ደጃች መሸሻ ወርቄን አስከተርከ ድረስ ልከው የቦታ ባለቤትነት ማስረጃ አሰባስበው በማዘጋጀት የዴር ሡልጣን ምሥራቃዊውን በር በ1895ዓ.ም አስከፍተው ለመነኮሳቱ አዲስ ሕይወት ዘርተውባቸዋል። ከዚያም በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለሥላሴ የዴር ሡልጣን ጉዳይ ሲያስጨንቅ የኖረው አባታቸውን አፄ ምኒልክን ብቻ ሳይሆን ብዙ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ሲቸገሩበት ኖረው ውጤት ሳያገኙበት የቀረ፡ በነ ሀዬ ነአኩቶ ለአብ፣ በነ ሀዬ ዳዊት፣ በነ ራስ ዓሊ፣ በነ ደጃች ውቤ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ሲከፈልበት የኖረ ሥር የሰደደ ችግር መሆኑን ጠንቅቀው የሚያውቁ፤ አርቆ ተመልካች በመሆናቸው ችግሩን በውይይት ለመፍታት ገና በአልጋ ወራሽነታቸው ጀምሮ ያደረጉት ጥረት ከፍተኛ ነበር።



ኢየሩሳሌም ድረስ መጥተው መነኮሳቱን አነጋግረዋቸዋል። በወቅቱ የነበሩት አበምኔት መምህር ይርዳውና መነኮሳቱም አቤቱታ አቅርበውላቸዋል። ያን ጊዜ የግብፁ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ በኢየሩሳሌም የተሾሙት ግብጻዊ ጳጳስ ደግሞ አቡነ ጢሞቴዎስ ይባሉ ነበር።

አልጋ ወራሹም ኢትዮጵያውያን መነኮሳትና አበምኔቱ ያቀረቡላቸውን አቤቱታ ካዳመጡ በኋላ በኢየሩሳሌም የተሾሙት ግብፃዊ ጳጳስ ታመው ወደ ሀገራቸው ስለሄዱ ሳያገኟቸው በመቅረታቸው አዝነው ሚያዝያ 18 ቀን 1916 ዓ.ም ማሳሰቢያ ደብዳቤ ጽፈውላቸዋል። በሳምንቱም ሚያዝያ 26 ቀን 1916 ዓ.ም ወደ ካይሮ ሄደው ለፓትርያርኩ ከአንድ እስከ ዘጠኝ ተራ ቁጥር የያዘ ከፍተኛ የሆነ ሽልማት ሸልመዋቸዋል። ለግብፅ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም ለትምህርት ቤቶች የገንዘብ ስጦታ አበርክተው ችግሩን በውይይት ለመፍታት ግብፃውያኑ አመቻችተው እንዲቆዩዋቸው አደራ ጭምር አሳስበው ከሀገራቸው የመጡበትን መንግሥታዊ ጉዳይ ለማከናወን ወደ አውሮፓ ሄደዋል።

ከዚያ እንደተመለሱ ግን የኮፕት ማኅበር ቅን ሐሳብ ይዞ አልጠበቃቸውም። ችግሩን በውይይት ለመፍታት ፈቃደኛ ሆኖ አላገኙትም። በዚህም አዝነው ከሔዱ በኋላ፡-

1ኛ. ለግብፃውያኑ የጻፉትን ማሳሰቢያ፣

2ኛ. የኢትዮጵያ መነኮሳት ያቀረቡትን ማመልከቻ፣

3ኛ. ለግብፁ ፓትርያርክ የሰጧቸውን የሽልማት ዓይነት ዘርዝረው ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ «ኢየሩሳሌምን እወቁ!» በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፍ ከገጽ 29 እስከ ገጽ 32 በስፋው ገልጸውታል። ይህም የሚያስረዳው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ገና በአልጋወራሽነታቸው ለዴር ሡልጣን ገዳማችን ያደረጉትን ከፍተኛ ጥረት ነው።

ከዚህም ሌላ ችግርን በክርክርና በጦርነት ከመፍታት በፍቅርና በስላማዊ ውይይት መፍታት የሚበልጥ መሆኑን በጥልቀት የሚያውቁ ብልሀ አዋቂ እግዚአብሔርን ፈሪ አርቆ አስተዋይ እንደነበሩ የሚያስረዳ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ግብፃውያን ኮፕቶች ክርስቶስ ለሞተለት ፍቅር ደንታ የሌላቸው

www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፈርያን ልባቸው በትዕቢት የደነደነ ክርስቲያን ነን ሲሉ ክርስቲያናዊ ፍቅር የሌላቸው መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግን ተከራክረው የሚረቱበት ብዙ በቂ ማስረጃ እያላቸው፣ እስከ ካይሮ ድረስ ተጉዘው ዘጠኝ ዓይነት የተለያየ የወርቅ ሽልማት እስከማበርከት ደርሰዋል:: ችግሩንም በውይይት ለመፍታት የጣሩት እንደኛ «ኅሥሳ ለሰላም ወዴግና ሰላምን ፈልጋት ተከተላትም» ብሎ ነቢዩ ዳዊት የተናገረውን ለመፈጸም ነው::

ሁለተኛ የዛሬዎቹም ግብጻውያን አባቶች እንደቀድሞዎቹ እንደነ ቅዱስ አትናቴዎስ እንደነ ቅዱስ ቄርሎስ ቅድስና ያላቸው ለመንፈሳዊ ፍቅር የሚሳሱ የክርስቲያን አጋሮች መስለዋቸው ነው:: ነገር ግን ነቢዩ ዳዊት «ከጠማማ ጋር የዋለ ጠማማ ነው» እንዳለ ንጹሕ ደም እፍሰው መንግሥተ ሰማያት እንገባለን ከሚሉ አክራሪዎች ጋር በመዋላቸውና በመጐራበታቸው ወይም በነዚያ ጠባይ በመበከላቸው ጠባያቸው ተለውጦ ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን አሳደው ለመምታት ጨርሰም ለማጥፋት ሳንጃቸውን እንደወደሩ፣ ድንጋያቸውን እንደጠረወሩ ይኖራሉ:: ይህም የሆነበት ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕ 16 ቁ 1 ላይ የተናገረው ይፈጸም ዘንድ ነው፣ ቃሉም፡ «እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ:: ከምኩራባቸው ያወጧችኋል፣ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል::» የሚል ነው::

የአሁኖቹ ግብፃውያን ይህ ዓይነቱ ምኞት ያላቸው ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም:: ይህ ዓይነቱ ምኞት ባይኖራቸው ኖሮ 1600 ዘመናት ወርቅ በሳጥን የዝሆን ጥርስ በግመል እየጫኑን ያበረከትንላቸው ገጸ በረከት ከግምጃቤታቸው ሳያልቅ እኛን ለማጥፋት ጧት ማታ ሰይፍ ባልመዘዙብንም ነበር:: በየጊዜው የሚፈጽሙብን ግፍ ይቅርና በ1994 ዓ.ም ሐምሌ 21 ቀን በገዛ ቦታችን ላይ በሊቀ ጳጳሳቸው መሪነት አዘናግተው አታለው ያፈሰሱት የንጹሕ ኢትዮጵያዊ ደም በቂ ማስረጃ ነው::



# ምዕራፍ ሦስት

## ግብፃውያን ኢትዮጵያውያንን አጠቁ ሲባል እንዴት ነው

ምንጊዜም ግብፃውያን ኢትዮጵያውያንን አጠቁ ሲባል የሃይማኖት ወንድሞቻችሁ ነን እያሉ በማታለል እንጂ በሌላ መንገድ አይደለም:: ይህንንም ለመረዳት ከ 17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የፈጸሙብንን ተንኮል ከታሪኩ መመልከት ያበልጋል:: ለማስታወስም ያህል በገዳሙ የሚኖሩት አረጋውያን መነኮሳት፣ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ የታሪክ ሰነድ ብለው ከጻፉት መጽሐፍ ላይ መዝግበው ከያዙት ታሪክ ውስጥ ዋና ዋናውን እንደሚከተለው ገልጸነዋል:: ይኸውም:-

1ኛ. የኢትዮጵያ መነኮሳት ከላይ እንደገለጽነው ከጎልጎታ ወጥተው ከጎልጎታ በስተ ምሥራቅ ዴር ሡልጣን በተባለው በታላቁ ገዳማቸው በነበሩበት ጊዜ ግብፃዊው መዓልም ኢብራሂም ገሪሪ የሚባለው ሰው እ.ኤ.አ. በ1770 ዓ.ም ገደማ መጥቶ መነኮሳቱን አባቶች የሃይማኖት ወንድማችሁ ነኝ፤ በከተማው ቤት ስላጣሁ ከእናንተ ቦታ ማረፊያ ስጡኝ ብሎ ስለለመነ አስጠጉት:: እርሱም የተማረ ነበርና ከቱርክ መንግሥት ሥራ አግኝቶ ከፍ ያለ ባለሥልጣን ሆነና በመነኮሳቱ ላይ ሠልጥኖ ለእነርሱ ተጠያቂ ነኝ እስከ ማለት ደርሶ ከቤታቸው ከፍሎ ይስሐቅ ቤክ ለሚባለው ሰው በኪራይ ሸጠባቸው:: ቀጥሎም ወደ ግብፅ ተላልኮ ጊዮርጊስ የሚባለውን ግብጻዊ ቄስ አስመጥቶ በገዳሙ አስገባውና ኢብራሂም ገሪሃሪ ሲያልፍ ቀሲስ ጊዮርጊስ በሱ ሥፍራ ተተክቶ ለገዳሙ ዋና እኔ ነኝ አለ:: ግብፆች በዚህ የተንኮል ተግባራቸው ከገዳማችን ገብተው ከዚህ በኋላ የመጡ ግብፃውያን ሁሉ ሐበሾች የኛ ጥገኞች ናቸው እያሉ መነኮሳቱን ያንገላቷቸው ጀመር::

www.ethiopianorthodox.org

2ኛ/ ይባስ ብለው በ1820 ዓ.ም የገዳሙን ቤት እናሳድሰዋለን ልቀቁ በማለት ኢትዮጵያውያን ከነንዋያቸው ከገዳማቸው አስወጧቸውና ከታደሰም በኋላ ተመልሰው እንዳይገቡ አደረጓቸው:: መነኮሳቱም ሥፍራቸውን ለቀው መውደቂያ ቢያጡ የጭቃ ጎጆ እየበጁ ዛሬ ከሚገኙበት ሥፍራ ውስጥ ብቻ ተወስነው ቀሩ፡ ዋናውን የኢትዮጵያን ገዳም በዚህ ዓይነት የተንኮል ተግባራቸው አስለቅቀው እስካሁን ይዘውት ይገኛሉ::

3ኛ/ አሁንም እንደዚሁ ቀሲስ ጊዮርጊስ እኛ ከምንኖርበት ደር ሡልጣን ከፍሎ በምሥራቅ በኩል ያለውን ለመስኮቦች ሸጠው:: የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቦታውን መሸጡን ሰምተው ሊጠይቁት ቢጠሩት ደንግጦ በልብ ድካም ዐረፈ::

4ኛ/. በ1831 ዓ.ም የምሥር መሐመድ አሊ ልጅ ኢብራሂም ፖሻ ኢየሩሳሌምን ይዞ ስለነበር ለኮፕቶች እጅግ ጥሩ አጋጣሚ ሆነላቸው:: አበሾች በተላላፊ በሽታ ተለክፈዋልና በአካባቢው ያለው ነገር ሁሉ ተጠራርጎ እንዲቃጠል ትእዛዝ ይተላለፍልን ብለው ፈቃድ ጠየቁ:: ኢብራሂም ፖሻም ይህንኑ በመፍቀዱ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1838 ዓ.ም በኢትዮጵያውያን ቤተ መዘግብት ውስጥ የነበረውን የርስት ማስረጃና ካርታ ጭምር በቅዱሳት መጻሕፍት የተመላውን ግምጃ ቤት በሙሉ በእሳት አቃጠሉት :: ወዲያውም የገዳሙን መክፈቻ ቁልፎች እጅ አደረጉ:: በኢትዮጵያዊነቱ ለሚያምን ሁሉ ከዚህ የበለጠ የሚያናድድ የለም::



ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግብፆች ዴር ሡልጣን የሚባለው ገዳም የኮፕቶች ርስት ነው እንጂ የሐበሾች አይደለም ማለትን ደፍረው ለመናገር ቻሉ::

5ኛ/ ከላይ እንደጠቀስነው በ1838 ዓ.ም በዴር ሡልጣን ገዳም ተነሥቶ በነበረው ተላላፊ በሽታ ምክንያት ንብረታቸውን፣ ንዋየ ቅድሳታቸውንና መጻሕፍቶቻቸውን ቢያቃጥሉባቸውም እንኳ ኢትዮጵያውያን የራሳቸው ንብረት ሆነው በኖሩት በቅዱስ ሚካኤልና በበርባዕቱ እንስሳ አብያተ ክርስቲያናት ሲቀድሱና ሲጸልዩ ኖረዋል:: በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ አድርጎ ወደ ጎልጎታ የሚያሳልፍ፡ መንገድ በመኖሩ ቱሪስቶች ቤተ ክርስቲያኑን ጎብኝተው በዚያ ሲያልፉ ግብፃውያን መነኮሳትና ምእመናኖቻቸውም አብረው ያልፉ ነበር እንጅ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መቀደስ ይቅርና ቆመው የኅሊና ጸሎት እንኳ አድርሰው አያውቁም::

6ኛ/ በ1898 ዓ.ም ግብፆች የዴር ሡልጣን ሰሜኑን ጠባብ በር ባስፉት ጊዜ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ታላቅ ግጭት አድርገው ነበር:: በዚያ በቀል በጊዜው በነበረው ባለሥልጣን እየተረዱ ኢትዮጵያውያን በቤተክርስቲያናቸው እንዳይቀድሱና ቤተ ክርስቲያናቸው ተዘግቶ እንዲኖር አድርገዋል::

7ኛ/ አሁንም በዘመናችን በ1944 ዓ.ም አቡነ ፊልጶስ ተሾመው እንደመጡ ግብፆች «ዴር ሡልጣን የኮፕቶች ርስት ነው፤ ሕጋዊ ማስረጃ አለን፤» እያሉ ሲኖሩ ብፁዕነታቸው «በሰላምና በዕርቅ ለምን እንፈጽመውም፥ በዚህ በትንሹ ቦታ የተነሣ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጠብ ከሚፈጠር» ብለው ቢጠይቋቸው የትምክህት ኃይለ ቃል መልስ ከመስጠት በስተቀር በበጎ አመለካከት የማያቀርቡላቸው ሆነ:: በዚህን ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

አቡነ ፊልጶስ ሕጋዊ ማስረጃዎችን ሰብስበው በጆርዳን መንግሥት ክስ አቅርበውባቸው መልስ አሳጧቸው:: ግብፃውያን ግን መልስ ቢያጡ ከሕግ ለመሸሽ «አንድ ቤተ ክርስቲያን ነን፥ የባዕድ ዳኛ በመካከላችን አይገባብንም፤» አሉ:: የጆርዳን መንግሥትም «ሁለታችሁን በሚያጣላ በርስት እንጂ በሃይማኖት አልገባንም፤» በማለት በቀረበባቸው ክስ መሠረት የግድ እንዲቀርቡና አለን የሚሉትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ አስገደዳቸው:: በዚህን ዓይነት ከሁለታችንም በኩል የቀረበውን ማስረጃ የጆርዳን መንግሥት ዘጠኝ ዓመት ያህል መርምሮ ካጠናው በኋላ ግብፆች የጻፉትና የሰበሰቡት መሠረት የሌለው ሆኖ በመገኘቱ «የዴር ሡልጣን ጠቅላላ መብቱ የኢትዮጵያ ነው» ብለው ዐሥራ ሀራት ሚኒስትሮች የአጸደቁት ታሪካዊ ውሳኔ አስተላለፈ:: በ1953 ዓ.ም ይዞታችን ተረጋግጦ በሕግ ተረተው የተዘጋው ተከፍቶ ቤተ ክርስቲያኖቻችንን መልሰውልን እንድንረከብ ተደረገ::

ግብፆች ይህ ውሳኔ እስቀጥፏቸው በሕግ መሸነፋቸውን ሰውረው እንደልማዳቸው ባደረጉት ከፍተኛ ጩኸት የምስር ፕሬዝዳንት ጀማል አብዱል ናስር በጆርዳን ንጉሥ ላይ ባደረገው ከባድ ተጽዕኖ ውሳኔው ሳይሻር በቴሌፎን ትእዛዝ ፍርዱን አሳግዶ እንደገና የቤተ መቅደሶቹ ቁልፎች ለግብፃውያን ተመለሱላቸው:: በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ ገዳማት ላይ ከባድ ሐዘን ሆነ:: ፍርዱን የፈረደውና መልሶ ፍርዱን ያገደው የጆርዳን መንግሥት በጦርነት ድል ሆኖ፥ ሀገሪቱን ለቆ ሲወጣ ደግሞ የእሥራኤል መንግሥት ሀገሪቱን ተረክቦ ማስተዳደር ጀመረ:: የኢትዮጵያ ገዳምም ለእሥራኤል መንግሥት አቤቱታውን ለማሰማት መረጃዎችን አቀረበ:: ከዚህ በኋላ በሕጋዊ መንገድ የተፈረደውን ፍርድ መሠረት በማድረግ ለ135 ዘመን ያህል በግፍ ተነጥቀው የነበሩት በዴር ሡልጣን የሚገኙት የሀርባዕቱ እንስሳና የቅዱስ ሚካኤል ሁለቱን ቤተ መቅደሶች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን



ሚያዝያ 18 ቀን 1962 ዓ.ም እጅ አደረገች:: ተዘግተው የነበሩት ቤተ መቅደሶቻችን ተከፈቱ:: በዚህ ጊዜ የግብፁ ጳጳስ በእግዚአብሔር ላይ አኩርፎ ኀልኀታ አልገባም ከማለቱም በላይ የግብፃውያን ምእመናን ለትንሣኤ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይመጡ ከልክሏል::

በዚያ ቦታ ላይ የተፈጸመውን ግፍ አሁንም እንደገና እናስታውስ ካልን:-

1ኛ. አባ ገሚካኤል ሳህሉ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ብዙ ዓመታት ሲያገለግሉ ኖረው ሚያዝያ 10 ቀን 1940 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ከዴር ሡልጣን ገዳም ሬሳቸው በሚወጣበት ጊዜ ግብፆች ቀምተው የያዙትን የሴሚናዊ በራችንን ቆልፈው እንከፍትም በማለታቸው ሬሳቸው 3 ቀን ቆይቶ የኢየሩሳሌም ማዘጋጃ ቤት ጽዳት ሠራተኞች ወስደው ቀብረዋቸዋል::

2ኛ አባ ወ/ማርያም መርሻ በዴር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያውያንን መብት ለማስከበር ብዙ መከራ ሲቀበሉ ኖረው ከዕለታት አንድ ቀን በዴር ሡልጣን ገዳም ውስጥ በሰሜን በኩል ያለው ቅጽር እየፈረሰ ሲወድቅ ድንጋዩን አንሥተው ሲክቡ /ሲጠግኑ/ የግብፆች ቀዋስ እብደላ የተባለ ገፍትሮ ጣላቸው:: ጎናቸውም ተሰብሮ ደም እያስመለሳቸው ቆይተው በዚሁ ጠንቅ ምክንያት ጥር 10 ቀን 1946 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፤ አስከሬናቸው በበሩ ወጥቶ እንዳይቀበር የሰሜናዊ በራችንን ዘግተው 38 ሰዓት እንደቆየ የኢየሩሳሌም ማዘጋጃ ቤት ጽዳት ሠራተኞች ወስደው ቀብረዋቸዋል::

በዚህ አኳኋን እንደገዟቸው ክብቶች አድርገው በመመልከት የሰላም ኑሮ አሳጥተዋቸው ሲኖሩ የሞቱትም እንኳ በሰላም እንዳይቀበሩ ሰብአዊ መብታቸውን አሳጥተው ከሃይማኖታቸው ውጭ በሆኑ ሰዎች እንዲቀበሩ አድርገዋቸዋል::

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ከዚህ በላይ ለማስታወስ ያህል የተፈጸመውን ግፍ ከሞላ ጎደል ባጭሩ ጠቀሰን እንጂ ስለ ጎልጎታም ሆነ ስለዴር ሡልጣን ባለቤትነት የሚቀድመን ሳይኖር ዘወትር እንደ አንግዳ ደራሽ አድርገው ግብፆች በአባቶቻችን ላይ ሲፈጽሙት የኖሩት አሁንም የሚፈጽሙት ግፍ እንዲህ ባጭር ጊዜ ተዘርዝሮ የሚፈ ጸም አይደለም።

አሁንም ግፉ አለከእልተገታ ድረስ የመነኮሳቱ ፈቼኸት አይገታም፤ መንፈሳዊ ትግላቸውም አይቋረጥም። ነገር ግን ፈቼኸቱም ሆነ መንፈሳዊ ትግሉ የመነኮሳቱ ብቻ መሆን የለበትም፤ የመብት ጉዳይ ስለሆነ ሊያስብበትና ሊቆረቆርበት የሚገባው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። መነኮሳቱ በቦታ ጠ ባቂነታቸው የደረሰባቸውንና የሚደርስባቸውን ችግር ለሚሰማቸው ሁሉ ያሰማሉ።

ምክንያቱም፦

1ኛ. የሚኖሩበት ቦታ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያውም በሠለጠነው ዓለም ውስጥ የሰው ልጆች ሊኖሩበት ይቅርና እንስሳ እንኳ ሊያድርበት የማይገባ በጨለማ የተዋጠ ግበ በምድር /የቀበሮ ጉድጓድ/ ነው።

2ኛ. ሽንት ቤቱ ተበላሽቶ አካባቢው በክፉ ሽታ ተበክሎ አረጋው ያን አበው መነኮሳት በተለያየ ህመም እየተጠቁ ናቸው።

3ኛ. የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ጣሪያው እየተቀረፈ በመውደቅ ላይ ነው።

4ኛ. ሕዝብ በሚመላለስበት የጋራ ይዞታ በሆነው ቦታ በኛና በእነርቡ ግንብ ላይ መስቀል ያለው ሁለት ቅስት ተክለውበታል።



ይህም ይዞታን ለማስፋፋት እኛን ቦታ ለማሳጣት ነው። እነሱ ሲታትስኩ እያሉ እኛ እንዳናድስ እንደሚከለክሉ ሁሉ እኛ ልንከለክላቸው አልቻልንም፤ ለምን እንደተፈቀደላቸውም አልገባንም። ያልነበረ ነገር ተተክሎ ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ በአንድ ሌሊት በቅስቱ ላይ የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ይዞታ ነው ብለው እንደሚጽፉበት አያጠራጥርም። ይህም ቅልቅ ጥቃት ነው።

5ኛ. በጥንት ይዞታችን ቤት ውስጥ አንድ በው አስቀምጠ ውበታል። ይህ ቤት የኛ ለመሆኑ አያጠያይቅም። ከጥንት ጀምሮ በለማችን የተመዘገበው በቤቱ ውስጥ ያለው የመብራት ቆጣሪ ምስክር ነው። ይህንንም የተረዱ ኮፕቶች ቆጣሪውን በስማቸው ለማዛወር ከባለስልጣኖች ጋር እኛን እያታገሉ ማስረጃ ለማግኘት እየጣሩ ናቸው። በዚህም ቤት እንዲቀመጥ ያደረጉት ሰው በአርጅና ምክንያት ሲደክም ሌላ ወጣት ተክተውበታል። በማታለል ቤታችንን ነጥቀው በዚህ ቦታ ላይ የነሱ ሰው እንዲ ቀመጥ ካደረጉበት ምክንያት አንዱ የፈረሰውን እንዳናድስ፣ እንደነሱ የሰው ልጅ በሚኖርበት ቤት ክብራችን ተጠብቆ እንዳንኖር ለማድረግ፣ የየዕለት ሥራችንን እየተከታተለ አንድ ምለማር ሲመታ ጥቆማ እንዲያደርግላቸው ነው።

እነሱ ግን ሲታትሰኮ የሚባለው ሥርዓት ሳይገታቸው ውስጥ ለውስጥ መሬቱን በድጅኖ እየቆፈሩ ሦስት ዐራት አብያተ ክርስቲያናትና የተለያዩ ክፍሎችን አውጥተዋል። በዚህም ሁሉ ለምን እንዲህ ታደርጋላችሁ የሚላቸው ሰው አልተገኘም። እኛ ግን ከግንባችን ላይ የተፈነቀለ አንድ ድንጋይ መልሰን ከቦታው ለማኖር ይቅርና ወደ ቤት ውኃ የሚያስገባ የተሰነጠቀ ግንብ በሲ ሚንቶ ለመድፈን አይፈቀድልንም። መነኮሳቱም ተስፋ ባለመቁረጥ ዘወትር ለእስራኤል መንግሥት አቤቱታ እያቀረቡ ናቸው። በዴር ሱልጣን የሚገኙ አበው መነኮሳት ስለሚኖሩበት

www.ethiopianorthodox.org

ቤት ምክንያቱን ያልተረዱ የዓለም ቱሪስቶች ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጊዜ በኋላ የተፈረጀችው በድህነት ስለሆነ በድህነት ምክንያት መስሏቸው እኩሌቶቹ ከንፈራቸውን እየመጠጡ የሚያዝኑልን ሲሆኑ እኩሌቶቹ ደግሞ እበታዋሽ የሌላቸው ተረፈ ሕዝቦች ናቸው በማለት ሲያሽሟጥጡብን ይታያሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግብፃውያን ከብረው ገነው የሚታዩት በማናቸውም ነገር ከኛ የሚበልጡበት ምክንያት ኖሮ አይደለም፤ መንግሥታቸው በሃይማኖት ስማይመስሉት ዜጎቹ የውስጥም ሆነ የውጭ ፖሊሲው እንዳይናጋበት ለእስራኤል መንግሥት ጧት ማታ በለሚያሳስብላቸው በመብት ላይ መብት አግኝተው ስታትስኮ የሚባለው ውሳኔ ሳይገታቸው የፈለጋቸውን እየሠሩ የእኛን መነከሳት እያስቃዩ ይኖራሉ:: ይህም ጥረታቸው የኛ ሰዎች ተመርረው መኖሪያ አጥተው ቦታውን ጥለው ሲሄዱ ይዞታችንን እጅ ለማድረግ ነው::

እንደተባለውም አንዳንዶች አበው መነኮሳት መከራው አስመርሯቸው ~~ጧት ማታ አቤቱታ እያቀረቡ ናቸው::~~ ይህ አዝማሚያ የግብፃውያንን ሕልም እውን የሚያደርግ መስሎ ይታያል፤ እንግዲህ እኛ ኢትዮጵያውያን ለእስራኤል መንግሥት አመልክተን ችግራችንን የምናስወግድበት መፍትሔ የምናገኝ አይመስለንም:: አስተዋሽ ተቆርቋሪ እንደሌለው ዜጋ አድርገው መከራ የሚያጸኑብን ሁሉ ሲገቱ የሚችሉት እጃችንን ዘርግተን ይግባኝ ለክርስቶስ በማለት የማይቋረጥ ጸሎት ለማቅረብ ስንችል ነው:: እንደሚታወቀው የቀድሞይቱ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ተብሎ ተነግሮላታል:: ይህም የሚያሳየው በጸሎት በእምልኮት ለእግዚአብሔር ተገዥነቷን ሲሆን በእንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ምሕረት ጸጋና በረከት እስከ ዓለም ፍጻሜ እንደማይለያት የሚያመለክት ነው:: ይህንንም የተረዱ ጠላቶቿ ቅድስናዋን ለማጉደፍ እምነቷንና ጸጋዋን ለመግፈፍ ከጥንት ጀምረው ሲታገሏት ኖረዋል::



# ምዕራፍ አራት

## የዛሬይቱ ኢትዮጵያ

በዛሬይቱም ኢትዮጵያ ትግላቸውን አጠናክረው ይታያሉ፡- ድህነት ለመቀነስ፣ ዝክር፣ የጽዋ ማኅበር፣ ተዝካር፣ በዓል ማክበር ይቅር ይላሉ:: እንደሚታወቀው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ችግሯ አሁንም እንደ ቀድሞው ያለ ችግር ነው፤ ዛሬም ከቀድሞው ተያይዞ በመጣ የውስጥ ችግር በመታወኳ የኢትዮጵያነት መልኳ እየተለወጠ ነው:: በተለይ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ የደረሰባት ችግር መልኩን ለውጦ እየከበደ በመምጣቱ በተለመደ ቋንቋዋ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርስቶስ ሳያሰኛት አልቀረም:: ኢትዮጵያን ያላወቁ አለቁ፤ እንጂ አሁንም ያሉት ወደ ኋላ መለስ ብለው ታሪኳን ቢመረምሩ ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና እየተመራች እግዚአብሔርን ያወቀች፥ በሕገ ኦሪት እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ሲሉ ነቢያተ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የመሰከሩላት፥ ከ3000 ሺህ ዘመናት በላይ የበለጸገ ሕያው ታሪክ ያላት ለመሆኑ የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ያረጋገጡላት፥ ጥንታዊ የሰው ዘር መገኛ፣ የታሪክ ማኅደር፣ የሥልጣኔ ምንጭ፣ የዓለም ጥቁር ሕዝብ ማንነቱ የታወቀባት ቅድስት ሀገረ እግዚአብሔር ናት::

ሀገረ እግዚአብሔርም ያሰኛት ጥንት በሕገ ልቡና ኋላም በሕገ ኦሪት ቀጥሎም አሥሩን ቃላተ ኦሪት በስድስት ቃላተ ወንጌል አጠናክራ በሕጉ እየተመራች እግዚአብሔርን ስታገለግል በመኖሯ ነው::

እግዚአብሔርን አውቃ ሕጉን ጠብቃ ከመኖሯም የተነሳ ወዳጆቹ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት ቅዱሳን መላእክት ከቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም ጋር ምዕራፍ አድርገዋታል::

www.ethiopianorthodox.org

በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ምዕራፈ ቅዱሳን እሥራተ ማርያም ለመባል በቅታለች። ዝክር፣ የጽዋ ማኅበር በማዘጋጀት ቅዱሳን መላእክት ቃል ኪዳን የተቀበሉበትን፣ ተአምራት ያደረጉበትን፣ ጻድቃን፣ ቅዱሳን ሰማዕታት የተወለዱበትን በሰማዕትነት የሞቱበትን ዕለት፣ ወርና ዓመት ጊዜና ቦታ ለይታ በዓላቸውን በማክበር በስማቸው ለተራበ በማብላት ለተጠማ በማጠጣት ፍቅሯን እየገለጸች አትርሱኝ በማለት ስትማፀንባቸው ኖራለች።

ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕ፡ 16 ቁ 9 ላይ «እኔም እላችኋለሁ በኃላፊው ገንዘብ ለእናንተ ወዳጅ ግዙ፤ ገንዘባችሁ ባለቀ ጊዜ እነርሱ በዘለዓለም ቤታቸው ይቀበሏችሁ ዘንድ» ብሎ ያስተማረውን በተግባር መፈጸም ማለት ነው።

ላፈጸምም እመች ሆኖ ያገኘችው፡-

ሀ. ዝክር

ለ. የጽዋ ማኅበር

ሐ. ተዝካር

መ. በዓል ማክበር ነው።

## ዝክር

1ኛ ዝክር ማለት ዘከረ፡- ስም ጠራ፣ ተዘከረ፡- አሰበ ከሚለው ግእዛዊ ቋንቋ የወጣ ወይም የተገኘ ቃል ነው።

በዚህ ትርጉም ዝክር ስም መጥራት፣ ማሰብ፣ ማስታወስ ማለት ነው፣ የእግዚአብሔርን ባለሟሎች ስም ጠርቶ የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን አስቦ የመስጠት የመመጽወት መነሻው ወይም መሠረቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው። ቃሉም



«እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ፤ እኔንም የተቀበለ የላከኝን ተቀበለ፤ በነቢዩ ስም ነቢይን የተቀበለ የነቢይን ዋጋ ያገኛል። በጻድቅ ስም ጻድቅን የተቀበለ የጻድቅን ዋጋ ያገኛል፤ ከእነዚህ ከታናናሾች ላንዱ በደቀመዝሙሬ ስም ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ ያጠጣ እውነት እነግራችኋለሁ ዋጋውን አያጣም» የሚል ነው ማቴ 10፥40።

እንደሚታወቀው ልዑል እግዚአብሔር የማያደርገውን የማይናገር የቍናገረውን የማያስቀር እውነተኛ አምላክ ዘለዓለማዊ ጌታ የጽድቅ ባለቤት ነው። በመሆኑም እርሱን ለሚፈሩ ቃሉን ለሚያከብሩ በትእዛዙ ለሚመሩ ወገኖቹ ከመከራ ሊያድናቸው፥ በተድላ በደስታ ሊያኖራቸው፥ ዘራቸውን ባርኮ ሊያበዛላቸው ከብዙ ዘራቸውም መካከል በተፈጥሮ ገንዘቡ የሆነውን ዓለም የሚያድንበት ቤዛነት ያለው ዘር መርጦ እንደ ሚያስነሳላቸው ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል። እነሱም የተገባላቸው ቃል ኪዳን ተግባራዊ ሆኖ የሚጠቀሙበት መሆኑን አውቀው፤ «የሠራዊት ጌታ አሸናፊ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆን፤ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር፤» ብለዋል ኢሳ 1፥9

የቃል ኪዳኑም አመሠራረት አዋንዮስና አውሳብዮስ የተባሉት ሊቃውንት በመቅድመ ወንጌል እንደተናገሩት ነው። የመጀመሪያው ሰው አዳም ያደረገውን ስሕተትና የሠራውን ኃጢአት የተፈረደበትንም ፍርድ እያሰበ ልዑል እግዚአብሔርም መሐሪ ይቅር ባይ፥ ሰውን በንስሐ ተቀባይ፥ እንደመሆኑ መጠን በኃዘን ደፍርሶ ተሽብሮ የነበረ ልቡናውን በተስፋ ሊያጸናለት ስለፈቀደ አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ የምሕረት ቃል ኪዳን ሰጥቶታል። /ቀሌምንጦስ/ የቃል ኪዳንም ሁሉ መሠረት ይህ ነው። ሁለተኛም ከአዳም አሥረኛ ትውልድ በሆነው በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰብአ ትካትን በኃጢአታቸው ብዛት በፈሳ ውኃ አልም

www.ethiopianorthodox.org

ድርግም አድርጎ ሲያጠፋቸው ኖኅና ቤተሰቦቹን አድኖ ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሏት በእኔና በእናንተ መካከል ሕያው ነፍስ ባለውም ሥጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ:: ሥጋ ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ ዳግመኛ የጥፋት ውኃ አይሆንም ቀስቲቱም በደመና ትሆናለች በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ያለውን የዘለዓለም ቃል ኪዳን ለማሰብ አያታለሁ ብሎ ቃል ገብቶላቸዋል:: ለገባላቸውም ቃል ኪዳን ምልክት ወይም ማረጋገጫ አድርጎ ዐራት ሕብር ያላት ቀስት በደመና ላይ ዘርግቶ እስከ ዓለም ፍጻሜ እንድትኖር አድርጓል:: ዘፍ 9፥1-18:: ሦስተኛም ዓለም ሁሉ እንደፈረሰ ጥሮ እንደጦር ጉሮሮ ተካክሎ ጣዖት በሚያመልክበት ዘመን አብርሃም በሕገ ልቡና እየተመራ አምልኮተ እግዚአብሔርን ይዞ በመገኘቱ የመንግሥተ በማይ ምሳሌ የምትሆን ከነዓንን እንደሚያወርሰውና ዘሩንም እንደሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ እንደሚያበዛለት በዘሩም አሕዛብ እንደሚባረኩ ቃል ኪዳን ሰጥቶታል:: የሰጠውንም ቃል ኪዳን ለማረጋገጥ ይምልበት ዘንድ ከእርሱ በላይ ምንም ምን ስለሌለና ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ አምላክ አንድ እርሱ ብቻ ስለሆነ «እኔ ሕያው ነኝ ቃሌ ከአፌ በጽድቅ ወጥታለች አትመለስም ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ፤» ብሎ በመሐላ አጽንቶለታል ኢሳ 45፥23፣ ዘፍ.17፥2-9፣ ዘፍ. 22፥16::

ለይስሐቅና ለያዕቆብም ይህንን የመሰለ ቃልኪዳን ሰጥቷቸዋል ዘፍ.26፥2-5፣ ዘፍ. 35፥9-14 እንዲህም አድርጎ የሰጣቸውን የምሕረት ቃል ኪዳን ከነርሱ በኋላ የተነሡ ልጆቻቸው እነሙሴ ሳይንቁና ሳያቃልሉ «በራስህ የማልክላቸውን የአብርሃምንና የይስሐቅን የያዕቆብንም ቃል ኪዳን አስብ፤» እያሉ በመጸለይ ከአስቃቂ መቅሰፍት ከድንገተኛ ሞት ወገኖቻቸውን ሲያድኑ ችለዋል ዘፀ. 32፥9-15



ነገር ግን ከነሱ መካከል ደግሞ ስድስት መቶ ሺ የሚሆኑት ሠራዊት የታሪካቸውን ሂደት ስንመለከት የጥርጥር መንፈስ አድሮባቸው እናገኛቸዋለን:: እግዚአብሔር በራሱ ምሎ ለአባቶቻቸው የገባላቸውን ቃል ኪዳን እውነት ነው ብሎ መቀበል ስለተሳናቸው በምድረ በዳ እንደሻሸ ተነጥፈው እንደ ቅጠል ረግፈው እንደግንድ ተረብርበው መቅረታቸውን እንረዳለን:: ዘኁ. 14፥1-45::

ይህም ሁኔታ ከአዳም ጀምሮ ለተነሡ ቅዱሳን አባቶች የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን እውነት ነው ብሎ ቢቀበሉት ለምሕረት ሐሰት ነው ብሎ ቢያቃልሱት ለመቅሰፍት የሚዳርግ መሆኑን ያስገነዝባል::

እንግዲህ የአባቶች ቃል ኪዳን ይህን ያህል ግዳጅ ለመፈጸም የቻለበትን ምሥጢር ስንመረምር መሠረቱ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ ለአዳም የገባለት የምሕረት ቃልኪዳን ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ቃልኪዳን ከእግዚአብሔር ለሰው ባይመሠረት ኖሮ ሰውና እግዚአብሔር ፊት ተማልሰው ተራርቀውና በከረረ ፀብ ውስጥ ሁነው ፍጻሜ በሌለው ዘመን ሊኖሩ በቻሉ ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር የኀሊና ገዥ እንደመሆኑ መጠን የመጀመሪያው ሰው አዳም ያደረገውን ጸጸት አይቶና ተመልክቶ ይህን የምሕረት ቃል ኪዳን ሊሰጠው ችሏል::

አዳምም የተሰጠው ቃል ኪዳን ተፈጻሚነት የሚያገኘው በልጅ ልጁ መሆኑን ከተረዳ በኋላ ለሕይወቱ መገኛነት የተመደበችውን የልጅ ልጁን እምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን በተስፋ ሲጠብቃት ኖሯል:: በተስፋ ሲጠብቃት የነበረችውም የልጅ ልጁ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሁና ተገኝታለች:: ከዚህም የተነሣ ልደታ፣ በዓታ፣ ኪዳነ ምሕረት እያልን በዓሏን በምናከብርበት ቁጥር «መሠረተ ሕይወት ማርያም

www.ethiopianorthodox.org

ወጥንተ መድኃኒት ዘአምቀዲሙ» የሚለውን መዝሙር እንዘምራለን። ይህም ማለት ከቀድሞ ጀምሮ የድኅነታችን ጥንትና የሕይወታችን መሠረት እመቤታችን ማርያም ሆይ በጸሎትሽና በአማላጅነትሽ ለዓለም ቤዛ እንድትሆኝ አድርጎ ልጅሽን የፈጠረ እግዚአብሔር ስሙ የተባረከና የተመሰገነ ይሁን» ማለት ነው። እንዲህም እያልን ስለ እርሷ ያለንን አክብሮትና ፍቅር በመግለጽ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

ከዚህም ጋር ኪዳነ ምሕረት እያልን በስሟ እንመጸውታለን። ኪዳነ ምሕረት የሚለውም አነጋገር ምንም እንኳ ቃል ኪዳን የተቀበለችበትን ዕለት የሚያስታውስ ቢሆንም ምሥጢሩ ሲመረመር በእርሷ አማካይነት የተነገረው የምሕረት ቃል ኪዳን እንደመጠሪያ ስም ሆኗት ኪዳነ ምሕረት እየተባለች ስትጠራበት የምትኖር መሆኗን የሚያስገነዝብ ነው።

ምክንያቱም የአዳም ተስፋው፣ የኖኅ መርከቡና የቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተደመናው፣ ዘር ያልወደቀባት የአብርሃም እርሻውና አሕዛብ የሚባረኩባት ንጽሕት ዘሩ እርሷ መሆኗን ሊቃውንት ሳይሠውሩ፣ አንቺ ነሽ ብለዋታል። እንዲህም ከሆነ ለቅዱሳን አባቶች ቃል ኪዳን መነሻውና መድረሻው መሠረቱና መደምደሚያ ጉልላቱ በእርሷ አማካይነት የተመሠረተው ቃልኪዳን ስለሆነ ኪዳነ ምሕረት ተብሎ መጠራት ይገባታል። በመሠረቱ ማርያም ማለት ወደ መንግሥተ ሰማያት መርታ የምታስገባ ማለት ነው። እንደስሟም ትርጓሜ ተወዳዳሪ የሌላት ንጽሕትና ቅድስት፤ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች የአምላክ እናት በትሆን ከፍጹም ርኅራኄዋ የተነሳ ከጻድቃን ይልቅ ለኃጥአን በዚህ ዓለም አልቅሳለች። በልጇ መቃብር ላይም ሁና የምሕረት ቃል ኪዳን ለምናለች፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ልመናዋን ሰምቶ ቃል ኪዳኗን ተስፋ የሚያደርገውንና



በስሟ የሚማጸነውን እንደሚምርላት የካቲት 16 ቀን የምሕረት ቃል ኪዳን ሰጥቷታል። በዚህም መሠረት ፍጹም ኃጢአተኛ የነበረው ስምዖን የተባለው ሰው በስሟ ተማጽኖ ለተጠማው ድኃ ጥርኝ ውኃ በማጠጣቱ ምክንያት ለተድላ ገነት እብቅታዋለች።

በጥርኝ ውኃ እንዴት መዳን ይቻላል የሚል ጠያቂ ቢኖር ለተጠማው ደሀ ጽዋ ውኃ ያጠጣ ዋጋውን አያጣም ብሎ የተናገረ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ከላይ የጠቀስነውን ቅዱስ ቃሉን ይመልከት እንላለን። ማቴ.10፥40

## የጽዋ ማኅበር

2ኛ. ለጽዋ ማኅበር መሠረቱ ከላይ የጠቀስነው ቢሆን ማኅበርተኞች ማኅበራቸውን በነቢያትም ሆነ በሐዋርያት በመላእክትም ሆነ በጻድቃን በሰማዕታት በተለይም በእመቤታችንና በመድኃኔ ዓለም ስም ይሰይሙታል። እንደቁጥራቸው ብዛት በዓመት 12 ቀን ተካፍለው እያንዳንዱ ማኅበርተኛ በተራው ለማኅበርተኞቹ የሚሆነውንና ለነዳያን የሚመጸወተውን አቅሙ እንደፈቀደ ያዘጋጃል። ወሩ ሲደርስ ማኅበርተኞቹ ከቤተ ክርስቲያን አስቀድሰው እንደተመለሱ በተረኛውም ቤት ሆነ በቤተክርስቲያን አካባቢ ዝግጅቱ ባለበት ቦታ ይገኛሉ።

በሙሴውና በምክትል ሙሴው አማካይነት ሰዓልናከ በመባል የሚጠራው ኅብስት በመሶብ ወርቅ፣ ወይኑ በጽዋ ተሞልቶ ይቀርብና ካህኑ ይጸልይበታል። የተጸለየበትንም ሰዓልናከ ሁሉም ከቀመሱ በኋላ ቦታ ቦታቸውን ይይዛሉ፣ በሙሴውና በምክትል ሙሴው አማካይነት ምጽዋቱ ለነዳያን ይሰጣል።

ማኅበርተኞቹም ድርሻቸውን ከተሳተፉ በኋላ የፕሮግራሙ ፍጻሜ ሲቃረብ ሙሴው ከምክትል ሙሴው ጋር በመሆን ተረኞቹን ለማስጠንቀቅ ማነህ ባለሳምንት ያስጠመድህ በአሥራ ስምንት፣ ማነህ ባለሁለት ያስጠመድህ በአሥራ ሁለት፣ ማነህ ባለ

www.ethiopianorthodox.org

ሦስት ያስጠመድህ በአሥራ ሦስት፣ አያለ ከማኅበርተኞቹ ጋር የቅብብሎሽ ድምፅ ከአበማ በኋላ ተረኞቹ በተራ እየተነሡ፡- «እኔ ነኝ ወንድማችሁ ቢያውለኝ ቢያውላችሁ ቈጠማዬን ኅዝጉዤ ማይ ቀድቼ እቆያችሁ፤» በማለት ግንባራቸውን መሬት አስነክተው ከጉዝጓዙ ላይ ይወድቃሉ፣ ካህኑም እንደወደቃችሁ ኃይለ እጋንንትን ያውድቅላችሁ፣ የራቀውን ያቅርብላችሁ፣ የቀረበውን ያዘጋጅላችሁ፣ ለየወሩ በሰላም ያድርሳችሁ:: ብሎ ከጸለየላቸው በኋላ በክብር ያንሳችሁ ብሎ ይመርቃቸዋል::

ሙሴውም ቀጠል አድርጎ «ባለአራት ተራህን እትሳት ጌሾህን ኮትኩት ብቅልህን አብቅል፤ ሙሴ፥ ግልገል /ምክትል/ ሙሴ አይናችን በሳላብን እጃችን በአዳላብን፤ ባለቤት ዳቦው ባረረበት ጠላው በቀጠነበት ማሩን እንላለን::» በማለት ተራቸውን ከጉዝጓዙ ላይ ይወድቃሉ::

መላው ማኅበርተኛም «ሙሴ፥ ግልገል ሙሴ ዓይናችሁ እልሳላም፤ እጃችሁም አላዳላም፤ ባለቤት ዳቦውም አላረረ ጠላውም እልቀጠነ ሁሉም መልካም ነው:: ስለማናቸውም ግን ይቅር ይበላችሁ፤» ይላሉ:: ለዚህም ካህኑ «ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ይበላችሁ፤ ማኅበራችንን ያስፋ፤ አምላክ ቅዱሳን ረድኤቱን በረከቱን ያድላችሁ፤» ብሎ ከጸለየ በኋላ ኑዛዜ ሰጥቶ ያሰናብታቸዋል::

በዚህም አኳኋን ክርስቲያኖች በጽዋ ማኅበር ተሰባስበው የሚሠሩት በጎ ሥራ ለነፍስና ለሥጋ ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኝ ነው:: ለነፍስ «ብራብ አብልታችሁኛል፣ ብጠማ አጠጥታችሁኛል፤» አሰኝቶ መንግሥተ ሰማያትን ለማውረስ የሚያበቃ ሲሆን በሥጋዊም ኑሮ በዙል ከማኅበርተኞች አንዱ የታመመ እንደሆነ አባላት የሚታከምበትን ገንዘብ አዋጥተው ያሳክሙታል::



እርሻውን አርሰው፣ ዘር ዘርተው፣ አርመው ኮትኩተው፣ አጭደው ወቅተው እህሉን በጎተራ ይሞሉለታል::

ሚስቱ እንዳትቸገር ልጆቹ እንዳይራቡ እየተንከባከቡ ታሞ እስኪነሳ ድረስ በዚህ አኳኋን ይረዱታል:: ቢሞትም ተዝካሩን ያወጡለታል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የጽዋ ማኅበር ለክርስቲያኖች ይህንንና ይህን የመሰለ ከፍተኛ ጥቅም ያለው ነው::

## ተዝካር

3ኛ ተዝካር ማለት የሙታን መታሰቢያ ማለት ነው:: ሲራክ «የሞተ ሰውስ ዐረፈ ነገር ግን ነፍሱ ታርፍ ዘንድ ተዝካር አውጣለት ከዚህ በኋላ ለቅሶህን ተው::» ብሏል ሲራ. 38+10 ቤተዘመዶቻችንን በቁርባን በጸሎተ ፍትሐት ሁልጊዜ እንድናበባቸው ይህ አነሱን በእጅጉ እንደሚጠቅማቸው፥ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር በባለሟልነት እንደሚያቀርባቸው ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ያበተማሩንን ጠቅሰው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ኩኩሐ ሃይማኖት በተባለው መጽሐፋቸው ዝከርና ተዝካር ከሚለው አንቀጽ ላይ ምዕ 17 ከገጽ 223 እስከ 234 ድረስ በሰፊው ጽፈውታል ያንን መመልከት ጠቃሚ ነው::

ሠለስቱ ምዕትም በፍትሐ ነገሥት ሕያዋን ለሙታን ሙታን ለሕያዋን ቢጸልዩ ከፍተኛ ጥቅም የሚገኝ መሆኑን አስረድተውናል::

በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ ሙታን የሚጠቀሙበትን ሕያዋን በረከት የሚያገኙበትን ተዝካረ ሙታን፥ ጸሎተ ፍትሐት ቁርባን አያለች በማዘጋጀት ጠቃሚ ሥራ ስትሠራ ኖራለች::

www.ethiopianorthodox.org

# በዓል

በዓል ማለት ዕረፍት ክብር ማለት ነው። የሰው ልጅ ሠርቶ ማረፍን በዓል ማክበርን በፈጠራ የጀመረው አይደለም። ሠርቶ ማረፍን ያሳየ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የሠራ ውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ። በሰባተኛው ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ፣ እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም እግዚአብሔር ሊሠራው ከጀመረው ሥራ ሁሉ ዐርፎበታልና፤» ይላል። ዘፍ.2+2።

በዚህም መሠረት የሰው ልጅ ሁሉ ከተግባረ ሥጋው ዐርፎ በዓል እንዲያከብር የሥራና የዕረፍት የክብር ባለ ቤት እግዚአብሔር ትእዛዝ ሰጥቷል። ትእዛዙም የእግዚአብሔር የአምላክህን ሰንበት አክብር የሚል ነው ዘጸ.20+8፣ ይህ ከዐሥሩ ቃላት አንዱ ነው። አምላካዊ ትእዛዝ በመሆኑም ሰው ሊሽረው የማይችል ነው።

ነገር ግን ትእዛዝ ማፍረስ ከአባት ከእናት የተለመደ በመሆኑ እንደ ውርስ ተቆጥሮ ይህንን አምላካዊ ትእዛዝ አፍርሰው ድህነትን ለመቀነስ በዓል አንሻር የሚሉ ልጆች በዘመናችን ተፈጥረዋል፣ ምንአልባትም ካለማወቅ የተነሣ ከሆነ በዓል መሻር የሚያመጣውን መዘዝ ለመረዳት ከፈርዖንና ከሰለጸአድ ታሪክ ቢ ማሩ የሚሻላቸው መሆኑን ከወዲሁ እንመክራቸዋለን።

ሙሴና አሮን ከእግዚአብሔር ታዘው ፈርዖንን «ፈንዎሙ ለሕዝብየ፤ ይግበሩ በዓልየ በሀቅል፦ በዓሌን እንዲያከብሩ መሥዋዕት እንዲሠውልኝ ወገኖቼን ልቀቅ» ብሎሃል እግዚአብሔ ር» ቢሉት «ቃሉንስ እሰማ ዘንድ እስራኤልንስ አለቅ ዘንድ እግዚ አብሔር ማነው? እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልንም ደግሞ አለቅም፤» አለ። ከዚህ በኋላ የደረበበት የመከራ ዓይነት፦



1ኛ. የወንዙ ውኃ ተለውጦ ደም ሆኖበታል፤
2ኛ. ወንዙ ጓጉንቸር እንዲፈላበት ሆኖ ወንዙ በከፋ ሽታ ተበክሏል፤
3ኛ. የምድሩ ትቢያ ቅማል ሆኗል፤
4ኛ. ተቆናጣጭ ዝንብ ሠፍሮ ሰውንም ከብትንም የሚያሳድድ ሆኗል፤
5ኛ. የግብፅን ከብት የሚፈጅ ቸነፈር ተልኳል፤
6ኛ. ሻህኝ ቁስል በሰው ሁሉ ላይ ተልኳል፤
7ኛ. በረዶና እሳት እንድነት ዘንቧል፤
8ኛ. ምድርን የሚያሰብስ አንበጣ ታዟል፤
9ኛ. ሰው የሚዳሰሰው ሥስት ቀን ሙሉ ጽኑ ጨለማ ሆኗል፤
10ኛ. ከሰው እስከ እንስሳ ያለውን በኩር የሚፈጅ ሞተ በኩር ታዝዟል፤
11ኛ. በኤርትራ ባሕር ከነሠራዊቱ ሰጥሟል፤

ይህንንም ታሪክ ለመረዳት ዘጸ 5 እስከ 13 ምዕራፍ ያለውን መመልከት ያስፈልጋል። ከእስራኤል ልጆችም መካከል ሰለጽአድ የተባለው በው ሰንበት ሽሮ ጭራሮ በመልቀሙ የደረሰበት ቅጣት ምን ይምስል እንደነበረ ዘኁልቁ 15 ቁጥር 32 ላይ ተመልክቶ መረዳት ይቻላል። እንግዲህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አቃሎ እግዚአብሔር በሚያመጣው መቅሰፍት የበዓል ሻሪ ዶቄት ከመሆን መጠንቀቅ፤ በዓል መሻር የሚቀንሰው ድህነትን ሳይሆን ረድኤትንና በረከትን እንደሆነ ማወቅ ያ ስፈልጋል። ታላቅ ብልህነትም ነው።

ኢትዮጵያም ይህን አውቃ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከ982 ዓመተ ዓለም ጀምሮ ከልደተ ክርስቶስ በኋላም እስከ ዛሬ ድረስ ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የሠራባቸውን ዓበይትና ንዑሳት በመባል የተቆጠሩትን አሥራ ስምንት በዓላት እያከበረች በነዚ ህም ላይ የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታትን የመላእክትን የእመቤታችንን በዓላት ስታከብር ኖራለች።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አምስት

## ምዕራባውያን በክህደት መርዝ ያደነዘዟቸው

ዛሬ ግን ምዕራባውያን በክህደት መርዝ ያደነዘዛቸው አንድ አንድ ሰዎች መሠረታዊ አቋሟን እያናወጡት ይገኛሉ። እነዚህ ሰዎች የኢትዮጵያ ልጆቿ ሳይሆኑ የአንጀራ ልጆቿ ናቸው። ስለሆኑም አውሮፓውያንን ደም ሲያፋለስ የኖረውን ክህደት ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ አድሰው ኢትዮጵያን ሥርዓት አልባ ለማድረግ ሲጥሩ ይታያሉ።

ተገላምጠው የሚያዩት ሰው ከማጣታቸው የተነሣ የጨለማው ፋና በመባል በታወቁት በነክቡር መልአክ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ መቃብር ላይ ቆመው ችግርን ወይም ድህነትን ለመቀነስ ዝክር፣ ተዝካር ይቅር፤ ድህነትን ለማጥፋት በዓል ይሻር በማለት የነ ዘመንፈስን ርኩስ መጽሐፍ በሥራ ለመተርጐም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲጮሁ ይሰማሉ።

የሐዋርያትን ትእዛዝ የሠለስቱ ምዕትን ድንጋጌ በይፋ ለማፍረስ ይህን ያህል ሲታገሉ ከነ መምሬ አዘነ በቀር እነ መምሬ አደፍርስና እነ መምሬ አሸብር በቃል ድጋፍ ሰጥተው በጭብጨባ ሲያጸድቋቸው በማየታችን በእጅጉ አዝነናል ።

ይህንንም ስሕተት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ይቀበሉታል ባይባልም ስሕተትነቱ እየታወቀ የነበረውን ሥርዓት ለማፍረስ ሆን ተብሎ በተቀናበረ ስብሰባ ላይ እንዲነገር ማድረጋቸው ቤተክርስቲያኒቱን መናቅ የሃይማኖት መሪዎቹንም እንደሌሉ መቁጠር ስለሆነ በእጅጉ ያናድዳል። እነዚህንም ሕግ አፍራሾች የሃይማኖት መሪዎች የሆንን ሁሉ ልንመክራቸው ልንገሥጻቸው. እምቢተኞም ሲሆኑ ልናወግዛቸው በተገባ ነበር። ነገር ግን የሃይማኖት መሪዎች ዝም ካልን ኢትዮጵያ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርስቶስ ከማለት በቀር ሌላ ኃይል የላትም።



# አንቀጽ አንድ

## ከብርሃን ወደ ጨለማ አሳዛኝ ጉዞ

ዛሬ ዓለም በሠለጠነበት የወንጌል ብርሃን በሁሉም ስፍራ በደረሰበት በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱሱ ክርስቲያን ሕዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ ቀላል አይደለም። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያን ሕዝብ የቀደሙ ቅዱሳን አባቶች አስተምረውና አሳምነው አጥምቀውና አቁርበው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ያደረጉት መሆናቸው ለማንም የተሰወረ አይደለም።

ባሁኑ ጊዜ ግን ይህንን ቅዱስ ክርስቲያን ሕዝብ በዘመናችን የተነሣው አስመላይ ጨካኝ ትውልድ በጭካኔ ወደ ጨለማ እየመራው ነው። እውነቱ የት ቦታ እንደሆነ እየታወቀ የሥልጣን ጥሙን ለማርካት ሲል ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን ራሱንም ጭምር በማታለል፡ እኔና መሰሎቼ ታግለን ሕገ መንግሥት አጽድቀንልሃል፤ ድንጋዩንም፣ ዛፉንም፣ ባሕሩንም የፈለግኸውን ልታመልክ ትችላለህ፤ ዲሞክራሲዊ መብትህ ነው፤» እያለ ሲወተውተው ሰምተናል።

በክርስቶስ ደም የከበረ ክርስቲያናዊ ስውነቱን ለጣዖታዊ ሥርዓት የፈሰሰ የእንስሳ ደም እየቀባ ሊያረክሰው ሲታገለው አይተናል። በዚህ ጉዳይ ላይም ከእኛ ወገን ትኩረት ሰጥቶ ለማስተማርም ሆነ ለመገሠጽ ቢያንስ ተገቢ አለመሆኑን እንኳ ለመግለጽ ሙከራ ያደረገ የለም። ምክንያቱም የስሕተቱን አስፈጻሚ ኃይሎች በመፍራትና የመንግሥትን አዋጅ ተቃወመ ይሉኛል በማለት ነው። ይህም አለማስተዋል ነው እንጂ መንግሥትም ቢሆን ክርስቲያኑን ሕዝብ ከክርስትና ጎዳና

www.ethiopianorthodox.org

እያፈናቀላችሁ በየወንዙ እያንከራተታችሁ በሠለጠነው ዓለም ዘንድ መሣለቂያ አድርጉት ያለ አይመስለኝም:: እንደ እውነቱ ከሆነ በተቀደሰ ክርስቲያናዊ ሕዝብ ላይ ይህን የመሰለ ደባ ሲፈጸም ከማየት የበለጠ አሳዛኝ ነገር የለም:: ሁላችንንም የሚያስፈርድብን ነው:: ይህም ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ አደጋ በመሆኑ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርስቶስ ከሚያሰኝ በደል እንዱ ነው:: ምክንያቱም የእግዚአብሔርን አምልኮት የሚቃወም ነገር በሀገር ላይ ከመጣ ሀገር ሰጥፋት ሰውም ለስደት ለሞት መዳረጉ የማይቀር ነው::

ብዙ ጦር ሠራዊት አሰልፎ በከባድ መሣሪያ ከሚወጋ ጠላት ይልቅ በሰው ላይ የተለያየ ተጽእኖ እያደረገ መጥፎ ምክር እየመከረ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣላ ጠላት ይከፋል:: እንዲህ ያለው ሰው ሁለተኛው በለዓም ይባላል:: በለዓም እስራኤልን ረግሞ ማጥፋት ቢሳነው ለጣዖት የተሠዋውን መሥዋዕት ለአሕዛብ ቆነጃጅት አበይዞ ወደ እስራኤል ሰፈር ሰደዳቸው:: የእስራኤል ጉልማሶችም የአሕዛብን ቆነጃጅት ባዩ ጊዜ እግዚአብሔርን ረስተው ለጣዖት የተሰዋውን እስከ መብላት ደርሰው ከአሕዛብ ቆነጃጅት ጋር አመነዘሩ:: እግዚአብሔርም ለአምልኮቱ ቀንቶ መቅሰፍት አምጥቶ በአንድ አፍታ 24ሺህ ሰው በመቅሰፍት ቀጥቷል:: ዘኍል 22፥1፣ 25፡፥10

ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር እየወደደው እግዚአብሔርን የሚጠላ ሕዝብ መከራ አይለየውም:: ለዚህም ሌላ ምስክር ሳንሻ እግዚአብሔር የሚወደው የኢትዮጵያ ሕዝብ በክሐድያን መሪዎች ግፈት ግራ እጁን አውጥቶ እግዚአብሔር የለም ካለበት ሰዓት ጀምሮ የተፈራረቀበት አሠቃቂ መከራ በቂ ማስረጃ ነው::



# አንቀጽ ሁለት

# የማይገባ ትምክህት

ዛሬም እግዚአብሔር ሕዝቡን ካለመታረቁ የተነሣ ከአንዳንድ ትምክህተኞች የምንሰማው ድምፅ ለጥሮ የከበደ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ነው:: ይኸውም ክብር ምስጋና ለኃያሉ ክንዳችን የሚል ነው:: በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያውያን ጥሮ እንዲሰማው የሚፈልገው ክብር ምስጋና ለኃያሉ እግዚአብሔር የሚለውን ምስጋና ብቻ ነው:: ነገር ግን ከቀድሞዎቹ የኋለኞቹ ካለመማራቸው የተነሣ የኃያሉ እግዚአብሔርን ብርቱ ክንድ አሁንም ሲክዱት ይታያሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ የቀድሞውን አሳልፎ ያሁኑን ያመጣ ኃያሉ እግዚአብሔር እንጂ የኔ ክንድ ያመጣው ድል ነው ብሎ ሊመካ የሚገባው ፍጡር ሊኖር ባልተገባም ነበር::

ይህ ትውልድ ከነጌዴዎን መማር ነበረበት:: ጌዴዎን ሦስት መቶ ሰው ብቻ ይዞ ከምድያማውያን ጋር በተዋጋ ጊዜ የተመካው በክንዱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ነው:: ለጦርነት የተዘጋጀው ሠላሳ ሁለት ሺህ ሰው ነበረ:: እግዚአብሔር ግን «ሰው በዝቷልና ቀንስ!» አለው:: ምክንያቱንም ሲነግረው፣ «እስራኤል: - እጄ አዳነኝ ብሎ እንዳይታበይብኝ ነው!» ብሎታል:: መሳ.7፥2:: ቅዱስ ዳዊትም መልካም አብነት ነው:: በክንድም በጉልበትም በጦር መሣሪያም መቶ እጥፍ ከሚበልጠው በጉልያድ ፊት በቆመ ጊዜ በእጁ የነበረው ጠጠር መወርወሪያ ወንጭፍ ብቻ ነበር:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ተመክቶ «በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ!» አለው:: በጠጠርም ግንባሩን መትቶ ገደለው:: የሚገርመው ነገር ጉልያድ:- በጦር ተወግቶ፥ በሰይፍ ተመትቶ፥ በፈረስ ተገፍቶ የማይወድቅ ሰው ነበረ:: 1ኛ ሳሙ.17፥45-47:: ከዚህም የምንረዳው ነገር ቢኖር ጉልያድን ከነዱ እንዳሳዳነው ነው:: እነ ፈርዖንም በቀይ ባሕር ሰምጠው ቀሩ እንጂ ክንዳቸው አላዳናቸውም:: ዘጸ.14፥26-31::

ነገር ግን አለመታደል ሆነና የኢትዮጵያ አምላክ እግዚአብሔር አሁንም በኢትዮጵያ ላይ ተፈሪነትን አላገኘም:: ሁሉን አድራጊ ፈጣሪ መሆኑንም ያወቀለት የለም የዚህም ውጤት ድርቅ፣ ረሃብ፣ ቸነፈር፣ ሞት፣ ስደት ሁኗል::

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ስድስት

# ስደተኞቹ እነማን ናቸው ?

ዛሬ ስደተኞቹ የፖለቲካ ሰዎች ሳይሆኑ ሠርቶ አደሮች ናቸው:: ድህነትን ለመቀነስ ድሆችን ማብዛት የሚጠቅም ይመስል በየፋብሪካውና በየኢንዱስትሪው ተቀጥረው ቤት ንብረት መሥርተው አሥር እና አሥራ አምስት ቤተሰብ ያላቸውን ሠራተኞች ባለ ኢንዱስትሪዎቹ ሠራተኛ ቅነሣ በሚል ፈሊጥ ከሥራቸው እያባረሩዋቸው የሚላስ የሚቀመስ አጥተው ሀገር ጥለው ተሰድደዋል:: ስደቱም በነሱ ብቻ ሳይገታ ሃያ አራት ሰዓት እንደመላእክት በቅዳሴ በውዳሴ በማኅሌት በዝማሬ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ የአድባራት ሊቃውንትና የገዳማት መነኮሳት ከመንፈሳዊ አልግሎታቸው ላይ በተለያየ ምክንያት በማይጨበጥ ተስፋ እየተፈናቀሉ በአውሮፖ፣ በሰሜን አሜሪካ፣ በካናዳ ወዘተ. በመሳሰሉት አህጉራተ ዓለም ሲንገላቱ ወይም ሲንከራተቱ ይታያሉ:: የስደቱ በር የተዘጋባቸው ደግሞ ከቆሙት በታች ከሞቱት በላይ ሆነው መከራቸውን ያያሉ:: እነዚህም ቀኑ የጨለመባቸው፥ ሜዳው ገደል የሆነባቸው ናቸው::

ስደቱም ሁለት ዓይነት ነው፤ ይኸውም አንደኛው የምሁራን አባቶች ስደት ሲሆን፣ ሁለተኛው የልጆች ስደት ነው:: ምሁራን አባቶች ቢሰደዱ ከሀገራቸው፤ ቢፈናቀሉ ከሥራቸው ነው:: ከሃይማኖታቸው አይናወጡም:: ከመንፈሳዊ ዓላማቸው አይለወጡም፤ ይለወጣሉ ተብሎም አያሰጋም:: ምክንያቱም የሃይማኖታቸውን ምስጢር ስለተረዱት የሃይማኖት ፍቅር አላቸውና ነው:: በእጅጉ የሚያሳዝኑት ግን ልጆቻቸው ናቸው:: ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱት ሕፃናቱ ለልመና ሲዳረጉ ማየት አንጀት የሚያላውስ ሐዘን ነው:: መሰደድ የሚችሉት ጉልበት ያላቸው ደግሞ ወንዶቹ መሐመድና ዓሊ፣ ሴቶቹ ፋጡማና ከዲጃ



በመባል ስማቸውንና ሃይማኖታቸውን ለውጠው በዓረብ ሀገሮች ተሰደው ማየትም እጅግ የሚዘገንን ነው:: ባልሠሩት ክፉ ሥራ ሲጠረጠሩም ሴቶቹ የፈላ ውኃ እየፈሰሰባቸው፣ ወንዶቹም በትሳለ ሰይፍ አንገታቸው እየተቀላ የትም የሚወድቁ መሆናቸውን መስማት እጅግ ያሳዝናል:: ከሞት የተረፉት ደግሞ ወደ ሀገራቸው ቢመለሱም በዕለት ጉርስ ሳገኙት፥ ኅጅነቱንም ሆነ ጠቃሚነቱን ሳልተረዱት እምነት ተቆርቋሪ ሆነው ክርስትና የተነሱባትን ቤተክርስተያን ለማፍረስ ከተቃዋሚዎቿ ጋራ ወግነዋል:: እሳት ሊያነዱባትም ክብሪት እየጫሩ ናቸው::

ይህም ኢትዮጵያን ወይም የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የወላድ መካን አድርጎ ባዶ የሚያስቀር ከባድ አደጋ በመሆኑ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርስቶስ የሚያሰኝ ነው:: እጅግ የሚያሳዝነው እንደ ባሪያ አሳዳሪው ዘመን ዛሬም ዜጎቻችን ሃይማኖታቸውን እየለወጡ እንደ ከብት ሲሸጡ መታየታቸው ነው:: በመሠረቱ ቀድሞ በታሪክ እንደሰማነው አሳዳሪው ወይም ጌትየው አገልጋዩን ያለውድ በግድ ይሸጠው ነበር እንጂ ሳይገደድ በራሱ ገንዘብ ራሱን የሚሸጥ አገልጋይ አልነበረም:: ዛሬ ግን ልጆቻችን በራሳቸው ገንዘብ ራሳቸውን እየሸጡ ለሥራ ተሰደው በሄዱበት ሀገር ሠርተው ዶላር ሊያተርፉ ይቅርና ራሳቸውን ከመከራ ለማትረፍ ተስኗቸው እያለቀሱ የመከራቸው ዜና ሲያስለቅስን የሚኖር ሁኗል:: ይህንንም ከተረዳን:-

1ኛ. በምክንያትም ሆነ ያለምክንያት ከሥራቸው አፈናቅለው ዘመዶቻቸውን ለመተካት ሲሉ ለስደትና ለመከራ የዳረጓቸውን፤

2ኛ. ዶላር በቁና እንደሚታፈስ አስመስለው እየሰበኩ በማታለል ታሪክ የማይረሳው በደል የፈጸሙባቸውን ግፍ አድራጊዎች ልንገሥጻቸው ከዚያም አልፎ ልናወግዛቸው በተገባን ነበር:: ምክንያቱም እንደዚህ ያሉትን ሰዎች በጊዜውም ያለጊዜውም መምከር ማስተማር መገሠጽ እንደሚገባ ከቅዱስ ጳውሎስ

www.ethiopianorthodox.org

ተምረናልና ነው:: «ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ዝለፍና ገሥጽ ምከርም:: ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ:: እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ:: አንተ ግን ነገርህን በልክ አድርግ፥መከራን ተቀበል፥ የወንጌልን ሰባኪነት ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም::» የሚል ነው:: 2ኛ ጢሞ.4፥2-5:: በተጨማሪም «ሌሎቹ ደግሞ እንዲፈሩ፥ኃጢአት የሚሠሩት በሁሉ ፊት ገሥጻቸው::» የሚል አለ:: 1ኛ ጢሞ.5፥20:: ነገር ግን በታዘዝነው መሠረት ሊገሥጹ የሚገባቸውን አልገሠጽናቸውም::

ምን አልባት ሳይሰሙን ምን አደከመን እንል ይሆናል:: ነገር ግን እነርሱ ሰሙም አልሰሙም እኛ መናገር አለብን:: ፀሐይ የሚሞቀኝ የለም ብላ ከመውጣት፣ ወንዝም የሚጠጣኝ የለም ብሎ ከመፍሰስ እንደማያቋርጥ ሁሉ መምህራንም የሚሰማን የለም ብለን ዝም ማለት የለብንም:: ጌታ ባይሰሙም ለአይሁድ ነግሯቸዋል:: የግብፁ ንጉሥ ፈርዖን ባይሰማም ሙሴና አሮን እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ተናግረውታል:: ነቢዩ ኢሳይያስ ከናፍሩ በለምፅ የረከሱት ንጉሡ ዖዝያን አይሰማኝም ብሎ ዝም በማለቱ ነው:: ኢሳ.6፥5:: ሊቀ ካህናቱ ዔሊም በሥጋ ዝምድና ተሸንፎ ልጆቹን ባለመገሠጹ በመቅሠፍት ሞት ተቀጥቷል:: ልጆቹም ለጦር ሜዳ ተቅስፈዋል:: ሊቀ ካህናቱ ዔሊ በዚህ ሥራው ራሱንም ልጆቹንም ማትረፍ አልቻለም:: ስለዚህ ራሳችንንም ሆነ ሌላውን ሳናተርፍ ከእግዚአብሔር መንገድ መውጣት የለብንም:: ምክንያቱም ዓለም ልቡን አደንድኖ እኛን ባይሰማ እግዚአብሔር ፍርዱን መስጠቱ አይቀርም:: እመቤታችን «በክንዱ ኃይል አድርጎአል፤ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል፤ ገዢዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል፤» ያለችው ለዚህ ነው:: ሉቃ.1፥51:: ስለሆነም ለተራቡት ወገኖቻችን ልንምኽላቸው ይገባል::



በማቴዎስ ወንጌል እንደተጻፈውም «እነዚህን ሰዎች እንደራባቸው ልሰዳቸው አልፈቅድም፤» ብሎ ሰባት እንጀራና አንድ ዓሣ አበርክቶ የተራቡትን አራት ሺህ ሰዎች አሰባስቦ እንደመገባቸው ዛሬም የተራቡትን ከተሰደዱበት አሰባስቦ ሊመግባቸው የሚችል የበረከት ባለቤት ነው:: ማቴ 15፥32-39

እኛ ከችግረኞች ጎን መቆም ከተሳነን በእኛ ፈንታ ለተበደሉ ወገኖቹ በአጋርነት የሚቆሙ እንደ ኤልያስና እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ ያሉ መንፈሳውያን መሪዎችን ሊያስነሣሳቸው ይችላል::

## አስረጅ አንድ
## ኤልያስ ስለናቡቴ

ኤልያስ በናቡቴ ጉዳይ ላይ ገብቶ ምን እንዳደረገ ለመረዳት በሚከተለው ዓይነት ታሪኩን መመልከት ያስፈልጋል::

ናቡቴ የሚባል እስራኤላዊ ነበረ:: ይህ ሰው በንጉሡ በአክአብ ቤተመንግሥት አካባቢ ከአባቶቹ የወረሰው የወይን ቦታ ነበረው:: ንጉሡ አክአብ ናቡቴን አስጠርቶ «የወይን ቦታህን ልቀቅልኝ፥ በቤተመንግሥቴ አካባቢ ስለሆነ እፈልገዋለሁ ሌላ ቦታ ተካልኝ ብትለኝ እተካልሃለሁ ወይም በሽያጭ መልክ ዋጋውን እከፍልሃለሁ፤» ሲል ጠየቀው:: ናቡቴም «ይህን ርስት ይህን የወይን ቦታ የወረስኩት ከአባቶቼ ነው፤ ከአባቶቼ የወረስኩትን የወይን ቦታ እሰጥህ ዘንድ እግዚአብሔር አያድርግብኝ አልሰጥህም፤» ብሎ መለሰለት:: በዚህ ጊዜ አክአብ ተናዶ ከቤቱ በመግባት እህል ውኃ አልቀምስም ብሎ ተበሳጭቶ ተኛ:: ሚስቱ ኤልዛቤልም «ምን ሆነህ አዝነህል?» አለችው:: እርሱም «ናቡቴ የወይኑን ቦታ ስጠኝ ወይም ሽጥልኝ ብለው አይሆንም ስላለኝ በዚህ ምክንያት ተናድጄ ነው፤» አላት:: እርሷም:-

www.ethiopianorthodox.org

«አሁን ተነሥተህ እህል ቅመስ፤ መንግሥቱ የእኛ ነው እንጂ የእርሱ ነውን? ነገ የማደርገውን አሳይሃለሁ!» ብላ አጽናንታው አድራለች::

ንግሥት ኤልዛቤል እግዚአብሔርን የማትፈራ ሰሰው የማታዝን የማትራራ ኃጢአት ለመሥራትም የምትደፍር ነበረች:: በመሆኗም ወዲያውኑ ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቧል ብላችሁ መስክራችሁ፥ ሕዝቡን ሰብስባችሁ፥ በድንጋይ ወግራችሁ ግደሉት!» ብላ የሞቱን ደብዳቤ ጽፋ አሽከሮቿን አዘዘች:: አሽከሮቿም እንደታዘዙ ሕዝቡንና የሀገር ሽማግሌዎችን ሰብስበው «እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሲሰድብ ሰምተነዋል!» የሚሉ የሐሰት ምስክሮችን አስመስክረው በድንጋይ ወግረው ገደሉት:: አርሷም መሞቱን በሰማች ጊዜ «ናቡቴ ሙቷልና ሔደህ የወይኑን ቦታ ውረስ!» ስትል ለአክአብ ነገረችው:: እርሱም እንደነገረችው: - የወይኑን ቦታ ለመውረስ ሲወርድ እግዚአብሔር ተቆጥቶ «ያስገደልከውን የናቡቴን የወይን ቦታ ልትወርስ ወረድክን ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተንም ደም ይልሱታል ይላል እግዚአብሔር ብለህ ንገረው!» ሲል ነቢዩ ኤልያስን ልኮታል:: ኤልያስም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ነግሮታል:: ነገሥ ቀዳ. 20፥19 ኤልዛቤልም በተመሳሳይ መቅሠፍት እንደምትሞት ሲናገር «በግፍ ባስገደለችው በናቡቴ የወይን ቅጽር አጠገብ ኤልዛቤልን ውሾች ይበሏታል» ብሏል:: ነገሥ. ቀዳ. 20፥23

ነቢዩ ኤልያስ በዚህ አኳኋን «ድሀ ተበደለ ፍርድ ጎደለ!» በማለት እግዚአብሔር እንደአዘዘው ንጉሡንና ንግሥቲቱን ሳይፈራና ሳያፍር በፊጸሙት ግፍ ገሥጿቸዋል ዘልፏቸዋል::



# አስረጅ ሁለት

## ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለደሀይቱ መበለት

የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዘመኑ ፍርድ እንዳይጎድል ድሀ እንዳይበደል ጠንክሮ የሚያስተምር፥ ነገሥታቱን እንኳን ለመገሠጽ ወደኋላ የማይል፥ የድሆች መመኪያ የምእመናን አለኝታ የሆነ ታላቅ አባት ነበር::

ይህም ታላቅ አባት ከሚያስተምራቸው ምእመናን መካከል የንጉሡ የአርቃድዮስ ሚስት ንግሥት አውዶክስያ መፍቀሪተ ንዋይ፥ ገፋኢተ ነዳይ መሆኗን ታሪክ የመሰከረባት ናት:: ለለገንዘብ ፍቅር ፍርድ በማጉደል፥ ደሀ በመበደል የታወቀች ጨካኝ ነበረችና የአንዲት ድሀ ሴት የከተማ ቦታ ነጥቃ ወሰደች:: ድሀይቱም ሔዳ ከዮሐንስ አፈወርቅ ዘንድ ተማጸነች:: የደረሰበትንም በደል ስትገልጽ: - «እኔ ተረድቸበት ልጆቼ የሚረዱባትን በዓመት ሦስት ጊዜ የምታፈራውን ለቤተክርስቲያን ቅርብ የምትሆነውን ቦታየን ንግሥት አውዶክሰያ አለውድ በግድ ቀምታ ወሰደችብኝ», ብላ ነገረችው:: እርሱም ይህን ሰምቶ «መልሽላት!» ብሎ መልእክተኛ ላከባት:: አውዶክስያም የላከበትን ነገር በሰማች ጊዜ «ቦታይቱ ለቤተ መንግሥት ቅርብ ናት ብዬ ነው:: እንዲያው ልውሰድብሽ አላልኋትም፤ አሁንም ቦታ ብትል ቦታ ገንዘብም ብትል ወርቅ ብር ልስጣት!» ብላ መልሳ ላከችበት:: ከዚህ በኋላ እንዲህ ብላለች ብሎ ነገሩን ቢነግራት «እንደነገርኩህ ቦታዬ ለቤተ እግዚአብሔር ቅርብ ናት በዓመት ሦስት ጊዜ ታፈራለች፤ በዚህም ላይ ርስት የመንግሥተ ሰማይ እምሳል ነው፤ ስለሆነም እኔንም ልጆቼንም ከምድራዊ ርስትና ከሰማያዊ ርስት ነቅያቸው አልሞትም» አለችው:: እርሱም «አይሆንም ብላለችና መልሽላት!» ብሎ መላልሶ መከራት:: ብዙ ጊዜም ማለዳት፤ እርሷ ግን ሰይጣን አድሮባታልና «ይሆናል አይሆንም የምትል እርሷ ማን ናት? መንግሥቱ የኔ ነው እንጂ

www.ethiopianorthodox.org

የርሷ ነውን?» ብላ ላከችበት። በዚህ ጊዜ እርሱ «መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ» ነውና «ክምእመናን አትገናኚ፤ ቤተ ክርስቲያን አትግቢ፤ ሥጋውን ደሙን አትቀበይ፤» ብሎ አወገዛት። እርሷም ወደ እስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ወደ ቴዎፍሎስና ወደ ቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ ወደ ኤጲፋንዮስ ዘንድ ወደ ሌሎችም ጳጳሳት አዝና ተቆጥታ ላከች።

ሊቃነ ጳጳሳቱና ኤጲስ ቆጶሳቱ ተሰብስበው መጡ። እርሷም «ዮሐንስ አፈወርቅ ያደረገብኝን እዩልኝ በሙሉኝ፤ በሃይማኖት ያይደለ በምግባር ብንጣላ እወገዘኝ፤ እንግዲህ ወዲህ እኔ ከሱ ጋራ እሱ ከኔ ጋር መኖር አይሆንልኝም፤ ዕለት ዕለት ያሳዝነኛልና፤ ስለ ዚህ ጉባኤ ሠርታችሁ መጽሐፍ ተመልክታችሁ የሚሻርበትን ምክንያት ፈልጋችሁ ከሹመቱ እንዲሻር አድርጉልኝ፤» አለቻቸው። እነርሱም «ክምድር በላይ ደግነቱ በእራሱ ማዕዘን የታወቀ፤ ትምህርቱ ከሁሉ የደረሰ ዮሐንስ አፈወርቅን ምን ምክንያት ፈልገን እንሽረዋለን፤ አይሆንም፤» አሏት። እርሷም «ይህን ካላደረጋችሁ አብያተ ጣዖታት ይትረኃዋ አብያተክርስቲያናት ይትአጸዋ ብዬ አዋጅ አነግራለሁ የቀደመውን የአባቶችን ዘመን በአዋጅ አመልሰዋለሁ፤» አለቻቸው። እነርሱም «በዚች ሴት ሰይጣን አድሮባታል፤ ሰይጣን ደግሞ ያበጀመረውን ማስገፋት ልማዱ ነውና አሁን ያሰበችውን ተናገረች እንግዲህ ወዲህም የተናገረችውን ሳታደርገው አትቀርም።» ብለው ወደ ዮሐንስ አፈወርቅ ሔዱ። «ሃይማኖት የሆነ እንደሆነ ዕለቱን ጠንክር ይሉበታል፤ የምግባር ነገር እየቀደም ይደረጋል፤ አሁንም ክግዝት ፍታት፤ ይህ ካልሆነ የእባቶቼን ዘመን እመልሰዋለሁ ብላለች፤ እንዲህ ከሆነ መናፍቃን ጠፉ ምእመናን ዐረፉ፤ ክህደት ጠፋ ሃይማኖት በፋ ሰንል፤ እንግዲህ ወዲህ ሃይማኖት መጥፋቱ አይደለምን?» አሉት። እሱም መልሶ «ይህም እንጂ ሃይማኖት ነው፤ ንጉሥ በዘውዱ፤ ደሀ ባመዱ እንደሚባለው ጌታ፡- ሁሉ በየገንዘቡ ጸንቶ ይኑር ብሏል፤ ይህችስ ሃይማኖቷን ትክድ የለምን? ዳግመኛስ እርሷ የአባቶቿን ዘመን ብትመልሰው እኔስ ከአባቶቼ አለያለሁን? በዚያውስ ላይ እርሷ



በገሃነመ እሳት ስትቃጠል ትኖራለች እንጂ እኔ ምን እጎዳለሁ፤ አይሆንም» አላቸው። ከዚህ በኋላ ተመልሰው በየቦታቸው ሔደዋል። እነሱ ከሔ ዱ በኋላ ግን ንግሥቲቱ እውዶክስያ ተቆጥታና ተበሳጭታ፡- ክፉ ሥራ ሠርተው፤ ፈጣሪያቸውን በድለው፤ ዮሐንስ አፈወርቅ አውግዞ የለያቸው፤ ከሹመታቸውም የሻራቸው ብዙ ኤጲስ ቆጶሳት ነበሩ። እነዚያን ሰብስባ ከአደባባይ ተገኝታ «ዮሐንስ አፈወርቅ በማይገባ ነገር አውግዞኛልና ፍረዱኝ፤» አለቻቸው። እነዚያም እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው በማይገባ አውግዟታልና ተግዞ ተሰዶ ይሙት በቃ ብለው ፈረዱበት።

ከዚያ በኋላ እርሱን መንፈቀ ሌሊት አበጠርታ በፈረስ በሠረገላ አድርጋ ደሴተ አጥራክያ ሰዳዋለች። እርሱም በዚያ ተግዞ ተቀምጧል፤ ባጋዘችውም ጊዜ በከተማ ያሉ ንጉሡም፤ መኳንንቱም፤ ሕዝቡም፤ ካህናቱም፤ ከፈረስ ከሠረገላ ወረዱ፤ ያለጫማ ሔዱ፤ ከል ለበሱ፤ ከል ጠመጠሙ፤ እንደ አባት ያከብሩት፤ እንደመምህር ያፍሩት ነበርና በርሱ ስደት በርሱ ግዞት አዝነው ተክዘው ተቀመጡ።

ዳግመኛም ንጉሥ በሚገዛው ህገር ሁሉ ፍጹም መነዋወጽ ተደረገ። አስቀድመን እንደተናገርነው እርሱ አጥራክያ በደረሰ ጊዜ በደሴት ያሉ ሰዎች «እንግዲህ ይመክረናል፤» ብለው እጅግ ደስ አላቸው። እርሱም መክሮ አስተምሮ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ መለሳቸው። በዚያን ጊዜ የሮሙ ንጉሥ አኖሬዎስ ሊቀ ጳጳሳቱም ዮናክንዲኖስ ይባሉ ነበር። እነሱም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተጋዘ ሰምተው አዝነው ተቆጥተው ለንጉሡ ለአርቃዲዎስ ደብዳቤ ላኩበት። ደብዳቤውም «ከዚህ ከሠራኸው ሥራ ተከልክለህ፤ የኛን ቃል ሰምተህ፤ ዮሐንስ አፈወርቅን ከቀደመ ቦታው ከቀደመ መዓርጉ ካልመለስከው እንግዲህ ወዲህ በእኛና በአንተ መካከል ፍቅር አንድነት የለም፤» የሚል ነው። እርሱም የላኩበትን ደብዳቤ በተመለከተ ጊዜ አዝኖ ተክዞ የሷን ፈቃድ ነሥቶ መልእክተኛ ሰዶ ዮሐንስ አፈወርቅን ከተሰደደበት አስመጥቶ ከቀደመ ቦታው ከቀደመ

www.ethiopianorthodox.org

መዓርጉ መልሶታል። ይህም በተደረገ ጊዜ በቁስጥንጥንያ ያሉ ሕዝቡ ሁሉ እጅግ ደስ አላቸው። ንግሥቲቱ አውዶክስያ ግን ዮሐንስ አፈወርቅ ከስደቱ መመለሱ ያስፈቃዷ ነበርና ሌላ ምክንያት ፈልጋ እንደገና ቀድሞ ወደ ተጋዘበት ሰፍራ ሰደደችው። እርሱም በመንገድና በእሥራት ድካም ሰለጸናበት ፃና ከመድረሱ በፊት ግንቦት እሥራ ሁለት ቀን በአራት መቶ ሰባት ዓ.ም ዐረፈ።

እግዚአብሔርም በታማኝ አገልጋዩ ላይ ስለደረሰው ግፍ መፍረዱን አልተወም። «ወእመንደባ በደዌ ዓቢይ» ይላል በዕኑ ደዌ ታማ ተሠቃይታለች፤ እድናስሁም ብላ ለብዙ መድኃኒት ብዙ ገንዘብ ጨርሳለች። ነገር ግን «ወእልቦ ዘበቁዓ ዘእንበለ ዘአልሀማ» ተብሎ በወንጌል እንደተጠቀሰችው ሴት ደዌዋ እየባሰባት ሔደ እንጂ አላዳናትም። ከዚህም በኋላ ሰክፉ እድራጊ በጎ መካሪ አይታጣምና፤ «ከዮሐንስ አፈወርቅ መቃብር ሔደሽ ብትማፀኚ እርሱ ይማልድሻል እግዚአብሔርም ይቅር ይልሻል፤» ብለው መከሯት። እርሷም ይህን ሰምታ ፈጥና ሔዳ ከመቃብሩ ላይ ወድቃ «የሩኅሩኅ ሎሌ ራራልኝ የአዛኝ ሎሌ እዘንልኝ የበደልሁህን በደል ይቅር በለኝ!» እያለች ብትጸልይ ከደዌዋ ተፈውሳለች። ይህም የሚያስረዳው የቅዱሳንን አማላጅነት ነው።

ይህ እውነተኛ ታሪክ የተገኘው ከሰንክሳር፣ ከዮሐንስ ፣ ከአቡሻህር፣ ከጊዮርጊስ ወልደአሚድ፣ ከሐዊ፣ ከገድለ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው።

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደገለጽነው የኤልያስና የዮሐንስ አፈወርቅ ታሪክ የሚያስገነዝበን ማንኛውም የሃይማኖት መሪ «ፍርድ ጎደለ፣ ደሀ ተበደለ!» ብሎ የመገሠጽ ሥልጣን ያለው መሆኑን ነው።



# አንቀጽ ሦስት

## ባሁኑ ጊዜ የአክአብን ያህል እንኳ የሚጸጸት አልተገኘም

በእርግጠኛነት ለመናገር ባሁኑ ጊዜ ኤልያስን ወይም ዮሐንስ አፈወርቅን ሁኖ ለመገኘት ይቅርና ከራሴ ጀምሮ ከኛ ውስጥ የአክአብን ያህል እንኳ በሚታየውና በሚሠራው ክፉ ሥራ የሚጸጸት አልተገኘም። በያዝያን ዘመን እግዚአብሔር ኢሳይያስን ለመገሠጽ እንደተናገረው፥ ሰው ሁሉ ራሱን ጠብቋል፤ አንገቱን ቀብሯል፥ በፍርሃት ተውጦ ዝምታን መርጧል በዚህም ምክንያት እንደርስት የሚጠቀሙበት ደመወዛቸው ተነጥቆ ስሌላ እየተሰጠ ምሁራኑ ሲሰደዱ ልጆቻቸው ለልመና ሲዳረጉ የርኅራኄ ድምፅ ያሰማቸው የለም።

ይህ ዓይነቱም የጭካኔ ጠባይ የሰብአዊ መብት መሥራችና የርኅራኄ ምንጭ ከሆነችው እናት ቤተክርስቲያን ጠባይ ጋራ ተቃራኒ ነው። ሊቃውንት ያወግዙታል ምእመናንም አጥብቀው ይሸሹታል። ለሽሽታቸውም መመሪያ ያደረጉት «ከዚያች አገር ሲያሳድዷችሁ ወደ ሌላ አገር ሽሹ፤» ተብሎ በማቴዎስ ወንጌል በም. 10 ቁ. 23 ላይ የታዘዘውን አምላካዊ ትእዛዝ ነው። በዚህም መሠረት ከጥቂቶቹ በቀር ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን በዓለም ዙሪያ የሚገኘውን የስደተኞች ካምፕ አጣበው ይገኛሉ።

በመሠረቱ ኢትዮጵያ በረዥም ታሪኳ ውስጥ ለዘመናት የስደተኞች መጠጊያ ሁና ትኖር ነበር እንጂ የእርሷ የሆኑት ተሰደው በስደተኞች ካምፕ የተመዘገቡበት ጊዜ አልነበረም። ነገር ግን ወደ ክምኒስቱ ዓለም ደርሳ ግራ እጇን በእግዚአብሔር ላይ ከቃጣች ጀምሮ ለንስሐ የሚያበቃ መካሪ አጥታለች። አሁንም በድፍረት ብሔራዊ ሃይማኖት የለኝም እስከማለት በመድረሷ ሳታጣ ያጣች፣ በራሷ ምሁራን ሌላውን ዓለም ያበለጸገች ራሷን ግን በድህነት አረንቋ የጣለች ሀገር ሁና ትገኛለች።

www.ethiopianorthodox.org

የዛሬን አያድርገውና ክርስትናን በንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ አማካይነት በመጀመሪያው መቶ ዓመት (በ34 ዓ.ም) የተቀበለች ሀገር ናት:: የተቀበለችውንም የክርስትና ፋና በጨለማ ውስጥ ለነበሩ ሰዎች በትምህርተ ወንጌል እንደ ዕንቁ ያበሩ ብዙ ቅዱሳን አበው ፈልቀውባታል:: የውጭ አገር ተወላጆች የሆኑ ዘጠኙ ቅዱሳን አበው ወበን ድንበር ሳይገታቸው ለመጠጊያነት ወይም ለመኖሪያነት የመረጧት ገናና ሀገር ናት::

ቀድሞም ሆነ ዛሬ ኢትዮጵያ ታይቶ የማይጠገብ ቅርስ ተነግሮ የማይበለች ታሪክ፥ የተቀደሰ ባሕልና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ያላት ሀገር ናት:: ይህም እውነት በነገረ መለኮት ሊቃውንትም ሆነ በዓለም ጠቢባን የታመነ ነው::

የዚህ ሁሉ አኩሪ ታሪክ ማዕከል ግን ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ናት:: ምክንያቱም የራሷ ፊደል ያላት፣ ከዓለም በፊት በመላእክት ዜማ እግዚአብሔርን ያመለገነች አገር ነች:: ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንደዛሬው ባልተስፋፋበት፥ የዕውቀት ብርሃን ባልተዘረጋበት፥ የሥልጣኔ ቅርስ በሌሎች ዓለማት ባልታየበት ዘመን፤ ቋጥኝ ፈልፍላ ተራራ ንዳ በሰማያዊ መቅደስ አንጻር ብርቅና ድንቅ የሚሆኑ እግዚአብሔር የሚመለገንባቸውን መቅደሶች የሠራች ይህች ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ታሪክ መሠረት ወይም ማኅደር ናት::

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክም የሚነበበው፣ የሚተረጐመው ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ነው:: እንግዲህ የዚች የዓለም ጥቁር ሕዝብ ነፃነት ምሳሌ የሆነች ኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊቷን ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ባህል ረስቶና አኮላሽቶ፣ ክዶና አፍርሶ፣ የምዕራባውያኑን እምነትና ባሕል መከተል ማለት ከአንድ ቢሊዮን በላይ ነው የሚባለውን የጥቁር ዓለም የበው ዘር ታሪክ ማጻፈንና የመንፈስ ኩራቱን መልሶ ማጨለም ነው:: እንደገናም ለቅኝ ግዛት አሳልፎ መስጠት ማለት ነው:: ከዚች ታሪካዊት ቡርክተ ማኅፀን እናት ቤተክርስተያን የተገኘ ትውልድ ሁሉ ይህን እውነታ ልብ ሊለው ይገባል::

ዘር ከመከር፣ መሠረት ከጉልላት የተባበረላት ሐዋርያዊቷ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መላው ታሪኳ ከኢትዮጵያ ጋር የተበናበለ ነው:: ምክንያቱም የሀገሪቱ የደስታና የመከራ ሕይወት ተካፋይ ናትና::



ኢትዮጵያ በታሪኳ የተቀበለችውን ማንኛውንም የመከራ ገፈት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሳትቀምስ ያለፈችበት ጊዜ ይኖር ይሆን? ጭራሽ ፍፁም የለም:: በዮዲት፣ በግራኝ መሐመድ፣ በድርቡሾች እንዲሁም በፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ለአምስት ዓመታት የተፈራረቀው በቆቃና መከራ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊቷ ቤተክርስቲያን የጋራ ታሪክ ለመሆኑ የታሪክ መዛግብት ዋቢ ናቸው:: ለዚህም ምስክሩ የምንጊዜም የኢትዮጵያ ሕዝብ መመኪያና መከበሪያ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን በማዕታት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና፣ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ዘጎሬ የፈጸሙት አንፀባራቂ የሰማዕትነት ገድል ነው:: ይህም ከላይ የተገለጸውን ታሪክ እንደ ብሎን የሚያጠነክር ሐቅ ነው:: በዚህ ብሩህ የመሥዋዕትነት ጐዳና ታልፎ ነው ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህልውና የተጻፈባት የታሪክ መዝገብና የዓለም ጥቁር ዘር የነጻነት ምሳሌ ለመሆን የበቃችው::

የኢትዮጵያ ባለውለታ የሆነችው ጥንታዊቷና ኢትዮጵያዊቷ ቤተክርስቲያን በግንባር ቀደምትነት ያደረገችው ከላይ የተገለጸው አንጻባራቂ ገድልና የከፈለችው መሥዋዕትነት ሁሉ ተረስቶ በ1966 ዓ.ም በዘውድ ምትክ የተተካው የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት እንደ ባዕድ በመቁጠር ያላትን ሀብት ወርሷል:: ገዳማውያን አበው መነኮሳት ንብረታቸውን አጥተዋል:: ሁለተኛው ፓትርያርክ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ በግፍ ተገድለዋል::

ህገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመያ ጊዜ «እግዚአብሔር ያለም!» የሚል ቃል እግዚአብሔር ሲመለክበት፣ ውዳሴ ቅዳሴ ማኅሌት ለእግዚአብሔር ሲቀርብበት በኖረው መስቀል አደባባይ ላይ ተነግሯል:: ይህም ምእመናንን ለመንፈሳዊ እልህ አነሣስቷል:: ወጣቱን ትውልድ ከቤተክርስተያን ለማራቅ አኢወማ በሚል ድርጅት ስም ቤተ ክርስቲያንን ታግሏታል:: ይህን የአሥራ ሰባት ዓመታት የክህደትና የመከራ ባሕር እግዚአብሔር በከሃሊነቱ የሚያስተምረንን ትምህርት አስተምሮ ማሻገሩ የትላንት ትዝታ ነው::

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሰባት

# ክህደትን በዲሞክራሲ ያወጀ ትውልድ

በእግዚአብሔር ቸርነት የመከራ ደመና ከምድረ ኢትዮጵያ ተገፍፎ በምትኩ ፌዴራላዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚል አዲስ መንግሥት ከተመሠረተ ዛሬ ደግሞ አሥራ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል:: ለኢትዮጵያ ሕዝብም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኗል ተብሏል:: ለእኔ እንደሚገባኝ ዲሞክራሲ ማለት ምስፍና ሕዝብ ማለት ነው:: የሕዝብ የበላይነት፣ የሕዝብ ገዥነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ማለት ነው::

ዛሬ ግን ትውልዱ ዲሞክራሲ የሚለው የአባቶችን ታሪክ ማኮሳሸቱን፣ የኑዛዜ ቃላቸውን መርሳቱንና በኢትዮጵያዊነቱ ማፈሩን ነው:: በሌላ መልኩ በምዕራባውያን ቅጥረኞች ግፊት ሃይማኖቱን ሲለውጥ ወድቆ ወደማይነሣበት የክህደት አዘቅት እንደሻማ ሲቀልጥ የታደሰ መሰሎት ተሐድሶ በሚል ፈሊጥ ተሰባስቦ ቤተክርስቲያኒቱን ለማፍረስ ሲሯሯጥ የውስጥ ድጋፍ ከመስጠት በቀር ተው ተመለስ ብሎ ገሥጾ የሚገታው አልተገኘም::

የራስን ትቶ እንደ ቅኝ ተገዥ የባዕዳንን ባህል እምነትና ሥርዓት መከተል ሀገርን መካድ ወደ ባንዳነት መለወጥ መሆኑን አላወቀም:: እንደሚታወቀው አንድ ሀገር በየትኛውም የዓለም ክፍል ከራሱ ማንነት ጋር የሚመሳሰል እምነትና ባህል አለው:: በመሆኑም የሰው ወርቅ ስለማያደምቅ የሌላውን መከተል አያስፈልግም:: የኛ ሳይሆኑ የእኛ መሰለው ከእኛ ጋር የነበሩ ሰዎች



ግን ይዘውት የቆዩትን እምነትና ሥርዓት የተቀደሰውን ኢትዮጵያዊ ባህል ሲለውጡት አላመነቱም:: ጥቂትም ቅሬታ አልተሰማቸውም ክህደታቸውንም በዲሞክራሲ ስም አውጀዋል::

ይህም የሚያሳየው የዲሞክራሲ ባህል የነፃነት ትርጉም ላልገባቸው፣ እውነቱን በሐሰት እምነቱን በክሕደት ለውጠው ለሚዘላብዱ ሐሰተኞች ፍሬ ቢስ ገለባዎች ትርጉሙን እንኳ ሳይረዱት ዲሞክራሲ ማወጅ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን መሆኑን ነው::

ዛሬ ፍቅር እየቀዘቀዘና እየጠፋ በኢትዮጵያዊነት ስሜት መረዳዳትና መተሳሰብ እየተረሣ ሂዷል:: ኢትዮጵያዊው ለኢትዮጵያዊው ባዕድ ሆኖ ሁለት ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር ሲገናኙ መጀመሪያ የሚጠያየቁት ክልላቸውን ነው:: ይህም ጠባብ አስተሳሰብ ሥር እየሰደደ ሲሔድ ተተኪው ትውልድ ኢትዮጵያዊነቱን እየረሳ ስለሚሄድ ችግሩ ከባድ ነው:: ይህም ብቻ አይደለም ለኢትዮጵያ ወርቃማ አገልግሎት ያበረከተች ለትውልዱ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ ድንቅና ለዓለም ቁሪስት መስህብነት ያላቸው ቅርሶችንና ታሪካዊ ባህልን ያወረሰች ኢትዮጵያዊቷ ቤተክርስቲያንም በምዕራባውያኑ ሚሲዮናውያን ከዳር እስከ ዳር እየታመሰች እየተፈተነች ነው:: የሕልውናዋም ማንነት በጥያቄ ውስጥ ገብቷል::

የዛሬን አያድርገውና ይህች ቤተክርስቲያን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በብሔራዊ ፍቅር አዋሕዳ ያኖረች አንድነቱንም በብዙ መሥዋዕትነት ጠብቃ ያቆየች ናት:: ከዚህም ጋር በተለይ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር እንዳይጋጭ ተከባብሮ ለመኖር የሚችልበትን ትምህርት ስታስተላልፍ ኖራለች:: በመሆኑም በሃይማኖት ቢለያይም በጋራ ሀገር መከራውንም ደስታውንም በጋራ እየተሳተፈ በፍቅር ተሳስሮ በሰላም መኖር የሚገባው መሆኑን እየሰበከች ሁሉንም አስተባብራ ያኖረች ባለውለታ ናት:: ግራኝ መሐመድ አሥራ አምስት ዓመታት እሳት እንድዶባት ገዳማቷንና

www.ethiopianorthodox.org

አላነሣሣችም:: ይሁን እንጂ ያሁኑ ትውልድ ውስታዋን ያወቀ አይመስልም፤ ቢያውቅም ያስታወሰ አይመስልም:: ባለማስታወሱም በኒቅያና በቁስጥንጥንያ እንዲሁም በኤፌሶን ጉባኤ ተወግዘው ከተባረሩ ጠላቶቿ ጐን አቁሞ ሲያወዳድራት ገናና ስሟንም አዋርዶ ከታችኛው መሥመር ሲመዘግባት እየታየ ነው::

ዛሬ በዓለማችን ላይ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ አድገዋል መጥቀዋል በልጽገዋል ከመባላቸውም ሌላ የዲሞክራሲ ሥርዓት መሠረት መሆናቸው የሚነገርላቸው አገሮች እንኳ የየራሳቸው አፊሴላዊ ሃይማኖት እንዳላቸው ይታወቃል:: ለምሳሌ ኢጣልያ ካቶሊክ፣ ጀርመን ፕሮቴስታንት፣ ግሪክና ሩሲያ ኦርቶዶክስ፣ ሳውዲዓረቢያ እስልምና የየመንግሥታቸው ብሔራዊ ሃይማኖት ነው::

ኢትዮጵያም ከአራተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ብሔራዊ ሃይማኖቷ እንደሚታወቀው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መሆኑን የሚክድ አይኖርም:: ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ሁና የኖረችው በተአምራት ብቻ ሳይሆን በመሪዎቿም ጥንካሬና የሃይማኖት ጽናት ጭምር ነው::

ዛሬ ግን የግብጽና የሲቢያ የሲባኖስና የሶሪያ ክፉ ዕድል እየተፈታተናት ነው:: በፈተናውም ተደናግጣ የምትጨብጠውን አጥታለች:: በተለይም ኢትዮጵያዊቷ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሕልውናዋ ከኢትዮጵያ ሕልውና ጋር የተያያዘ በመሆኑ መስደጃ አጥታለች:: ወደ ኢጣልያና ወደ ጀርመን ወይም ወደ ሳውዲዓረቢያ እንዳትሰደድ የየራሳቸው ብሔራዊ ሃይማኖት ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ በመላ ታሪካቸው ሕልውናዋን ለማፍረስ ታሪኳን ለመደምሰስ የረጅም ዘመን ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ በተለያዩ ዐረፍተ ዘመናት በጠርነት ሲፈትኗት የኖሩ ናቸው::

ይህ እየታወቀ ዛሬ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለዘመናት ስትሰጥ የኖረችበት



ውለታ ተረስቶ ሦስት ሺህ ዘመናት በይዞታነት ስትገለገልባቸው ለነበሩ ቅዱሳት መካናት ጊዜ አገኘን በሚሉ መናፍቃን ካርታ እየተጠየቀች ነው::

ከሦስት ሺህ ዘመናት ይዞታ በኋላ ካርታና ፕላን ማቅረብ በእጅጉ ስለሚያስቸግር በዚህ ምክንያት ዓውደ ምሕረቷ፥ መካነ መቃብሯ የጥምቀትና የመስቀል በዓል ማክበሪያ ቦታዋ እንዲወሰድ መናፍቃን በሚሰጡት ደም አፋሳሽ ትእዛዝ ምእመናን ተንገላተዋል፣፣ እየተደበደቡም ታሥረዋል:: ለዚህም ምስክሮቹ የአርባ ምንጭ ምእመናን ናቸው:: እንግዲህ የዲሞክራሲ ትርጉም ኢትዮጵያዊቷን ቤተክርስቲያን ህልውና አልባ ማድረግ፥ ታሪኳን ማፈራርስ፥ እንደመናፍቃኑ አዛዦች አመለካከት የምእመናንን ሰላም ማደፍረስና ህብቷን መዝረፍ ይዞታዋን መንጠቅ ሆኗል::

እንዲህም ከሆነ መፍትሔው እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርስቶስ ብቻ ነው:: ይግባኝ ሰሚው ክርስቶስም ለአቤቱታ የተዘረጉ እጆቿን ተመልክቶ በሚፈርድባቸው ጊዜ ጠላቶቿ አይቀጡ ቅጣት እንደሚቀጡ የታመነ ነው:: ስለዚህ የፋሽስት ኢጣልያን ከዚያም በፊት የነበረውን የግራኝን ታሪክ ተመልክተው ከወዲሁ ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል::

የሚሠሩትን አለማወቅ የሚያስከትለው መዘዝ ብዙ ነው:: «የጅብ ችኩል ቀንድ ይነከሳል፤» እንዲሉ ቸኩለው በዲሞክራሲ ስበብ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማዳከም ጨርሶም ለማጥፋት የሚወስዱት እርምጃ ሁሉ ለማንም ለምንም አይበጅም:: የአፍሪካ ቀንድ ኢትዮጵያ ዛሬም እንደቀድሞው ወደፊትም እንደዛሬው የክርስቲያን ደሴት በመባል ጸንታ ትኖራለች እንጂ ይህን ስም የሚወርዘው የለም:: ምንእልባትም ቀርነ ሃይማኖቷን አፍልሰው ጎዳ እናደርጋታለን የሚሉ ካሉ ጉዳቱ በነሱ ላይ የሚከፋ መሆኑን መርሳት የለባቸውም::

www.ethiopianorthodox.org

በመሠረቱ ሰው የተፈጠረው ከተፈጥሮ ጓደኛው ጋር ተፋቅሮና ተባብሮ እግዚአብሔርን እያመሰገነ በሰላም ሲኖር ነው:: ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ መንግሥት በተለወጠ ቁጥር ኃይለኛው ደካማውን፣ ባለሥልጣኑ ተገዥ ወገኑን፣ ጊዜ አገኘሁ ብሎ እንዲያጠቃው አይደለም:: ይህንንም ኢትዮጵያውያን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ አንዱ ወድቆ ሁለተኛው ቢነግሥ በታሪካቸው ውስጥ ተከፋፍለው ሀገራቸውን ለጠላት አጋልጠው አያውቁም::

የሃይማኖት ልዩነትም አቃቅሯቸው ወይም አጋጭቷቸው እንደማያውቅ የዓለም ሕዝብ ምስክር ነው:: ምክንያቱም ኢትዮጵያዊቷ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያውያን በጥልቀት ያስተማረቻቸው ተፋቅሮና ተባብሮ መኖርን፣ ተካፍሎ መብላትን በመከራም ሆነ በደስታ መረዳዳትን፣ ወንድማማችነትን እና ለጋራ ሀገር በጋራ መቆምን ነው:: በዚህም ጠባያቸው መላው ዓለም ሲያደንቃቸው ኖሯል:: ከቀድሞ ጀምሮ ከፋፍሎ ለመምታት ሲያደቡ የኖሩ ጠላቶቻቸውም ጊዜ አገኘን ብለው በመካከላቸው ጣልቃ ለመግባት ተፍጨርጭረዋል፤ ነገር ግን መግቢያ ቀዳዳ አላገኙም:: ይህም የሆነው በኢትዮጵያዊቷ ቤተ ክርስቲያን አርቆ አስተዋይነት ነው:: ይሁን እንጂ ጠላቶቿ ባርቆ አስተዋይነቷ አጽንታ ያቆየችውን አንድነት አልፈለጉትም:: የአንድነት መሠረት የሆነውንም ትምህርት ለኤፌሶን ሰዎች ከተሰጠው ትምህርት በመነሣት «እግዚአብሔር አንድ ነው፥ ሃይማኖትም አንዲት ናት፥ ጥምቀትም አንዲት ናት፤» እያለች በማስተማር ሁሉንም አስባስባ በሃይማኖት አንድ ለማድረግ ያደረገችውን ጥረት አጣጥለውታል::

ቀድሞም ቢሆን ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ቃል ሲያስተምር ትምህርቱን ካልተቀበሉት ውስጥ አንዳንዶቹ ዓላማውን ለማደናቀፍ ታግለውታል:: በምእመናን ላይ መሰናክል እየፈጠሩ በእጅጉ ስለአስቸገሩትም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አይቀጡ ቅጣት ቀጥቷቸዋል:: ከነዚህም ውስጥ አንጥረኛው አለእስክንድሮስና ጠንቋዩ በርያሱስ ተጠቃሾች ናቸው:: 2ኛ ጢሞ 4፥14፣ የሐዋ. ሥራ 13፥7-12



ከቅዱሳን ሐዋርያት በኋላም መሠረተ እከይ ከሆነው ከአርዮስ ጀምሮ ስሕተቱ እንደመናፍቃኑ ቁጥር እየበዛ በመሔዱ ልብወለድ በሆነ ፈጠራ ሃይማኖትን የሚፈበርኩ ሰዎች ብዙዎች ሆነዋል:: በዚህም ምክንያት ከእርስ በርስ ጭቅጭቅና ንትርክ አልፎ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙ ወገኖች ደም እስከ መፋሰስ ደርሰዋል:: በየጊዜው የምናየውና የምንሰማው ክስተት እጅግ አስገራሚና አሳዛኝ ትርዒት ነው:: ለዚህም በአየርላንድ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት መካከል ሲካሄድ የቆየውን የትጥቅ ትግል መጥቀስ በቂ አስረጅ ነው:: ከዚህ ችግር የተነሣ ግን ክርስቲያኖች እንዳይለያዩ ለማቀራረብና አብሮ ለመሥራት እንዲቻል ኅብረት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በጄኔቫ ተመሠረተ:: የዚህ ማኅበር ዋና ዓላማ በአብያተ ክርስተያናት መካከል ጥላቻና አለመግባባት ተወግዶ አንዱ የራሱን ጠብቆ የሌላውን አክብሮ በመተባበር በመቀራረብና በአንድነት እየሠሩ እየተረዳዱ መኖር ነው::

አንዱ የአንዱን በግ መስረቅም በቻርተሩ ወንጀል እንደሆነ ተደንግጓል:: የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መንፈስ ይኸን ቢመስል ዛሬ ግን የሚሠራው ሌላ ነው:: አንዱ የአንዱን በግ ለመንጠቅ የሚያደርገው ሩጫ ከፍ ያለ ነው:: በተለያዩ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ወገኖች መካከል በሚካሄደው ጦርነት ለደም መፋሰስ ምክንያትም ይህ መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባዋል:: በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በተለያየ አቅጣጫ በጐቿን እየተነጠቀች ነው፤ አሁንም በመነጠቅ ላይ ትገኛለች:: ከዚህም አልፎ ኢትዮጵያዊው የዜማ ደራሲ በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ መዘመር ከጀመረበት ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የማንነቷ መገለጫና ልዩ መለያዋ የሆነውን ጥንግ ድርብ፣ መቋሚያ፣ ጸናጽል፣ ከበሮ በማን አለብኝነት ዲሞክራሲን ጥግ በማድረግ ነጥቀዋታል:: ለዚህም ምስክሩ ከየካቲት 23-25/

www.ethiopianorthodox.org

ጥግ በማድረግ ነጥቀዋታል። ለዚህም ምስክሩ ከየካቲት 23-25/ 1992ዓ.ም የተካሄደውን የፕሮቴስታንት ማኅበር ጉባኤ በተመለከተ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ለተከታታይ ቀናት ባስተላለፈው ማስታ ወቂያ ላይ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለ1500 ዘመናት የተጠቀመችበትን አንጡራ ሀብቷም የሆነውን ጥንግ ድርብ ለብሰው፥ የማያውቁበትን መቋሚያ ጸናጽል ይዘው የቤተ ክርስቲያኗ ሳይሆኑ ለማስመሰል ያደርጉት የነበረውን የታሪክ ቅሰጣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መስተዋት የተመለከቱ ምእመናን በሙሉ በኃዘን ከመገነዛቸውም በላይ ኀሊና ቸውን ያቆሰለ አሳዛኝ ትዕይንት ነበር። የዴሞክራሲ ትርጉም የአንዱን እንጡራ ሀብት ሌላው የራሱ አስመስሎ ሊጠቀምበት የሚገባ ነው የሚል አልነበረም።

ነገር ግን የሰው ልጅ ባለውና በተሰጠው ሀብት የማይረካ፥ ለከንቱ ምኞቱ ወሰንና ድንበር የሌለው ከመሆኑ የተነሣ የራሱ ያልሆነውን ለማግኘት ሲል እንኳን በዲሞክራሲ ስም በእግዚአብሔ ርም ስም እያታለለ ቤተክርስቲያንን ቢዝነስ መሥሪያ ወይም የንግድ መናኸሪያ ለማድረግ ሲጥር ይታያል። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ አስፈሪው አደጋ ይህ እንደሚሆን እገምታለሁ።

ከላይ እንደተገለጸው ቤተክርስቲያን አንጡራ ሀብቷን በጠ ላቶቿ ስትነጠቅ የድረቡልኝ ጩኸት ለማሰማት አንኳ አፍራ በዝምታ አልፋዋለች። እንዲህም ከሆነ ነገ ተነገ ወዲያ ገፍትረው ሲጥሏትና ሲረግጧት መስማትና ማየት ለኛ ከምንም በላይ የከበደ አደጋ ነው። ነገር ግን የተፈጥሮ ግዳጅ ሆነና ሰሎሞን እንደ ተናገረው ጆሮ የማይበማው ነገር ዓይን የማያየው ግዙፍ ፍጡር የለም።



# ምዕራፍ ስምንት

# እናቶች በሕፃናት ላይ

በዘመናችን በዲሞክራሲ ሰበብ የሰማነውና ያየነው ከላይ የተጠቀሰው ብቻ አይደለም። ሌላም ኀሊናችንን የሚያቆስል ብዙ ነገር አለ። ከብዙውም ክብደት ያለው ከእናቶች አንደበት ይሰማ የነበረው አሳፋሪ ነገር ነው። እንደሚታወቀው በቀድሞ ጊዜ እናቶች ለሕፃናት የርኅራኄ ምንጭ እንደነበሩ የሚነገር ሲሆን ባሁኑ ጊዜ ግን በሕፃናት ላይ የሚያሳዩት ጭካኔ ሰብአዊ ተፈጥሮን የሚያስጠላ ሆኗል።

አስከዛሬ ድረስ ውስጥ ለውስጥ ይሠሩት የነበረውን የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ባሁኑ ጊዜ ወቃሽና ከሳሽ ሳይኖርባቸው በይፋ ለመፈጸም የሚያስችላቸውን ውሳኔ ለማግኘት በቅድስት ሀገራችን ርእሰ ከተማ ያሰሙት የነበረ ጩኸት እጅግ የሚያስደነግጥ እግዚ አብሔርንም የሚያሳዝን ያልታሰበ ክስተት ነበር።

ይኸውም በሥጋዊው ዓለም እንኳ መንፈሳዊት የክርስትና ደሴት እየተባለች በምትጠራው ቅድስት አገራችን በቅርቡ ከእናቶቻችን አንደበት ልጆቻችንን ለመግደል ውርጃ ይፈቀድልን ተብሎ የተሰማው እንግዳ ዜና ነው። ይህም እጅግ አስደንጋጭና አስገራሚ ነበር። ለሰው ልጅ የሕይወት ዋስትናው ሕገ እግዚአብሔ ርን መጠበቅ እንደሆነ ይታመናል። እግዚአብሔር አምላክ በአምሳለ ንጉሥ በደብረ ሲና ተገልጾ ለሊቀ ነቢያት ሙሴ በመለኮታዊ ጣቶቹ ከሠራቸው አሥርቱ ሕግጋት መካከል «አትግደል፤ አታመንዝር፤» የሚሉ ሕግጋት ይገኙበታል። ይህን የሰማይ የምድር ጌታ የቅዱስ እግዚአብሔርን ሕግ በመጣስና ትእዛዝ በማፍረስ ጽንስ ማስወረድ/ውርጃ/ በሕግ ይፈቀድልን፤ ሕጋዊነቱ ይጽደቅልን የሚል የጭካኔ ቃል፦ የርኅራኄ ምንጭ ከሆኑ እናቶች ተሰምቷል። ይህ ያለምንም አስገዳጅ ኃይል በራሳቸው ፈቃድ በአደባባይ በኢ

www.ethiopianorthodox.org

ትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ከአሕዛብ አገሮች ተሞክሮ ጋር እያነጻ ጸሩ ሲያስተላልፉ የተደመጠው ኀሊናን የሚሰቀጥጥ ዜና፤ ኢትዮጵያውያት ደጋግ እናቶችን ምን ነካቸው?» እንዲህ ያለውን ሄሮድሳዊ ጠባይ በሕፃናት ላይ ከወዴት አመጡት?» የሚያሰኝ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ እናቶች በጨካኝ ንጉሥ እንኳ ታዘው ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍርሃትና ፍጹም እምነት እንዲሁም ለሕፃናት ከነበራቸው ርኅራኄ የተነሣ የንጉሡን ትእዛዝ ጥሰው ከማኅፀን የሚወጡ ሕፃናትን ማዳናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቧል።

ከልዑል አምላካችን ከእግዚአብሔር ጋር ከአምስት መቶ ጊዜ በላይ ቃል በቃል የተነጋገረው ሊቀ ነቢያት ሙሴ በጻፈው መጽሐፍ በኦሪት ዘጸአት በምዕራፍ 1፥15-22 ያለውን እንመልከት ቃሉም የሚከተለው ነው። «የግብፅ ንጉሥ አንዲቱ ሲፓራ ሁለተኛይቱም ፉሐ የሚባሉትን የዕብራውያንን አዋላጆች እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። እናንተ የዕብራውያንን ሴቶች ስታዋልዱ ለመውለድ እንደደረሱ ባያችሁ ጊዜ ወንድ ቢሆን ግደሉት ሴት ብትሆን ግን በሕይወት ትኑር። አዋላጆች ግን እግዚአብሔርን ፈሩ የግብፅም ንጉሥ እንዳዘዛቸው አላደረጉም። ወንዶቹን ሕፃናትንም አዳኑአቸው የግብፅም ንጉሥ አዋላጆችን ጠርቶ ለምን እንዲህ አደረጋችሁ? ወንዶቹን ሕፃናትንስ ለምን አዳናችሁ፤» አላቸው። አዋላጆችም ፈርዖንን «የዕብራውያን ሴቶች እንደግብጽ ሴቶች ስላልሆኑ እነርሱ ጠንካሮች ናቸውና አዋላጆች ሳይገቡ ስለሚወልዱ ነው፤» አሉት። እግዚአብሔርም ለአዋላጆች መልካም አደረገላቸው። ሕዝቡም በዛ እጅግም ጸና አዋላጆችም እግዚአብሔርን ስለፈሩት ታላላቅ ነገር አደረገላቸው

እዚህ ላይ እናቶች ለሕፃናት ምን ያህል ርኅራኄ እንዳላቸውና በሕፃናት ሞት የሚሰማቸውን ጻር የሌለው ኃዘንና ለቅሶ መግለጽ ይበልጥ ጥሩ ትምህርት እንደሚሰጥ እናምናለን። በቅዱስ መጽሐፍ ላይ እንደተመዘገበው እስራኤላውያን በረሃብ ምክንያት ወደ ግብጽ ወርደው ብዙ ዘመን በተድላ በደስታ ከኖሩ በኋላ የሚያስጨንቅ የሚያስለቅስ መከራ አገኛቸው። ከላይ የተገለ



ጸው ከፉ ንጉሥ ፈርዖን ተነሣባቸው። ለእግዚአብሔር በተመረጡ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ የመከራ አገዛዝ አጸናባቸው። የበደልና የግፍ መርግ ባላያቸው ጫነባቸው። ከሁሉ እጅግ የከፋው ከባድ መከራ ደግሞ በሴት ልጅ ላይ የሚደርሰው ግፍ ነበር። ሴት ልጅ በምጥ ተይዛ እንኳ የሚያላርፉትን አለማግኘቷ ከሁሉም በላይ የሚሰቀጥጥ ዘግናኝ ግፍ ነው።

የጸነሱ ሴቶች ጭቃ እየረገጡ ጽንሱ ጭንጋፍ እየሆነ እንዲወጣ እየተፈረደባቸው ተሰቃይተዋል። ብዙ ሕፃናትም በዚህ ምክንያት ለሞት ተዳርገዋል። ከዚህ የተነሣ ራሔል የተባለች እስራኤላዊት እናት ለጡብ ጭቃ እየረገጠች ሳለ በምጥ ተይዛ ብትወልድ «ከጭቃው ጋር እርገጭው፤» ተባለች። በዚህ ምክንያት ከዚህ መከራ ሊረዳት ከእረመኔው አገዛዝም ነፃ ሊያወጣት ወደሚችል ወደ እግዚአብሔር አለቀሰች። እንባዋን በእፍኟ ሞልታ ወደ ሰማይ ረጨች። ይህንንም የራሔልን መከራና ሰቆቃ ነቢዩ ኤርምያስ «ድምፅ በራማ ተሰማ፥ ለቅሶና ብዙ ዋይታ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፥ መጽናናትም አላገኘችም፤» በማለት ገልጾታል። ማቴ.2፥18፣ ኤር 3፥15

ይህን የመሰለ የእናቶችን ልባዊ ርኅራኄ ማን ወሰደው? ለሕፃናት እንዲህ የሚንሰፈሰፍ የወላድ አንጀት ዛሬ ወዴት ሔዶ ነው ሕፃናትን መግደል ይፈቀድልን የሚል ጥያቄ የተነሣው? ለሕፃናት ከእናት በላይ ማንም የላቸውም። እናቶችም እንደ ራሔል ያለውን ርኅራኄ ለሕፃናት በልባቸው መቅረጽ ይገባቸዋል። የሕፃናት አሳዛኝ ገጽታ በልጅ ፍቅር የሚንሰፈሰፈውን የወላድ አንጀት ቀርቶ የልብ ጥንካሬ ያላቸውን ሰዎች ጭምር እጅግ የሚያሳዝን ነው። ይህንንም በተመለከተ ወደ አንድ ሥዕላዊ ታሪክ በመውሰድ የሚከተለውን ታሪክ ለመተረክ እወዳለሁ።

አንድ የፋርስ ንጉሥ በጠና ታመመ፤ ባለመድኃኒቶችም ሊያድኑት አልቻሉም። ንጉሡም በማዕድ የሚመገበው አብሮት የሚኖር አንድ ሥራቤኛ /መድኃኒት አዋቂ/ ሰው ነበረው። ንጉሡ «ያንተ ከእኔ ጋራ መኖር ጥቅሙ ምንድን ነው ከዚህ በሽታ ካልፈወስከኝ በስተቀር እገድልሃለሁ፤» አለው። ጠንቋዩም በተንኮል፡

www.ethiopianorthodox.org

- «ንጉሥ ሆይ የምነግርህን ካደረግህ ትድናለህ፤» አለው:: ንጉሡም «ምንድነው የምትነግረኝ?፤» አለው በዚህን ጊዜ ጠንቋዩ፤ «ለአባትና ለእናቱ አንድ የሆነ ልጅ አስፈልገህ እናቱ እሥራ ትያዘውና አባቱ ይረደው፤ በእርሱ ደም ትድናለህ፤» አለው:: ጠንቋዩ እንዲህ ማለቱ፤ አንደኛ. «አላውቅም ካልኩ ንጉሡ ይገድለኛል፤» ሁለተኛ. እንዲህ ያለውን ሥራ መሥራት ንጉሡ ይፈራል ፤ ሦስተኛ. «ጨክኖ ልጁን ለሞት አሳልፎ የሚሰጥ አይገኝም፤» ብሎ አስቦ ነው:: ንጉሡም በሚገዛው አገር ውስጥ ፈልገው በአንድ ሺህ የወርቅ ዲናር ሕፃን ልጅ ይገዙለት ዘንድ አሽከሮቹን አዘዘ:: በዚያችም አገር አንድ ልጅ ያላቸው ድሆች የሆኑ ባልና ሚስት ነበሩ፤ እነርሱም ይህን ነገር ሰምተው ልጃቸውን ወደ ንጉሡ ወሰዱ:: ልጁም እያለቀሰ «እኔ በፈጠረኝ በእግዚአብሔር ላይ ተማምኛለሁና እርሱ ያድነኛል፤» ይል ነበር:: እናቱም አጥብቃ አሠረችው፤ አባቱም ሊያርደው በንጉሡ ፊት ሾተሉን መዘዘ:: በዚህን ጊዜ ሕፃኑ ሀይኑን ወደ ሰማይ ሰቅሎ ከንፈሩን ያንቀሳቅስ ጀመረ:: ይህ የሕፃኑ አሳዛኝ ገጽታ የንጉሡን ልብ ነካውና ርኅራኄ አሳደረበት:: ንጉሡም በዚህ ምክንያት እስቲ አንድ ጊዜ ተዉት አለ:: ከዚያም «ሕፃኑን ምን እያልክ ነው?» ብሎ ጠየቀው:: ሕፃኑም «ለልጅ ማዘን መራራት የሚገባቸው ወላጆች ነበሩ:: እነሱ ግን አሳልፈው ሰጡኝ ደሀ ተበደለ ፍርድ ጎደለ፤ የሚል ንጉሥ ነበር፤ አንተም ስለጨከንከብኝ ከእናንተ ዘንድ ምንም በጎ ነገር እንደማይገኝ ስለተረዳሁ፤ የሰማይ የምድር ንጉሥ የሆነውን አምላኬን ይግባኝ እየጠየኩ ነው» በማለት መልስ ሰጠ:: ከሕፃኑም ድንቅ ምስክርነት የተነሣ ንጉሡ በእግዚአብሔር አመነ:: አባ ዳንኤል በተባሉ መነኩሴም ተጠምቆ ሰመ ክርስትና እና ሀብተ ወልድና እንዳገኘና ከደዌው እንደተፈወሰ ኅዳር 14 ቀን በሚነበበው ስንክሳር ላይ ተመዝግቦ ይገኛል::

እንግዲህ ይህ ሁሉ እውነታ ተዘንግቶ በሀገረ እግዚአብሔር በቅድስት ኢትዮጵያ፡- ርኵሰት የሆነውን የዝሙት ኃጢአት በመሥራታቸው የኖኅ ዘመንን ትውልድ በንፍር ውኋ ቀቅሎ ከገጸ ምድር ያጠፋውን፣ ሰዶምንና ገሞራን በእሳትና ዲን እንዲቃጠሉና የአመድ ክምር ሆነው እንዲቀሩ ያደረገውን እግዚአብሔርን ከሚያስቆጣ ኃጢአት በመራቅ በቅድስና ሕይወት ለዘለዓለማዊ ክብር መብቃት ይገባ ነበር:: ነገር ግን ዛሬም ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸውን አዋርደው ዘለዓለማዊ ጥቅማቸውን ባለማወቅ ኃጢአት እየሠሩ እግዚአብሔርን በማሳዘን ለሰላም ለሕይወት ለደስታ የተፈጠረላቸውን ጊዜ ከፍርድ በታች አውለው ለኃዘን ለመከራና ለትካዜ በመዳረግ ላይ ይገኛሉ:: እነሆ ዛሬ መድኃኒት የሌለው+ ብዙ ትውልድ እየቀሰፈ የሚገኘው÷ ማንንም የማያፍር÷ ከመካከላችን የለውን ልጅ የሚመነጥረው በሽታ ራሱ የዝሙት ውጤት አይደለምን? መድኃኒቱስ ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ ብቻ አልነበረምን? እንግዲህ ይህ እየታወቀ እግዚአብሔ ርን ለማሳዘንና ለማስቆጣት የዝሙት ኃጢአትን ከነፍስ ግድያ ጋር በማያያዝ «በሕግ ይፈቀድልን!» ብሎ መጠየቅ እጅግ የድፍረት ኃጢአት ነው:: ከእናቶችም አንደበት ሲሰማ ይበልጥ የሚያሳፍር ነው:: ከመወለዱ በፊት በማኅፀን እያለም ሆነ ከተወለደ በኋላ ያለው ነፍስ እኩል ነው:: ከማኅፀን ጀምሮ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ጥበቡ የሚጠብቀውን ገንዘቡ የሆነውን ፍጥረት በጭካኔ መግደል ጨካኙ ሄሮድስን መሆን ነው::



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ወራት በገሊላ ነግሦ የነበረው ንጉሥ ሄሮድስ ይባል ነበር:: ሄሮድስ ለምታልፍ መንግሥቱ ካለው ሥጋት የተነሣ ለማንም ርኅራኄ የሌለው ክፉ ጨካኝ ሰው ነበረ::

ስለ ክፉ ሥራውም የቅርብ አማካሪው ሰይጣን በመሆኑ ከዕለታት አንድ ቀን «ሄሮድስ ሆይ÷ ያልተረዳኸው ነገር አለ:: እንዳስረዳህም ከፈለግህ እነሆ የአንተን መንግሥት የሚነጥቅና የኔን ሥልጣን የሚሽር ሕፃን ተወልዷል:: ያንንም ሕፃን በተናጠል አታገኘውም በገሊላና በናዝሬት በኢየሩሳሌምና በቤተልሔም ዙሪያ የሚገኙትን የዓመት፣ የዓመት ከመንፈቅ፣ የሁለት ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ሕፃናት በአዋጅ አሰብስበህ አስፈጃቸው፤ ምንአልባትያ ሕፃን ከነዚያ አንዱ ስለሚሆን አንተ ከሥጋት ትድናለህ እኔም እፎይታ አገኛለሁ» ሊል መከሮታል:: እርሱም እውነት መስሎት

www.ethiopianorthodox.org

«ለእናት ለአባታቸው ርስት ጉልት ልብስ ቀለብ እሰጣለሁ፤ ሕፃናቱንም በማር በወተት በፍትፍት አሳድጌ ለሹመት አበቃለሁ ልጆቻችሁን ሰብስባችሁ አምጡልኝ!» በማለት የማታለያ አዋጅ አወጀ:: እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ጥቅም ታገኛለህ ሲሉት ሳያስቶ መሽቀዳደም ልማድ ነውና እንኳን ልጅ ያላቸው የሌላቸውም ካላቸው እየተዋሱ ሰብስበው አምጥተውለት አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ ሕፃናት በሰይፍ አስፈጅቷል:: የሕፃናቱ ደም እንደውኃ ፈሰሷል:: እናቶች በዕንባ ተራጭተዋል:: ዘጠኝ ወር የተሸከሙ ማኅፀናት በኃዘን ተኮማትረዋል:: ዛሬ ግን በተቃራኒው እናቶች በሕፃናት ላይ የሞት ፍርድ እናስፈርድ እያሉ ናቸው:: ይህም የዓለም ፍጻሜ መቃረቡን የመጨረሻ ክፉ ዘመን መሆኑን የሚያሳይ ነው:: ያን ጊዜ ሄሮድስ ቢጨክን ባልወለደ አንጀቱ ነው:: የወለዱ እናቶች የወላድ አንጀታቸው ጨክኖ «ልጆች ይገደሉ» ካሉ ጭካኔያቸው ከሄሮድስ ጭካኔ በላይ በመሆኑ የዓለም ክርስቲያኖች ሙሾ እያወጡ የሚያለቅሱበት በእጅጉ የሚያሳዝን ዘመን ነው::

ይህ ተግባር በደሙ ያነጻንን እና በሞቱ ያዳነን መድኃኔዓለም ክርስቶስን ማሳዘን ብቻ ሣይሆን ፈራጅነቱንም መካድ ነው:: ቤተክርስቲያን ይህ ሲፈጸም ዝም ብላ አትመለከትም:: ከተመለከተች መንፈሳዊ ሥራዋን አቁማለች ማለት ነው:: እኔ ከአባቶቼ ከሐዋርያት በወረስኩት መንፈሳዊ ሥልጣነ ክህነት ይህን የጽንስ ማስወረድ ተግባራት ሕጋዊ እንዲሆን የቀረበውን ጥያቄ ተቃውሜዋለሁ፤ እንዳይፈጸምም አጥብቄ አወግዛለሁ:: ይህም ዓይነቱ እንግዳ ነገር ሁሉ በዲሞክራሲ ጥግ ወይም ሽፋን የሚከሰት ነው:: በዲሞክራሲ ያለው ነፃነት እኮ የሰውን ልጅ ክብር የማይነካ የማንንም መብት የማይጋፋ የሰው ሁሉ ሰብአዊ መብት ተከብሮ ሁሉም በእኩልነት እንዲኖርና ለሰው ልጅ ፍትሕ እንዲሰፍን የሚያደርግ ሥርዓት ነው እንጂ፤ አንዱ የሌላውን ሀብት እንዲዘርፍ ወይም ደግሞ አገርንና ትውልድን የሚጎዳ ኃጢአት እንዲሠራ የሚሰብክ አይመስለኝም:: በመሠረቱ ሰው በአርዓያ ሥላሴ የተፈጠረ ነው:: ለባዊ ነባቢ ሕያውም ነው፤ ስለሆነም የወደደውን በመምረጥ የመሥራት ነፃነት ተሰጥቶታል::



ይህም በቅዱስ መጽሐፍ አስቀድሞ የተነገረ እውነት ነው:: ታዲያ በጎውንና ክፉውን የሚለይ አእምሮ ያለው እንደመሆኑ መጠን የሚጠቅመውን በመምረጥ መሥራት አለበት::

ለምሳሌ፦ ለአባታችን ለአዳም ከአንዲት ዕፀ በለስ በቀር በዓለም ላይ ያለው ሀብት ተሰጥቶት ነበር:: ነገር ግን አንዲቷን ዕፀ በለስ «አትብላ!» የሚል እምላካዊ ሕግ ተደነገገለት:: ይህንንም ሕግ ቢጠብቀው ሕይወት ባይጠብቀው ሞት የሚያስፈርድበት መሆኑ ተነገረው:: ነገር ግን ከንቱ ምኞቱ ድፍረት ሰጥቶት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ:: በመተላለፉም ከሕይወት ወደ ሞት ከክብር ወደ ሃሳር ደረሰ:: ዛሬ ለእኛም ቢሆን የመዳንም ሆነ የመጥፋት ምርጫ በእጃችን ላይ ነው:: «እሳትና ውኃ ሞትና ሕይወት በፊትህ አኑሬአለሁ በፈለከው እጅህን ስደድ» የሚል ቃል ስለተነገረን ምርጫው የእኛ ነው:: ሲራክ 15፥16

ዛሬ ያለው ትውልድ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም የታሪክ ባለዕዳ ሁኗል:: ምክንያቱም ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚያርቅ ተግባር መምረጥ ይቀናዋልና ነው:: በዚህ የመጨረሻ ዘመን በንስሐ ሕይወት መታደስ ሲገባው ከዕለት ወደ ዕለት አዳዲስ ኃጢአት እየፈጠረ በመሥራት ጥፋቱን ወይም ቅጣቱን እያፋጠነ ነው:: ከሰው ልጅ ኃጢአትና በደል ብዛት የተነሣ ዓለማችን እጅግ በርካታ በሆኑ ችግሮች ታጥራለች:: በጎሣ ግጭቶች በተለያዩ ችግሮች በጦርነት ተወጥራለች:: ሁሉን አስተባብሮ የሚይዘው ፍቅር ቀዝቅዟል:: የኑሮ ውድነት እጅግ አሻቅቦአል:: ገንዘብ ዋጋ አጥቷል፤ ብዙ አስከፊ ገጽታዎች እየተከሰቱ ነው:: እግዚአብሔርም ከሰው ኃጢአት ብዛት የተነሣ የምሕረት እጁን እየሰበሰበ በድርቅ ምክንያት ብዙ ወገኖቻችን በተለያዩ ጊዜያት በረሃብ እየተጎዱ ነው::

አሁንም ቢሆን መሐሪና ይቅር ባይ፣ ቸር ሰው ወዳጅ ወደሆነው አምላካችን ወደ እግዚአብሔር በንስሐ እንመለስ:: ምንም እንኳ በእንስሳዊ ግብር ተሸንፈን ከጽድቅ አንባ ብንኮበልልም «እንደወጡ ይቅሩ!» ሳይል «ወደ እኔ ተመለሱ!» እያለ በየጊዜው የርኅራኄ ጥሪውን አስተላልፎልናል:: ዛሬም ሆነ ቀድሞ በስሕተት ጎዳና ለሚገኙ ሁሉ ይህ ጥሪ እንዲደርሳቸው ለማድረግ

www.ethiopianorthodox.org

መልእክተኞቹን በብዛት እስነሥቶ በየእቅጣጫው ልኳል። ከተላኪ ዎቹም አንዱ በዐራት ሺህ ሰባት መቶ ዓመተ ዓለም የነበረ ኢ ዩኤል የተባለው ነቢይ ነው። ኢዩኤል የሮብዓም ልጅ እብያ በነገሠበት ዘመን የነበረ ነቢይ ሲሆን በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ ሲያስተላለፍ የሚከተለውን ቃል ተናግሯል። «አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጽም ልባችሁ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደኔ ተመለሱ፤ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ቁጣው የዘገየ ምሕ ረቱም የበዛ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ፤» በማለት መልእክቱን አድርሷል። ኢዮ.2፥12 እንግዲህ ነቢዩ ገልጾ እንደተናገረው ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት በሠሩት ኃጢ አት ባደረጉት ስሕተት ማዘንና መጸጸት ራስንም በጾም መግዛት መቻል ነው። በተለይም በልቡና ውስጥ ያለ የቂም ሰቀልን ስንኮፍ ቀደው ሳያወጡ፥ በኃጢአት ያረጀውን ሰውነት በልቅሶና በዋይታ በእውነተኛ ንስሐና ቀኖና ሳይለውጡ፥ አፍአዊ ልብስን በመቅደድ አመድ ላይ እየተንከባለሉ በመስገድ ፦ «የእግዚአብሔርን ጥሪ አክብሬያለሁ፤ የነቢዩን መልእክት ተቀብያለሁ፤ ከዚህም የተነሣ ወደ እግዚአብሔር ተመልሻለሁ፤» ማለት አይቻልም። አለመቻሉንም «ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤» ያለው ቃል ይወስነዋል። በዚህ አኳኋን ኢዩኤል መልእክተኛ ሆኖ የእግዚአብሔርን ቃል በወቅቱ ለእስራኤል ሲያ ስተላልፍላቸው ጾምን ለይተው እንዲጾሙ፥ ሕፃናት ሳይቀሩ ስቀኖና እንዲ ተባበሩና ካህናትም እያለቀሱ እግዚአብሔርን በጸሎት እንዲለምኑ አዝዟቸዋል። ወደ እግዚአብሔር የሚመለ ሱበትንም መንገድ በትክክል መርቷቸዋል። (ኢዮ.2፥15) እነር ሱም ባመለከታቸው መሠረት ወደ እግዚአብሔር በለተመለሱ እግ ዚአብሔርም በምሕ ረት ወደ እነርሱ ተመልሶ ፍላጎታቸውን አሟ ልቶላቸዋል። ጠ ላቶቻቸውንም አሳዶ እንደሚያጠፋቸው ቃል ከመ ግባቱም በላይ የክረምቱንና የበልጉን ዝናም በወቅቱ እያዘነመ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ እንዳች ሳያሳጣ መግቧቸዋል። ፊጽሞም ራርቶላቸዋል። ለዚህም ነቢዩ «እግዚአብሔርም ስለምድሩ ቀና ለሕዝቡም ራራ ለት፤» ቢል መስክሯል። ኢዩ.2 ቁ18። በእርግጥም ስለራራላቸው ሙሉ የተስፋ ቃል በጥቷቸዋል። ተስፋውም «እኔ በእስራኤል



መካከል እንዳለሁ እኔም አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደሆንኩ፥ ከኔም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ታውቃላችሁ፤ ሕዝቤም ለዘለዓለም አያፍርም የሚል ነው» ኢዩ2 ቁ 27። ይህንንም የተስፋ ቃል ለማግኘት ምክንያት የሆናቸው የኢዩኤል ስብከትና የንስሐ ጥሪ ነው። ኢዩኤል ልዑል እግዚአብሔር ከመዓት ወደ ምሕረት ተመልሶ ፍጥረቱን ይቅር የሚለው በጾም በጸሎት በልቅሶና በዋይታ ስፍጹም ንስሐና ቀኖና መሆኑን ስለተረዳ «ቀድሱ ጾመ ወስብኩ ምሕላ፦ ጾምን ለዩ ምሕላንም ያዙ» እያለ አጥብቆ አውጇል፤ ምዕ.2፥15። አዋጁንም በተግምባር ከፈጸሙ በኋላ እግዚአብሔር ከመዓት ወደ ምሕረት ተመልሶ «ሕዝቤ ለዘለዓለም አያፍርም፤» ብሎ የተስፋውን ቃል ሊሰጣቸው ችሏል። ኢዩኤልም ይህንን አይቶና ሰምቶ ከመደሰት ጋራ በመንፈስ ረድኤት እየተቃኘ ወይም እየተጉበኘ ዓለም ሁሉ የሚደሰትበትን ተስፋ ተፈጻሚነት ባለው ትንቢት ቁልጭ አድርጎ ተናግሯል። «መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፤ ጐበዛዝቶቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሮቼ /ባሪያዎቼ/ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ፤» በማለት እግዚአብሔር የተናገረውን መልእክት አስተላልፏል። ኢ ዮ.2፥28 እንዲህ አድርጎ እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚነሡ ማለትም በሃይማኖትና በቀና መንፈስ በንስሐ ዝግጁ ሆነው ለሚገኙ ሁሉ የእግዚአብሔ ር ቅዱስ መንፈስ ሲሰጥ እንደሚኖር አረጋግጧል። በዚህም አኳኋን ተልዕኮውን ከፈጸመ በኋላ ለክርስቶስ ልደት ስምንት መቶ ዓመት ሲቀረው ጥቅምት 21 ቀን ዐርፏል። ትንቢ ታዊ ቃሉም አንድ በአንድ ተፈጽሟል። እንግዲህ ከዚህ በላይ በተመለከትነው መሠረት ባጭሩ ልናስገነዝብ የምንወደው ነገር ቢ ኖር እስራኤል በቃሉ ተመርተው ሲመለሱ እነርሱ ለመዳን እግዚ አብሔርም ለማዳን የተገናኙበት ድልድይ ንስሐ መሆኑን ነው። ንስሐ የረከሰው ባልተቀደሰበት፥ ያረጀው ባልታደሰበት ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ተብሎ ዓለም በሚጠራበት ዘመን እስራኤልን በማያጠራጥር መንገድ ከእግዚአብሔር ጋራ ያገናኛቸው መሆኑ ተረጋግጧል። እንዲህም ከሆነ ዛሬም ቢሆን ዘወትር በኃጢአት የምንጠቃ ሁሉ ልንጠቀምበት ያስፈልጋል። ምንም እንኳ ነቢዩ «በወንዶችና በሴቶች ባሮች ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ አለ እግዚ

www.ethiopianorthodox.org

አብሔር» ብሎ የተናገረልን ትንቢት ተፈጽሞ መንፈስ ቅዱስ ቢያድርብንና በልጅነት መዓርግም ከእስራኤል በልጠን ብንገኝም፥ መንፈስ ቅዱስ ሳይለየን ልጅነታችን ጸንቶ ሊኖር የሚችለው ከክህደት ርቀን ከኃጢአት በንስሐ ተለይተን የተገኘን እንደሆነ ነው። ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ሲጽፍልን «በጸናችሁ ጊዜ እናንተን ያከበሩበትን መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑት፤ የሚያሳዝነውን ነገር ሁሉ ብስጭትንና መራገምን ሁሉ ጠብንና ስድብን ክፉ ነገር ሁሉ ጋራ ከእናንተ አርቁ፤» ብሏል። ኤፌ.4፥30። በዚህም ማስጠንቀቂያ መሠረት ከኃጢአት ርቀን ከክፉ ሥራ ሁሉ ተከልክለን የምንኖር ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ለሰከንድ ያህል እንኳ ሳይለየን እንደሚኖር አንጠራጠርም። ነገር ግን ከዐራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰውነታችን ኃጢአት የሚስማማው ደካማ በመሆኑ ደክመን በሠራነው ኃጢአት ሳናሳዝነው አልቀረንም። ምንም እንኳ ኤልያስ እግዚአብሔርን «ብቻዬን ቀረሁ፤» ባለው ጊዜ በአል የተባለውን ጣዖት ያላመለኩትን ሰባት ሺህ ሰዎች አስቀርቻለሁ፤» ባለው ዓይነት የዓለምን ፈቃድ ድል ነሥተው ሰውነታቸውን ለጽድቅ አስገዝተው የሚኖሩ ደጋግ ሰዎች ባይታጡም ከመቶው መካከል ዘጠና ዘጠኞችን የምናስደስተው ሁነን አልተገኘንም። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ፈርዶ ከመቅጣቱ በፊት ራሳችንን አጋልጠን በንስሐ ብንቀጣ ይሻላል። ማንነታችንን እያወቅነው ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እንበድላለን፤ እውነትም ከኛ ዘንድ የለም። ኃጢአታችንን ግን አምነን ብንናገር ኃጢአታችንን ይቅር ይለን ዘንድ የታመነ ቸር ነው፤ ከኃጢአታችንም ሁሉ ያነጻናል። «አልበደልንም፤» ብንል ግን እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤ ቃሉም ከእኛ ዘንድ የለም። ዮሐ 1፥8። ስለዚህ እርሱ ራሱ ቸር አባት እንደመሆኑ መጠን «ወደ እኔ ተመለሱ፤» ብሏልና እርሱን ከምናሳዝንበት ክፉ ነገር ሁሉ ተቆጥበን በፍጹም ልቡናችን በጾምና በጸሎት በልቅሶና በዋይታ በእውነተኛ ንስሐና ቀኖና ወደ እርሱ እንመለስ።



# አንቀጽ አራት

## ይህ ወቅት እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ የሆነ ወቅት ነው።

እንደ ነነዌ ሰዎች በንስሐ ተገኝተ ሆነን ወደ እግዚአብሔር ካልተመለስን እግዚአብሔር አይበለው እንጂ ገና የባሰ ጉድ እንዳለ ከወዲሁ ምልክት እየታየ ነው። ልዑል እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዝናመ ምሕረትን፣ እክለ በረከትን፣ ሥርየተ ኃጢአትን፣ ፍጹም የሆነ አምላካዊ ምሕረቱንና ይቅርታውን እንዲያደርግ ነጋ በኪዳን መሸ በቁርባን ሠርክ በጸሎተ ምሕላ ሳታቋርጥ ዘወትር የምትለምነው ጥንታዊቷና ሐዋርያዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዛሬ ያለችው በአስፈሪ አደጋ ላይ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ጠላቶቿ የቅድስና ስሟን አዋርደው «ትምክህተኞችና የነፍጠኞች ምሽግ፤» እያሉ ያለስሟ ክፉ ስም ከመስጠታቸውም በላይ ህልውናዋን ደፍረው ለማስደፈር ዕቅድ የያዙ ይመስላሉ። በአንዳንድ የቅድስና ሥፍራ ላይ የደረሰውም ጥፋት ይህንኑ የሚያመለክት ነው። ችግሩ እየገዘፈ መጥቷል። ቤንዚን አርከፍክፎ ቤተክርስቲያንን ማቃጠል ክርስቲያኖችን በተሳለ ሰይፍ እያረዱ መጣል እንደተጀመረ በዜና ቤተ ክርስቲያን ተገልጿል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባት ሁኜ ምእመናንን ለማገልገል የመሥዋዕትነት መስቀል ከጨበጥኩበትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመጨረሻው መዓርገ ክህነት ለሊቀ ጵጵስና ከደረስኩበት ጊዜያት ውስጥ ይህ ወቅት እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ የሆነ ወቅት ነው። ይህንንም ስል በቀድሞው ዘመን ችግር አልነበረም ማለቴ አይደለም፤ ያለፈው መንግሥት ክህደት ግልጽ ነው። ከማንም በላይ የከፋ «እግዚአብሔር የለም፤» ባይ በመሆኑ በሰነዘረው ዱላ ከሞቱት መካከል እርሱን በክህደት ከሚመስሉት በቀር ንጹሐን ሰዎች ለሰማዕትነት ክብር የበቁበት ዘመን ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያኒቱንም ወደ መጋዘንነት ሊለውጣት ቢዝትና ቢያስብም ለቤቱ የሚያስብ ባለቤቱ እግዚአብሔር ዛቻውንና ሐሳቡን እንዲለውጥ አድርጎ ተቃራኒዎቿ መናፍቃን በቅድስቲቱ ሀገር ሥልጣን እንዳይኖራቸው ልሣናቸው እንዲዘጋ መሰብሰቢያ አዳራሻቸው እንዲቆለፍ አድርጓል።

ዛሬ ግን መናፍቃን በቅድስቲቱ ሀገር ክምን ጊዜም በላይ ሠልጥነው የገዛ ልጆቿን እየመለመሉ ከራሷ ጉያ እውጥተው በውስጧ አደራጅተው ቤተክርስቲያኒቷን ለማፍረስና በገሀድ ማንነቷን ለማጥፋት ግልጽ ወረራ እያካሄዱ ነው።

ቀድሞ በኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ በኢትዮጵያ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ይባል የነበረ ዛሬ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስተያን፣ የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን እየተባለ ነው። .

ካቶሊክና ፕሮቴስታንት የኢትዮጵያ ለመባል ለዘመናት ታግለው በጦርነት ተፋልመው ያላገኙትን መብት ዛሬ ያለምንም ተቃዋሚ የኢትዮጵያ ለመባል በቅተዋል። ይህም በሱስንዮስ ዘመን በደንቀዝ በረሃ የፈሰሰውን የሰማዕታትን ደም ሳያስጮህ አይቀርም። እርቶዶክሳዊት ኢትዮጵያዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በረጅም ዘመን ታሪኳ ያበረከተችውን ውለታ እስታውሶ «ተዉ ሕግ አይፈቅድላችሁም» የሚል ተቆጭ የታጣበት ጊዜ ነው። ፊደል ቀርጻ ትውልድ ያስተማረች ቤተክርስቲያን የደረሰባትን ችግር የሚመለከተው አካል ፍትሕ እንዲሰጥ ለምናቀርበው አቤቱታ አንድ አንድ ቦታ ላይ መልስ ካለማግኘታችንም በላይ የብዙ ምእመናንን ጥያቄ ይዘን ስንሄድ ስሚ አጥተን መንገላታት ይገጥመናል። ቤተ ክርስቲያኒቱን ከመጥላት የተነሣ ለመንፈሳዊ አባትነታችን ይቅርና ለሰብአዊ ተፈጥሯችን የሚሰጥ ክብር የለም። «በስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤» ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል የተፈጸመው በሐዋርያት ላይ ብቻ ሣይሆን በኛም ላይ ሲፈጸም እየታየ ነው። አባቶቼ ሊቃነ ጳጳሳት የዚህ አይነት ችግር በየቦታው የገጠማቸው ለመሆኑ በተለያየ አጋጣሚ በተግባር የታየ ነው። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትልቁ ፈተናም ዛሬ ይህ ነው።

ታዲያ ዛሬ ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ከየት ወዴት እየተጓዘች ነው? ከታሪካዊነቷ ማኅፀን የተወለዳችሁ ልጆቿስ ምን እያሰባችሁ ይሆን?



# አንቀጽ አምስት

# ብሔራዊ ፊደልን መናቅ ቅኝ ተገዥነትን መናፈቅ ነው

እስኪ ወደኋላ መለስ ብላችሁ እናታችሁ ቤተ ክርስቲያን በየዛፉ ሥር «ሀሁ» እያለች ያስቆጠረቻችሁን ብሔራዊ ፊደል አስታውሱ። ዛሬ የምትኩሩበትን የጽሕፈት ሞያም በአንጨት ቅርፊት ላይ እየጻፈች አስተምራችሁ እንደነበር እስኪ ለአንድ አፍታ ትዝ ይበላችሁ። ልጅ የሚቆነጠጠውና የሚገረፈው ያስተማሩትን ፊደል ሲገድፍና ሲረሳ ነው። እናንተም የተማራችሁትን ከረሳችሁ በፈተና መውደቃችሁ የማይቀር ነው። ስለዚህ ከወዲሁ ልታስቡበትና ልትጠነቀቁበት የሚገባ ነው።

ይህች ቤተክርስቲያን በየታሪኩ አርከን ክሦስት ሺህ ዓመታት በላይ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ያበረከተች ናት። ይህንንም ስንል እንዲያው በከንቱ ለማጋነን የምንናገረው አይደለም። ብሉይ ኪዳንን በሐዲስ ኪዳን እየተረጎመችውንም በሊቃውንት አያመሰጠረች ልጆቿን ያስተማረች አስተምራም ያሠለጠነች መሆኗን ስለምናውቅ ነው። ስታሠለጥንም የዛሬን አያድርገውና በቀድሞ ጊዜ ሌላው ቀርቶ ሀሌታው ሀ ክሐመሩ ሐ፣ ሐመሩ ሐ ከብዙኃኑ ኃ፣ እልፋው አ ከዐይኑ ዐ፣ ጸድቁ ጸ ከፀሐዩ ፀ የፊደሎቹ ቅርጽ ያለቦታው እንዳይጸፍ ትቆጣጠር ነበር። ይህም የሚያኩራ ትምህርታዊ ጥበብ ነው።

ዛሬ ግን እንኳን ይህን ያህል ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደ ቅኝ ተገዥ ሀገር ፊደሏ ተለውጦ እናያለን። በመሠረቱ አንድ ሀገር በቅኝ ገዥዎች ቀንበር ሥር ወድቆ ባህሉና ታሪኩ እምነቱና

www.ethiopianorthodox.org

ሥርዓቱ ተረስቶ የማንነቱም ምልክት ሲሠረዝ እንጂ በሉዓላዊ መንግሥቱ ታፍሮና ተከብሮ ከቅኝ ግዛት ነፃ የሆነ ሀገር ያለው ዜጋ የተቀደሰ ባህሉን ሊለውጥ፥ ጥንታዊ ታሪኩን ሊረሳ፥ እምነቱንና ሥርዓቱን ሊያናንቅ ፊደሉን ሊፍቅ አይገባውም።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ሀገር ናት። በመሆኗም ማንኛውም ዜጋ በአፍ መፍቻ ቋንቋው እንዳይናገር የተከለከለበት ጊዜ ያለ አይመስለኝም። ነበረ ከተባለም ያ ጊዜ አልፏል። ባለፈ ነገር እየተቆጩ በቋንቋ አሳቦ ብሔራዊ ፊደልን መለወጥ ተተኪውን ትውልድ የሚያሳፍር እንጂ የሚያኮራ አይሆንም።

ይህንንም ስል ማንንም ለመቃወም አይደለም በተተኪው ጨቅላ ትውልድና በቅድስቲቱ ሀገር በኢትዮጵያ እንዲሁም በጥንታዊቷ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ማንነት ላይ ላነጣጠረው ችግር፦

1ኛ. ከየአቅጣጫው ተገቢ የሆነ መልስ ይገኝ እንደሆነ ብዬ፣

2ኛ. ጡቷን እያጠባች አሳድጋ በመንፈሳዊ ትምህርት አበልጽጋ፥ በከፍተኛ መዓረገ ክህነት ሰይማ፥ በሐዋርያዊ መንበር ያስቀመጠችኝ እናት ቤተክርስቲያን የወላድ መካን እንዳትሆን ስግቼ ነው። በተለይም የኢትዮጵያ ህልውና ከቤተክርስቲያኒቱ ህልውና ጋር የተያያዘ ስለሆነ ህልውናዋን ለመደምሰስ የሚፈልጉ የጠላቶቿ መበራከት አሳስቦኝ ነው።

ልበ አምላክ ዳዊት «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች፤» መዝ.67፥31። በማለት ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ፍቅር ሲገልጽ ከደቂቀ ነቢያት አሞጽና ሶፎንያስም እናንተ የእሥራኤል ልጆች ለኔ እንደ ኢትዮጵያውያን አይደላችሁምን? በኢትዮጵያ ያሉ ልጆቼ መባዬን ይዘው ወደ እኔ ይመጣሉ።» በማለት ፍጹም ፍቅርና ጠንካራ እምነት በእግዚአብሔር ላይ እንዳላት ተናግረዋል። አሞጽ 9፥7 ሶፎንያስ 3 ፥10 ስለሆነም ልዑላን ቃል ነቢያት በዚህ አኳኋን የመሰከሩላትን ኢትዮጵያን ከቤተክርስቲያኒቱ ጋር እንደ ትናንት ዛሬም ልንጠብቃት ይገባል።



የኢትዮጵያ ብሔራዊ መንግሥትም የሦስት ሺ ዘመናት አገልግሎት ለኢትዮጵያ ያበረከተችውን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ህልውና በተገቢው መልክ መጠበቅ አለበት። በጠላቶቿ ሤራ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከጠፋች ኢትዮጵያም አብራ መጥፋቷ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባዋል። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ በቀር ሌላ ታሪክ እንደሌላት በተደጋጋሚ የተገለጸ ፍንትው ያለ ሐቅ ነው። ይህ ከሆነ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ክብርና ህልውና መጠበቅ ማለት የኢትዮጵያን ታሪክና ክብር መጠበቅ ማለት ነው። እኛ አደራ በልተን እምነት አጉድለን ግን ባንጠብቅ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ትላንት የጠበቀ የማያንቀላፋ እረኛ እግዚአብሔር ዛሬም ይጠብቃል።

እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ያለ ማቋረጥ የምትዘረጋው ቅድስት ኢትዮጵያ እስከ ዛሬም እንደ ጠላቶቿ አበዛዝ ቢሆን ኖሮ ህልውናዋ ያከትም ነበር። ነገር ግን የመጣውን ፈተናና መከራ ሁሉ በሰማዕታት ልጆቿ ደም እየተከላከለችና ግርማ ሌሊትን ድምፀ አራዊትን ፀብአ አጋንንትን ታግሠው፣ ጤዛ ልሰው፥ ድንጋይ ተንተርሰው በሚኖሩ ቅዱሳን ጻድቃን ባሕታውያን ጸሎት ነው እየተጠበቀች የኖረችው። ዛሬም የሚጠፋውን በማይጠፋው፥ ጊዜያዊውን በዘለዓለማዊው ለውጠው ከዓለም ተለይተው የሚኖሩ የቅዱሳን አባቶቻችን ጸሎት ባይታደጋት ኖሮ እንደኛ ቸልተኛነት ጠላቶቿ ባገኙት አጋጣሚ ተጠቅመው ለዘመናት ሲመኙት የነበረውን ድቅድቋን ባፋጠኑት ነበር። ይሁን እንጂ አሁንም ታሪኳን ከመቀስቀሻ ቅርሶቿን ከመዝረፍ የተገታ የለም።

www.ethiopianorthodox.org

# አንቀጽ ስድስት

## ዘመናችን ያፈራው ትውልድ አታላይ ብቻ ሳይሆን ሾተላይም ነው

ሾተላይ፡- ዓይኑ ያረፈበትን ለጥፋት የሚዳርግ ነው ይባላል፤ ይህም ትውልድ እግዚአብሔርን የማይፈራ፥ ለእናት ሀገሩ የማይራራ የቅርስ ቀበኛ ከመሆኑ የተነሣ፡- በዓይኑ ያየውን፥ በእጁ የገባውን ሁሉ ጽላት ሳይቀር የሚዘርፍ ደፋር ነው:: እኔም በዚህ የምጽአት ዘመን በእናቴ ላይ የሚደርሰው ፈተና እጅግ እያ ስጨነቀኝ ነው:: ከልቤም እያስለቀሰኝ ነው:: እኔና መሰሎቼ የታሪክ ሸክማችንን መሸከም ያቃተን እየመሰለኝ ልቤ በኃዘን እየደማ ነው:: በእቅሜ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ለመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ ይህን እንደ ኑዛዜ ቃል ኀዘን ባደቀቀው ኅሊናዬ የማስ ተላልፈው የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን የሚያድን መስሎኝ ነው:: በርግጥም የሚተላለፈው መልእክት እውነት እስከሆነ ድረስ በታሪክ ከመወቀስ ማዳኑ የማይቀር ነው:: እንደሚታወቀው ቀድሞም አባቶቻችን ሰማዕተ ጽድቅ /የእውነት ምስክሮች/ ለመባል የበቁት፥ በታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ድነው ሕያው ታሪክ ያተረፉት፥ ስደት እስራትና ሞት ሳይፈሩ እውነት ተናግረው በአደባባይ መስክረው ነው:: ይህን የሚያውቅ ትውልድ ግን በአሁኑ ጊዜ አልተገኘም:: በተለይም ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ አደራ ተቀባይ የቅርስ ባለቤት መሆኗን የተገነዘበ የለም እንዲያውም የቅርስ ባለቤትነቷን ለማሳጣት ቅርሶቿ የሚገኙበትን መንገድ ለመሰለል ባሕር ተሻግረው የመጡ ብዙ ናቸው:: እንዚ ህም በዕለታዊ ጥቅም ከተሸነፉ በረኞቿ ጋር እየተመሳጠሩባት ይገኛሉ:: የዛሬን አያድርገውና ማንም እንደሚያውቀው፥ ከጥንት ጀምረው የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታትና መላው ሕዝበ ክር ስቲያን፥ ቤተክርስቲያን የታመነች አደራ ጠባቂ የእግዚአብሔር



ግምጃ ቤት መሆኗን ስለአመኑ ንብረታቸውን ያወርሱ የነበር ለቤተክርስቲያን ነው::

ከዚህም የተነሣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በቤተክርስቲያን ውስጥ የማይገኝ ቅርስ አልነበረም:: በየጊዜው ሲያደቡባት የኖሩ ተቃራኒዎቿ ግን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በረቀቀ ስልት ሻጭና ገዥ በመሆን ቅርሷን አሟጠው ወስደውታል:: ያልተወሰደውም በመቃጠል ላይ ይገኛል::

የጥንታዊቷ የአንሻ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በእሳት ቃጠሎ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የተገመቱ ጥንታውያን መጻሕፍትና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት ተቃጥለዋል:: በሰሜን ሸዋም የተደራጁ ሰዎች ከመስኖ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ብዙ መስቀሎችን ከሰረቁ በኋላ ጥቅሙን ለመካፈል ባለመስማማታቸው ባነሡት ግጭት አንድ ሰው ሞቶ እንደነበር በጊዜው በዜና ሰምተነዋል:: በጋዜጣም አንብበነዋል:: ይህ ሁሉ ሰዎች እስከምን ድረስ ለገንዘብ ተላልፈው መስጠታቸውን ያመላክተናል:: ሐምሌ 22 ቀን 1993 ዓ.ም. በሰላሌ ህገረ ስብከት ጥንታዊውን የደብረ ፍስሐ ሽንኩርት ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ጠባቂውን ገድለው ንዋያተ ቅድሳቱን ዘርፈው ሔደዋል::

እጅግ ጥንታውያን ከሆኑት ገዳማት መካከል ብዙዎቹ ተዘርፈዋል:: ተበርብረዋል፣ አንዳንዶቹንም በእሳት አቃጥለዋ ቸዋል:: የደብረ ጽዮን ስምና ማርያም ቤተ ክርስቲያን (ደቡብ ጎንደር)፣ የጥንታዊው የደውክና ዐማኑኤል ገዳም (ሰሜን ጎንደር)፣ የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ገዳም /አዊ ዞን/ ሙሉ በሙሉ የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው:: በሰሜን ወሎ የሚገኘው የወረኢሉ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት፣በሰሜን ሸዋ አንኮበር የምትገኘው የደረፎ ቅድስት ማርያም ዕቃ ቤት ደግሞ በቃጠሎ ንዋያተ ቅድሳታቸውንና ቅርሶቻቸውን ካጡት ብዙ ገዳማትና አድባራት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው:: የእነዚህ የመቃጠ ላቸው ዜና አዲስ አበባ ስለደረሰ እንደ ስምዐ ጽድቅ ባሉ ጋዜጦች ተመዝግቦ አንብበነዋል::

www.ethiopianorthodox.org

ከላይ እኔ የገለጽኳቸውን በዚሁ ጋዜጣ ላይ መመልከት ይቻላል:: ይህም ብዙ ዜናቸው ያልተበማና ጉዳታቸው ባይታወቅ በዚህ ትውልድ የተመዘበሩ፣እንደሾተላይ አይቶ፣እንደቀበኛ አላምጠና አድቅቆ ያጠፋቸው መኖራቸውን ያባየናል:: ከዚህ የተረፉት ደግሞ አሁንም ወደ ውጭ ሀገር እየተወሰዱ በመሸጥ ላይ ናቸው:: በቅርቡ በ1994 ዓ.ም. እንኳን ሰንደን ላይ ብቻ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት በ14 ሚሊዮን ብር ለሽያጭ በይፋ ገበያ ላይ ቀርበው ነበር፣የጥንታዊው የጣና ቂርቆበን ገዳም ደግሞ አንድ ግሰበብ ብቻውን ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን ንብረት እንደዘረፈው ፖሊስ መግለጹን በበምዐ ጽድቅ ጋዜጣ የኅዳር 1994 ዓ.ም. እትም ላይ ተመልክተናል:: እስከ አሁንም ድረስ እየወበዱት ነው:: ከሀገር ወጥተው በተለያዩ አህጉራተ ዓለም ገብተው ከሚገኙት ቅርሶቻችን መካከል ከ2737 በላይ የሚሆኑት ቅርሶቻችን በአሥራ ሦበት አህጉራተ ዓለም እንደሚገበኙ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የወጣው «ቅርስ» የተበኘው መጽሔት እንደሚገልጽ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በሃያ ዘጠነኛው ስምሪት አስገንዝቧል::

ቢወበዱትም በአንድ አንድ ሐቀኞች ኢትዮጵያውያን ጠቋሚነት ዘራፊዎቹ በድንገት መጋለጣቸው አልቀረም:: ይህንንም ወረራና ዘረፋ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ተባብሮ ጊዜ ባይሰጥ ባበቸኳይ ሊያበወግደው ይገባል:: በመሠረቱ አባቶቻችን ያስረከቡን ኢትዮጵያን ከነዳር ድንበሯ፣ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስተያን ከሥርዓተ እምነቷና ታይተው ከማይጠገቡት ቅርሷ ጋር እንደነበረ ታሪክ ምስክር ነው::

እንግዲህ ወገኖቼ የተረከብነውን አስወስደን ሰነገው ትውልድ የምናበረክበው ብናጣ ተተኪው ትውልድ ይቅርና በቤተክርስቲያን የረገፈው የአባቶቻችን ዐፅም ጦር ሆኖ ይወጋናል! በይፍ ሆኖም ይቆርጠናል:: በስዚህ ከአባቶቻችን በወረሳችሁት ብሔራዊ በሜትና ጀግንነት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር እንዳበከበራችሁ ሁሉ የቤተክርበቲያንንም ቅርበ ለማስከበር ኅብረታችሁ ይጠንክር::



ችግሩ በቀላል የሚታይ አይደለም:: ንዋያተ ቅድሳት ከቤተክርበቲያን በምክንያት እየወጣ ወደ ሌላ ሐዶ በባለቤትነት የሚያዙበት ከሃይማኖታችን ውጭ የሆኑ በዎች ከሆኑ ኢትዮጵያን የቢዛንታይን እድል እንዳጋጠማት የሚያረጋግጥ ነው:: ሆኖም ቢዛንታይን ወደ ቱርክነት የተሰወጠችው ክርስቲያኖች በሞት ከተሰወጡ በኋላ እንደነበረ ይታወቃል:: ኢትዮጵያ ግን ከአርባ አምስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የእርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ያሉባት የታደለች ሀገር ናት:: ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ አድባራትና ገዳማቷ አስተዋሽ፣ ጠባቂና ተቆጣጣሪ ያሏቸው መስሎ አይታይም:: እንደ ደብረ ዳሞ ያሉት ጥንታውያን ገዳማት ከአምበተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ የነበራቸው ቅርስ ሰእሳት ተዳርጓል:: እንደ አዲስ ዓለም ማርያም ያሉት የነገሥታት ንብረት ባለአደራ የሆኑ ታላላቅ አድባራት ተመሳሳይ ጥቃት ደርሰባቸዋል:: እንደ አበቦት ባሉት ገዳማት የሚኖሩ መናንያን መነኮባት በኢትዮጵያዊነታቸው ሠርተው ለመኖር ቢጥሩ የነበራቸውን ይዞታ ተቀምተዋል:: በየጊዜው ዘረፋ ሊካሄድባቸው ይታያል:: ይህንንም ችግር ትክክለኛ ፍትሕ በጥቶ ሊያበወግደው የሚችል ባለመገኘቱ የክርበቶበን ፍርድ የሚጠብቁ ሁኗል:: እንደሚታወቀው ቀድሞም ሆነ ዛሬ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተክርበቲያን እውነተኛው ቤዛ ክርበቶበ ብቻ ነው::

በመሆኑም በማይቋረጥ ጸሎት እንደ አቡነ ጴጥሮስ ይግባኝ ለክርበቶበ እያሉ ተባብሮ ለመጮህ መሰሎቼ ለሆኑት አባቶቼና ለመላው ሕዝበ ክርበቲያን ጥሪዬን አበተላልፋለሁ::

ወበብሐት ለእግዚአብሔር አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

## የሰማዕቱ የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ አጭር ታሪክ ፐሮፌሰር ስሽን ሩቢንሰን እንዳቀረቡት

ይህ ታሪክ በፀረ ቅኝ አገዛዝና ፀረ ጭቆና ትግል ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ ውስጥ በግፍ የተሰዉ የአንድ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ታሪክ ነው:: አቡነ ጴጥሮስ ይባላሉ:: ከአዲስ አበባ ሰሜን አቅጣጫ ወደ ዓባይ ሲጓዙ መንገድ ላይ በምትገኘው ፍቼ ከተማ ውስጥ በ1884 ዓ.ም ተወለዱ:: ስመ ጥምቀታቸው ኃይለ ማርያም ነበር:: የተለየ የጵጵስና ስም የተሰጣቸውና አቡነ ጴጥሮስ የተባሉት እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለመዐርገ ጵጵስና ሲበቁ ነው :: በወጣትነት ዘመናቸው በተወለዱባት ፍቼ ከተማና በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ታታሪና ትሑት በመሆናቸው ዕውቅናን አተረፉ:: የአብነት ትምህርት ለመማር የመረጡት ገና በልጅነታቸው ነው:: በ24 ዓመታቸው ሥርዓተ ምንኵስናን ፈፀሙ:: በፍቼና በወላይታ አካባቢዎች በነበሩት ገዳማት ዘንድም ስመ ጥር መምህር ሆኑ:: ለዚህም ነበር በ1910 ዓ.ም በወላይታ አካባቢ ለምትገኘው የደብረ መንክራት ገዳም ለደብረ ጽዮን ማርያም መምህርና ቀዳሽ ሆነው የተሾሙት:: እስከ 1916 ዓ.ም በዚህች ገዳም አገለገሉ:: ከዚያም ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ ሲጓዙ ዝዋይ ደሴት ላይ ለምትገኘው ለአመቤታችን ገዳም መምህር ሆነው እንዲያገለግሉ ተመደቡ:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው «... እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ... ምሕረትን፣ ርኅራኄን፣ ቸርነትንና ትሕትናን...» የተላበሱ ስለ ነበሩ በዝዋይ ደሴቶችና በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ተናፋቂ መምህር ሆኑ:: /ቆላ. 3፥12/ ትምህርታቸውና ስብከታቸው በሚለግሰው አክብሮት የተነሣ በደቀመዛሙርቶቻቸው ዘንድ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ ፍቅርና ክብርን አተረፉ::

በ1921 ዓ.ም ዐራት ኢትዮጵያውያን አባቶች ተመርጠው በመንበረ ማርቆስ /የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን/ ፈቃድ ጳጳሳት ተብለው ሲሾሙ ከእነዚህ አንዱ አቡነ ጴጥሮስ ተብለው የተሾሙት መምህር ኃይለ ማርያም ነበሩ::

እንደተሾሙም የመካከለኛውና የምሥራቅ ኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው ተመደቡ:: በቆይታቸው ግማሽ የሚሆነውን ጊዜ በደሴ



ከተማና በአካባቢዋ በሚገኙት ገዳማት፣ ቀሪውን ደግሞ በወረኢሉ አካባቢ የሚገኙ ገዳማትን በመጐብኘትና በማስተማር አሳልፈዋል:: በእነዚህ ሁለት አካበቢዎች /ደሴና ወረኢሉ/ ይሠሩት የነበረው የቤተክርስቲያን አስተዳደር ሥራ የተቃና ይሆን ዘንድ ከሁለቱም አካባቢዎች አንዳንድ ካህናት በረዳትነት ተመደቡላቸው:: ልክ እንደ ዝዋይ ሁሉ በደሴና ወረኢሉም ትምህርታቸው ተወዳጅ ነበር:: ለእምነታቸው ቀናኢና የክርስቶስን አርአያነት በትጋት የሚከተሉ ስለነበሩ በመንፈስ ልጆቻቸው ዘንድ ሁሉ የሚናፈቁ ሆኑ:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለወደፊት እንደምናነበው «ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቷችኋልና ስለርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም» የተባለውን በሕይወታቸው ተግብረዋል:: /ፊልጵ. 1፥29/

በፋሽስት መሶሎኒ ትመራ የነበረችው ኢጣሊያ በ1924 ዓ.ም ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ስትወር አቡኑ ከንጉሠ ነገሥታቸው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከጦራቸው ጋር ወደ ሰሜን ግንባር ዘመቱ:: ቁስለኞችን በማጽናናት፣ ለሰማዕታት ጸሎተ ፍትሐት በማድረስና ወንጌልን በመስበክ ይተጉ ነበር:: በሰሜን ግንባር ቆይታቸው የወራሪውን ኃይል አሸባሪነትና ብልግና በዐይናቸው አዩ:: ያ ግፈኛ ጦር ንጹሐንንና ቤት ንብረታቸውን፣ ሳር ቅጠሉን፣ ... ወዘተ በመርዝ ጋዝ ና በሌሎችም በተራቀቁ የጦር መሣሪያዎች ሲያጋይና በስተመጨረሻም የማይጨው ጦርነት ባለድል ሲሆን ተመለከቱ:: ከዚህ አስቃቂ ትእይንት በኋላ አርበኞቹ ለማፈግፈግና ወራሪውን ኃይል በሽምቅ ውጊያ ስልት ለመፋለም ሲወስኑ ብፁዕነታቸውም ያንን ዘግናኝ ድርጊት በኅሊናቸው እንደሳሉ ወደ መሐል ሀገር ተመልሰው በደብረ ሊባኖስ ገዳም እንዲ ተጠለሉ:: የገዳሙን መነኰሳትና ካህናትም በጾምና በጸሎት እንዲ ተጉ አደረጉ:: ራሳቸውም በጾምና በጸሎት ተጠምደው እግዚ አብሔር የኢትዮጵያን ሕዝብ በምሕረት እንዲታደግ እየተማጠኑ መ ወደፊት ለሚጠብቃቸው ታላቅ ተጋድሎ መዘጋጀት ጀመሩ:: መ ጽሐፉ «ይህ ናፍቆቴ ተስፋዬም ነውና፤ በአንድ ነገር እንኳ አላፍርም፤ ነገር ግን በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት ክርስቶስ በግልጥነት ሁሉ እንደወትሮው አሁን ደግሞ በሥጋዩ ይከብራል» /ፊሊጵ. 1፥20/ እንዳለው ማለት ነው::

በስብከታቸው ሁሉ ብፁዕነታቸው የሚከተለውን ጥያቄ ይሰነዝሩ ነበር:: «እንዴት ራሷ ክርስቲያን ነኝ የምትለው ሀገር ጣሊያን ክርስቲያን በሆነችው ኢትዮጵያ ላይ እንዲህ ዓይነት

www.ethiopianorthodox.org

እጅግ ዘግናኝ የሆነ የሽብር ተግባር ትፈጽምባታለች?» አቡኑ
ይህን ጥያቄ የሚሰነዝሩት ክርስቲያኖችን ሁሉ በእኩል ይመለከቱ
ስለነበረ ነው። ለእርሳቸው ሁሉም ክርስቲያኖች ክርስቶስን
በመንግሥተ ሰማይ ለማግኘት በተስፋ የሚናፍቁ የዚህች ዓለም
መጻተኛ ወንድማማቾችና እኅትማማቾች ነበሩ። ስለዚህ ሊደጋገፉ
እንጂ ሊጨካከኑ አይገባም። እንዲህ በማስተማር ነበር የወደፊት
ፈታኝ ተጋድሎአቸውን የጀመሩት። ወራሪው ኃይል እየፈፀመው
የነበረውን ጭካኔ የተሞላበት ተግባር አጥብቀው ማውገዛቸውን
በድፍረት ተያያዙት። በወቅቱ ወራሪው የፋሽስት ኃይል
በሳማውያን ዜጐችን ያለ ርኅራኄ ያሰቃይ /ይደፍር፣ ይጨፈ
ጭፍ፣ . ./ ነበር። ይህንም የሚያደርገው በወቅቱ በሰው ኃይልና
በመንፈስ እየበረቱ የመጡትን አርበኞች አያገዛችሁ ነው በሚል
ጥርጣሬ ነበር። በወቅቱ ከፍርሃታቸው የተነሣ የወራሪውን ኃይል
የበላይነት ተቀብለው በስሩ ለማደር የጀመሩ ጥቂት የቤተ
ክርስቲያኒቱ ካህናት ነበሩ። ወራሪው ጦር በነዚህ ባንዳ ካህናት
አማካይነት ወደ ተከበሩት አቡን ጦማር /ደብዳቤ/ ላከ። ይዘቱም
«የጣሊያንን ኃያልነት አምነህ ተቀበል፤ ፀረ ጣሊያን ስብከትህንም
አቁመህ ከኛ ተባበር፣ ይህን አሜን ብለህ ከተቀበልህ አዲስ አበባ
ውስጥ ምርጥ ቤት ተሰጥቶህ የተንደላቀቀ ኑሮህን ትገፋለህ»
የሚል ነበር። አቡኑ ግን ነገሩን በእግዚአብሔርና በክርስትናቸው
ላይ ያምፁ ዘንድ እንደተዘረጋ ወጥመድ ቆጠሩት። መልእክቱን
ውድቅ አድርገው እዚያው ደብረ ሊባኖስ ገዳም ውስጥ ይበልጥ በ
ጸሎትና በጾም ተግተው ቆዩ። «ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ
ክርስቶስ መነቀፉ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቧልና
ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ
ጋር መከራ መቀበልን መረጠ» ተብሎ እንደተጻፈለት ነቢይ
እርሳቸውም የሕዝባቸው ሙሴ ሆኑ። /ዕብ 1፥25-26/

የአርበኝነት ተጋድሎውም እንደበደድ እሳት በመላው ኢ
ትዮጵያ ተዳረሰ። በተለያዩ የጦር ግንባሮች አርበኞች አሸነፉ።
ብፁዕነታቸውም ሕዝባቸው በእምነቱ እንዲጸና፣ እግዚአብሔርም
በግፍ የተረገጠች አትዮጵያን ሳይዘገይ እንደሚጐበኛት በትጋት
ማስተማራቸውን ቀጠሉ። «ለእናንተም ለወዳጆቼ እላችኋለሁ፤
ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳ የሚበልጥ ሊያደርጉ
የማይችሉትን አትፍሩ። እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፤
ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ። አዎን፤
እላችኋለሁ እርሱን ፍሩ።» በማለት ክርስቶስ የተናገረውን አም
ልተው፣ አስፍተው ያስተምሩ ነበር።/ሉቃ. 12፥4-5/ በዚህም



ጣሊያን ኢትዮጵያን መውረሯ ውጉዝ እንደሆነና ሕዝባቸውም
የፍርሃት መንፈስ እንዳይገዛው ዘወትር ሳይታክቱ አስረድተዋል።

አዲስ አበባ የነበሩት የፋሽስት መስሎኒ ወኪሎችም የአ
ቡነ ጴጥሮስን ኢትዮጵያውያንን የማደፋፈር ስብከት ለማኮላሸት
ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። አቡኑ በሕዝቡ ዘንድ የነበራ
ቸው ተቀባይነት ከፍተኛ መሆኑን የተገነዘቡት እነዚያ ባለ
ሥልጣናት አቡነ ጴጥሮስን ከማሰርና ከመግደል ይልቅ አግባብተ
ለጣሊያን እንዲወግኑ ማድረጉ እንደሚመረጥ ግልጽ ሆኖላቸው
ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ በወርኃ ሐምሌ 1928 ዓ.ም አርበኞች
በአዲስ አበባ ላይ ጥቃት ሰነዘሩ። በዚህ ጊዜ አቡኑ የክብር
ልብሳቸውን ለብሰው፣ ከቢጫ መሐረም ጋር የሚይዙትን የእጅ
መስቀላቸውን እንደያዙ ወደ አዲስ አበባ ሰተት ብለው ገቡ።
በይፋ ፀረ ፋሽዝም ስብከታቸውን በወረራ ተጠፍሮ ለሚተ
ክዘው ሕዝባቸው ያሰሙ ጀመር። በዚያን ጊዜ ነበር የፋሽስቱ
ወታደሮች አቡኑን በቁጥጥር ስር አውለው በጣሊያን መንግሥት
ላይ ፈፅሙት ለተባለው ክህደት ፍርድ ቤት እንዲያቀርቡባቸው
ትእዛዝ የደረሳቸው። እንደታዘዙትም አደረጉ። ብፁዕነታቸው
በእስር ቤት ሆነው ለፍርድ የሚቀርቡበትን ጊዜ እየተጠባበቁ
እያለ በበርካታ የፋሽዝም ባለሥልጣናትና በባንዳ ቀሳውስት
ይለመኑ ነበር። ጣሊያን ያስፈነችውን የወረራ አገዛዝ ተቀብለውት
ቡራኬያቸውን ይቸሩት ዘንድ። ሆኖም ግን እርሳቸው ከአቋማቸው
ዝንፍ እንደማይሉ ሊታወቅ የሚከተለው ዛቻ /ማስፈራሪያ/
ደረሳቸው። «የታላቁ መሶሎኒ ጦር እየወሰደው ያለውን ርምጃ
ማውገዝህን አቁም፤ የጣሊያንንም የበላይነት ተቀበል፤ አርበኞችን
ቀማኞች ናቸው ብለህ አውግዝ፤ ይህን አልፈጽምም ካልህ ሕ
ይወትህን ታጣለህ» ተባሉ። ብፁዕነታቸው ግን ምንም ሰቆቃ ቢ
ጸናባቸውም ከቀረቡላቸው ግዴታዎች ውስጥ አንዱንም ለመፈፀም
ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። በአስተርጓሚ በኩልም ለሚጠይቃቸው
የፋሽስት መንግሥት ሹም የሚከተለውን ተናገሩ። «በነርብ ጋዝና
ሌሎች የሽብር ጦር መሣሪያዎች የፈጀሃቸው የሀገሬ ልጆች
ያሰሙት ሰቆቃና ለቅሶ መቼም ቢሆን ኀሊናዬ ለዛቻህ
እንዳይንበረከክ ያደርገኛል። የእናንተን አበቃቂ ወንጀል
እንዳላየሁኝ ዝም ብል እንዴት አድርጌ ነው ፈጣሪ አምላኬን
የማየው? እርሱ ምን እንደሚል ታውቃለህን? ጽድቅን
የምታውቁ ሕጌም በልባችሁ ያለ ሕዝብ ሆይ ስሙኝ፤ የሰውን
ተግዳሮት አትፍሩ፤ በስድባቸውም አትደንግጡ። እንደልብስም

www.ethiopianorthodox.org

ብል ይበላቸዋል፤ እንደ በግ ጠጉርም ትል ይበላቸዋል፤ ጽድቁ ግን ከዘላለም ማዳኔ ለትውልድ ሁሉ ይሆናል:: በስጽድቅ የሚሰድዱ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና:: ይላል» አሉት:: /ኢሳ. 51፥7-8/ ፣ /ማቴ.5፥10/

ከዚህ በኋላ በጥድፊያ የተሰየመው ችሎት በብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ላይ ሞት ፈረደባቸው:: የዚህ ዘግናኝ ውሣኔ ወሬው በመላው ሀገሪቱ ተዳረሰ፣ አቡኑ ተወዳጅ ነበሩና:: ለእግዚአብሔር አውነተኛ ጥሪ፣ ተወዳጅ ኢትዮጵያውያንን ከግፈኞች ለማዳን ተልዕኮ ራሳቸውን የሰጡትን ተወዳጁን ጳጳሳቸውን ለመሰናበት በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ አዲስ አበባ ተመሙ:: ይህ ሁሉ የሞት ዛቻ ሳይበግራቸው ለሀገርና ለሕዝብ ነጻነትና ክብር ሲሉ የፈጸሙትን የምዕተ ዓመት ጀግናቸውን ሊሰናበቱ ብዙዎች ተጓዙ::

ይህን ሕዝቡ ለጳጳሱ ያለውን ጽኑ ፍቅር የተረዳው ወራሪው ጦር እርሳቸውን ከእስር የማስለቀቅ ሙከራና ሌሎችም ዓመፆች ይካሔዱ ይሆናል የሚል ስጋት አደረበት:: ስለዚህ የሞት ቅጣቱ በአስቸኳይ እንዲፈጸም ተወሰነ:: አቡኑ ወደ ሞት እደባባይ ተወሰዱና የመጨረሻ ንግግራቸውን ይናገሩ ዘንድ ተጠየቁ:: መስቀላቸውን አንሥተው ሕዝባቸውን በሀራቱም አቅጣጫ ከባረኩ በኋላ የሚከተለውን የመጨረሻና ወርቃማ ንግግር ተናገሩ:: «የተወደዳችሁ የሀገሬ ልጆች፣ አርበኞችን ቀማኞች ናቸው ብለው ፋሺስቶች ቢያወሩላችሁ አትመኑ:: አርበኞች እነማን እንደሆኑ እኔ እነግራችኋለሁ:: አርበኞች ፋሽስቶች ከሚነዙት ሽብር ነጻ ለመውጣት እጅግ የሚናፍቁ ንጹሐን ናቸው:: ቀማኞችስ በእኔና በእናንተ ፊት ቆመው የምትመለከቷቸው ከሩቅ ሀገር መጥተው ሰላማዊ ሀገራችንን ኢትዮጵያን በጉልበት የሚያሸብሩት ወታደሮች ናቸው:: ለፋሽስት ወታደሮች መቼም እንዳትንበረከኩ የመቋቋም ብርታቱን እግዚአብሔር ለኛ ለኢትዮጵያውያን ያድለን:: ምድሪቱም የወራሪውን ጦር አገዛዝ አሜን ብላ ብትቀበል የተወገዘች ትሁን» አሉ:: ከዚያ በኋላ በተወዳጁ ጳጳስ ላይ የጥይት ሩምታ ዘነበባቸው::

ከርሸናው /ከግድያው/ በኋላ የፋሽስቱ ጦር በአቡነ ጴጥሮስና በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸመውን ግፍ ለመደበቅ ሲል ምንም ዓይነት ጽሑፍ ስለ እርሳቸው እንዳይጻፍ ከለከለ:: ይህ የተወሰነው በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ አቡኑ የነበራ



ቸው ዝና ጣሊያን አያራመደች የነበረውን ኢትዮጵያን ቅኝ የመግዛት ፓሊሲ ጥላ ያጠላበታል ከሚል ስጋት ነበር:: በወቅቱም የጣሊያን ድርጊት በሀገር ውስጥና በውጭ ተቃውሞ እየበረታበት ስለነበረ የአቡነ ጴጥሮስ የሰማዕትነት ዜና ሁኔታውን ያባብሰዋል የሚል ሥጋት በፋሽስቶቹ አድሮ ነበር:: ምንም እንኳ የጭካኔ ድርጊቱን ለመደበቅ ጥረት ቢደረግም እውነትን በሚናፍቁ ዘንድ የአቡነ ጴጥሮስ ገድል እስከ ዛሬ ድረስ ብሩህ ሆኖ ይኖራል:: ከሁሉም የበለጠው የአቡኑ ሰማዕትነት አስተዋጽኦ ግን የፀረ ፋሽዝም ትግሉን የበለጠ ማቀጣጠሉ ነበር:: የፋሽስቱ ጦር በሀገሬው ዘንድ ተአማኒነት ከማጣቱም ባሻገር በርካታ ኢትዮጵያውያን የፋሽስቶች ጠንካራ ይዞታ የነበረችውን አዲስ አበባን እየለቀቁ አርበኞችን የመቀላቀልና ለነጻነታቸው የመዋደቅ ወኔን ተላበሱ:: የአርበኝነት ትግሉም የበለጠ እመርታን አግኝቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀገሪቱ ነጻ ለመሆን በቅታለች::

የእኚህን ታላቅ ሰማዕት የመጨረሻ ሰዓታት ተወዳጅና በቅርብ ጊዜ ያረፈው ገጣሚ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን «ጴጥሮስ ያችን ሰዓት» በሚል ቲአትሩ ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል:: በሰማዕትነት ካለፉ ከአሥር ዓመት በኋላ የቆመ የእርሳቸው ሐውልት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይገኛል:: ይህም እስከ ሞት ለእውነት መታመንን፣ ለሰው ልጅ ክብር በጽናትና በቆራጥነት መጋደልን፣ በሐሳፊ ድሎት ወይም ዛቻ ተሸንፎ ክብርን አለማጉደፍንና ከሁሉም በላይ ሁላችንም አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ቆመን ስለሠራነው ተግባር መጠየቃችን ስለማይቀር በእምነት መጽናትን ለትውልድ ይናገር ዘንድ ቆሟል:: ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር!!!

## ምስጋና

በሀገረ ስዊድን የምትገኘው የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋህሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለተደረገላት ድጋፍ ሁሉ ሰማዕቱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የምዕተ ዓመቱ ሰማዕታት ከሆኑት ውስጥ አንዱ አድርጎ በማሰብ በኩል ባሳዩት ጥረት የስዊድንን ቤተ ክርስቲያን በተለይም የስትራንጋስ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የሆኑትን አባ ዮናስ ጆንሰንን ታመሰግናለች::

ፕሮፌሰር ስቨን ሩቢንሰን

www.ethiopianorthodox.org